

የብልጠት ተረቶች
ገድለ አርሴማ ሲፈተሽ
ቴዎድሮስ ደመላሽ

# የብልጠት ተረቶች

## ገድለ አርሴማ በቃለ እግዚአብሔር ሲፈተሽ

ቴዎድሮስ ደመላሽ
ዐዲስ አበባ

© ቴዎድሮስ ደመላሽ

የአዘጋጁ መብት በሕግ የተጠበቀ ነው፡፡
All right reserved

የመጀመሪያ ዕትም መጋቢት 2010 ዓመተ ምሕረት
ለሁለተኛ ጊዜ የካቲት 2014 በስስ ከፒ (በPDF) ለንባብ
በቃ

## አበርክቶት

መጽሐፉ ሲዘጋጅ በብዙ መልኩ ድጋፍ ላደረጉልኝ ለና. የወ. አ. ማኅበር አባላት ይሁንልኝ፡፡

## የሽፋን ስዕል

ቴዎድሮስ በዛብህ

## የአዘጋጁ አድራሻ፤

ስልክ +251 94 66 57 513
E-mail: tewoderosdemelash@gmail.com
Facebook: www.facebook.com/tewoderodemelash

# ምስጋና

ከእርሱ በሆነው ፍቅሩ ለወደደኝ፣ መጠን በሌለው ምሕረቱ ይቅርታውን ላበዛልኝ፣ ብቻውን ለነፍሴ መድኅን ላዘጋጀልኝ ሁሉን ቻይ ለሆነው አምላክ ለልዑል እግዚአብሔር ክብርና ምስጋና ይሁን፤ አሜን!

ብዜ፤ አንቺ ከጎኔ መሆንሽ ምን ማለት እንደ ሆነ እኔና እግዚአብሔር እናውቃለን። በቀጥታ የሥራው አካል ከመሆንሽም ውጪ በተረጋጋ መንፈስ ሥራዬን እንድሠራ ቤት ውስጥ የምታደርጊው ነገር ልብን የሚያሳርፍ ነው፤ አንቺን የሰጠኝ አምላክ ይባረክ። ስለ እኔ ዘወትር በመጸለይ በብዙ የምትተጊው እናቴ እግዚአብሔር አምላክ እድሜና ጤና ይሰጥሽ ዘንድ እጸልያለሁ። በረከቶቼ የሆናችሁት ያኪን፣ ምስጋናና ባርኮት ለእግዚአብሔር ክብር የምትሆኑ ሁኑ!!

መጽሐፉ ከነስሕተቱ እንዳይወጣ የፊደል እርማት በመሥራት፣ ሐሳብ በማቃናት፣ መረጃ በመጠቈምና አባታዊ ምክር በመስጠት ከጎኔ የነበሩትን መሪጌታ ሠረቀ ብርሃን ዘወንጌል እግዚአብሔር አምላክ እድሜና ጤና ይስጥልኝ።

የሽፋን ስዕሉን በመሥራትና በሞያው አይዞህ በማለት እየደገፈኝ ያለውን ወንድሜን ቴዎድሮስን እግዚአብሔር የእጅህን ሥራ ሁሉ ይባርክ እላለሁ። ወንድሜ ምትኩና ባለቤቱ አዲስ እግዚአብሔር የሰጠኝ ቤተሰቦቼ ናችሁ። በብዙ ጠቅማችሁኛል፣ በብዙ አበረታታችሁኛልና እርሱ ብድራታችሁን ይመልስ!

እናቴ ጥበበ፣ ወንድሜ በለጠና እኅቴ ሰናይት ከአገልግሎቴም አልፋችሁ ጓዳዬ ድረስ በመግባት ለምታደርጉልኝ ቤተሰባዊ ድጋፍ ሁሉን ቻዩ አምላክ ከጎናችሁ ሆኖ ጉድለታችሁን ይሙላ!

ምንም እንኳን ያለበት ሁኔታ ጥሩ ባይሆንም መጽሐፉ ታትሞ ለንባብ እንዲበቃ ከነበረው ጉጉት የተነሣ ከአቅሙ በላይ የሆነ ድጋፍ ያደረገለኝ ወንድሜን ዳዊትን እግዚአብሔር አምላክ በነገር ሁሉ ከእርሱ ጋር ይቁም! ይባርክም!

# ማውጫ

መቅድም ........................................................ 6
አርሴማ ማን ናት? ................................................ 11
ትውልዷ ........................................................ 13
ትምህርቷ ...................................................... 15
ውበቷ .......................................................... 15
ውበቷን ያዩ ሰዎች ልብ ታወከ ........................................ 15
ከውበቷ የተነሣ መብራት ወይም ብርሃን አያስፈልጋትም .. 17
ሰማዕት ለመሆን ለምን ፈለገች? ...................................... 19
በራስዋ መንግሥተ ሰማያትን ተቀዳጀች ................................ 21
ለሰው መዳን ያላት ልብ .............................................. 22
እውነትን ለመመስከር ፍላጎት የላትም .................................. 22
በአምላክሽ ልመን ያላትን ለመርዳት ፈቃደኛ አለመሆኗ ..... 23
ጸሎቷ .......................................................... 27
በጸሎቷ ለሚያምኑ... ............................................... 27
ነፍሰ ገዳይ እንዳልባል ............................................. 28
ሕያው እንደ ሆነ ወደ ሲኦል ይውረድ! ................................ 30
ስግደት ........................................................ 33
ሚካኤልና ገብርኤል ‹‹ነፍሴን እጅ ነሷት›› ............................ 33
ትሰግድላቸዋለች... ይሰግዱላታል ..................................... 34
በልቤ ጉልበት እንጂ በሥጋዬ ጉልበት አልሰግድልህም ....... 35
የስድብ አፍ ..................................................... 36
ለቸርነቷ ልማድ ወሰን የለውም ......................................... 40
ወደ ዘላለም ሕይወት የምትመሪ ......................................... 42
‹‹መድኀኒታቸው ነሽ›› ................................................ 44
አፏን ሳመቻት ................................................... 45
በአርሴማ ስም... ያደረገ... የዘላለም ሕይወትን ይወርሳል .. 46

ኑ እናመስግናት ........ 52
ማርያምና አርሴማ ........ 54
ማርያምን ያመሰግኗታል ........ 57
አርሴማ፤ ለኑሮ ሀብት የምታሰጥ........ 61
አርሴማ፤ ከእሳት ባሕር የምታድን ........ 62
ስለ አርሴማ ሰይጣን የሰጠው ምስክርነት ........ 62
የገነት ፍሬን እንዳፈራ ክብሯን ልናገር ........ 66
የመጽሐፍ ቅዱስ ምንባባት ያለ መልእክታቸው እንዲናገሩ ማስገደድ ........ 67
እንደ ማር ስለሚጣፍጥ አንብቡት ........ 68
ለዳንኤል አንበሶች ሰገዱለት ........ 69
ያልተጻፈ ማንበብ ........ 69
መጽሐፍ እንደ ተናገረ ........ 70
የእርስ በእርስ ተፋልሶ ........ 72
ሕግን የታመኑ የዘላለም ሕይወት ይወርሳሉ ........ 76
ማጠቃለያ ........ 77
ዋቢ ........ 78

# መቅድም

መጽሐፈ ሰዋስው ወግስ ወመዝገበ ቃላት ‹‹ገድል›› የሚለውን ቃል ‹‹ትግል፣ ፈተና፣ ውጊያ፣ ሰልፍ፣ ድልና አክሊል እስኪገኝ ድረስ የሚደክሙት ድካም፣ የሚሠሩት ሥራ፣ የሚቀበሉት መከራ›› በሚል ያስቀመጠው ሲሆን፤[1] ‹‹ሐዋርያት፣ ሰማዕታት፣ ጻድቃን ስለ ክርስቶስ ስም ስቃዩን ሳይሰቀቁ፣ ልዩ ልዩ መከራን ታግሦ በመጋደል መከራን መቀበል ገድል ይባላል›› የሚለው ከሣቴ ብርሃን ተሰማ ዐማርኛ መዝገበ ቃላት ደግሞ ‹‹ገድለ ቅዱሳን›› የሚለውን ሲተረጉም ‹‹ቅዱሳን፣ ሰማዕታት ስለ ክርስቶስ ሃይማኖት ከከሃድያን ነገሥታት አደባባይ የሚሰቃዩትን ልዩ ልዩ ስቃይን የሚነግር ገድል መጽሐፍ ይባላል›› ይላል።[2]

‹‹የገድል ዓይነቱ ብዙ ነው›› የሚለው መርሐ ጽድቅ ባህለ ሃይማኖት ከእነርሱም መካከል የሚከተለውን ያስነብባል ‹‹ሥጋን ለነፍስ ማስገዛትና ማድከም ነው። ‹እንስኬ ከመዝ እትጋደል ወእትባደር ወአጠውቃ ለነፍስየ ወአገርሮ ለሥጋየ› ይላል - 1ኛ ቆሮንቶስ 9፥27። እነዚህም ጾም፣ ጸሎት፣ ስግደት ሲሆኑ በራስ ፈቃድ የሚፈጸሙ ገድሎች ናቸው። ከእነዚህም ሌላ ፈጣሪያችሁን ካዱ ለጣዖት ስገዱ እያሉ የሚያስገድዱ ዓላውያን ነገሥታት እውነተኛውን ሃይማኖት የሚያስክዱ መናፍቃን ቢነሡ ፈጣሪያችንን አንክድም ለጣዖት አንሰግድም

---

[1] ኪዳነ ወልድ ክፍሌ (አለቃ) መጽሐፈ ሰዋስው ወመዝገበ ቃላት ዐዲስ (1948) ገጽ 301። ተስፋ ሚካኤል ታከለ (መምህር) (ተርጓሚ)፣ ገድለ አዳም (2002) ገጽ 2።

[2] ተሰማ ሀብተ ሚካኤል ግጽው፣ ከሣቴ ብርሃን ተሰማ ዐማርኛ መዝገበ ቃላት (2005 - ሦስተኛ ዕትም) ገጽ 1195። የኢትዮጵያ ቋንቋዎች ጥናትና ምርምር ማእከል፣ ኣማርኛ መዝገበ ቃላት (ዐዲስ አበባ፣ 1993) ገጽ 509።

የመናፍቃኑን ትምህርት አንከተልም በማለት ዐውቀው የሚቀበሉት ልዩ ልዩ ጸዋትወ መከራ ሁሉ ገድል ይባላል››፡፡[3]

እንዲህ ካለው የገድል ትርጉም ወጣ በማለት ‹‹ገድል መጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ አለን?›› የሚል ጥያቄ ይነሣል፡፡ ለጥያቄውም አዎን የሚል መልስ የሚሰጡ ሰዎች የሐዋርያት ሥራን ለምሳሌነት ያቀርባሉ፡፡[4] እሱንም መነሻ በማድረግ ወደ ቤተ ክርስቲያን በልዩ ልዩ ዘመናትና ምክንያቶች የገቡትን መጻሕፍት መጽሐፍ ቅዱሳዊ ለማድረግ ጥረት ይደረጋል፡፡

የሐዋርያት ሥራ (በእነርሱ ሐሳብ መሠረት ገድለ ሐዋርያት) እና አሁን ቤተ ክርስቲያን የከበቧት በርካታ ገድላት አንድ የማይሆኑበት ምክንቶች አሉ፡፡ የዚህ መጽሐፍ ዝግጅት ምክንያት እርሱ ባለ መሆኑ ወደዚያ መግባት አስፈላጊ ባይሆንም አንዱን ብቻ ለማሳያ ማቅረብ ተገቢ ነው፡፡ በዚህ መጽሐፍ የተፈተሸው ገድለ አርሴማም ሆነ ሌሎችን ገድላት ብንመለከት በገድሉ ላይ ታሪኩ የቀረበው ‹‹ቅዱስ›› ታላቅነት በስፋት ቀርቦ ይታያል፡፡ ይኼውም በእጆቹ ላይ ተደረጉ በሚባሉ ልዩ ልዩ ተአምራት ጎልቶ እንዲታይ የሚደረግ ይሆናል፡፡ በዚህም ውስጥ የክርስቶስ የማዳን ሥራ እና የእግዚአብሔር ክብር እንዲደበዝዝ ከዚያ ይልቅ ቅዱሱ ሁሉ በሁሉ ሆኖ እንዲታይ (ኀጢአተኛ ማጽደቅ፣ ወደ ሲኦል እንዲወርድ የተወሰነበትን ከፍርድ ውጪ ማዳን፣ ለልጅ ልጅ የሚተርፍ

[3] ትንሣኤ ዘጉባኤ ማተሚያ ቤት፣ መርሐ ጽድቅ ባህለ ሃይማኖት (ዐዲስ አበባ፣ 1988) ገጽ 121፡፡

[4] ተስፋ ሚካኤል ታከለ (መምህር) (ተርጓሚ)፣ ገድለ አዳም (2002) ገጽ 5፡፡ ዘበነ ለማ (መምህር) መጽሐፈ አሚን ወሥርዓት የሃይማኖትና የሥርዓት መጽሐፍ (ሚያዝያ 2009) ገጽ 121፡፡ ማኅበረ ቅዱሳን፣ ሐመረ ተዋሕዶ (ሚያዝያ 1999) ገጽ 67፡፡

ጽድቅ ማስጠት ወይም መስጠት…) የሚደረግ ሲሆን የክርስቶስ ስም ቢነሣ እንኳ ‹‹ቅዱሱን›› ከፍ ከፍ ከማድረግ ጋር በተያያዘ ነው (ክርስቶስ ተገለጠለት፣ እንዲህና እንዲያ ቃል ኪዳን ገባለት… ለማለት)፡፡

የሰው ሥራ ለሆኑት ገድላት ማሳያ እንዲሆን ተስፋ የተደረገው የሐዋርያት ሥራ ግን ከኢየሩሳሌም ጀምሮ እስከ ሮም ድረስ የወንጌሉ ሥራ እንዴት እንደ ተሠራ የሚያሳይ (በዚህ ምክንያት አንዳንዶች መጽሐፉን የሐዋርያት ሥራ ሳይሆን የመንፈስ ቅዱስ ሥራ (ግብረ መንፈስ ቅዱስ) ነው ሊባል የሚገባው ይላሉ) በመሆኑ እነ ‹‹ቅዱስ›› እንትናን ለማላቅ ከተዘጋጁት ገድላት ጋር ሊነጻጸር የሚችል መጽሐፍ አይደለም፡፡

ገድላት ላይ ለ‹‹ቅዱሱ›› በተገባለት ኪዳን አሁንም ድረስ (‹‹ቅዱሱ›› በዚህ ምድር በሕይወት ሳይኖር) ኀጢአተኛን ሲያጸድቅ ሐዋርያት ግን በስብከታቸውም በኑሮአቸውም ያስተላለፉት ‹‹በእርሱ የሚያምን ሁሉ በስሙ የኀጢአቱን ስርየት እንዲቀበል ነቢያት ሁሉ ይመሰክሩለታል›› ብቻ ነው (የሐዋርያት ሥራ 10፥43)፡፡ ታዲያ በምን መለኪያ ይሆን የሐዋርያት ሥራ አሁን አሁን እንደ አሸን ለፈሉት የሰው ሥራዎች ድጋፍ መሆን የሚችሉት?

# ይህ መጽሐፍ የተዘጋጀበት ምክንያት

አንድ ወዳጄን ሰላም ለማለት ቤቱ ሄድኩ፤ ከሰላምታችን በኋላ ‹‹እስኪ ቆይ አንድ ነገር ላሳይህ›› ብሎ በመሪ ራስ አማን በላይ የተጻፈና ‹‹መጽሐፈ ብሩክ›› የተሰኘ መጽሐፍ ከመጻሕፍት መደርደሪያው አውጥቶ እያሳየኝ ‹‹ይሄን መጽሐፍ አንብበከዋል?›› ሲል ጠየቀኝ። ምንም እንኳን መጽሐፉን ነጋዴዎች መሬት ላይ ዘርግተውት ብዙ ጊዜ ያየሁት ቢሆንም ‹‹የለም አልገዛሁትም አላነበብኩትምም›› አልኩት። በቆመበት መጽሐፉን ገለጥ ገለጥ አድርጎ ‹‹እስኪ ይህን ተመልከተው›› ብሎ ሰጠኝ።

እንዳነበው የሰጠኝ ቦታ በሰንጠረዥ የተዘጋጀ ቦታ ሲሆን በሦስት ዓይነት ቋንቋዎች የተጻፉ ስሞች አሉት (የመጀመሪያው ስሙ ቀጣይ ሁለቱ ደግሞ በሁለት ቋንቋዎች የተሠሩ ትርጉሞች ናቸው)። ስሞቹን አነበብኳቸው። ምን ሊያሳየኝ እንደ ፈለገ ግን አልገባኝምና ቀና ብዬ ዓይን ዓይኑን ሳየው ግር እንዳለኝ ገባውና አጠገቤ መጥቶ ገጾቹን ወደ ኋላ እየመለሰ ያስረዳኝ ጀመር። ገለጻውን ሲጨርስ ምንም ለማለት ስላልቻልኩ ዓይኔን መጽሐፉ ላይ እንደተከልኩ ቀርሁ።[5]

[5] በመጽሐፉ ላይ የሰፈረውና እንዲህ ትኩረቴን የያዘውን ሐሳብ በአጭሩ እንዲህ አስፍሬዋለሁ፤ በመጽሐፉ በገጽ 216 ላይ ‹‹ከሰው ልጆች ጋር ተቀላቅለው ምድራውያን የሆኑትን የረዓይቶችና የአፊሊሞን የኒኤፍሊምና የግያን ልጆች የነገዳቸውንና የአለቆቻቸውን ስም በሱባ ቋንቋ ከባቢሎን በኋላ በተወለደው በግእዝ ቋንቋ ዘርዝሬ የታወቁትን ብቻ እጽፋለሁ። አማርኛ ቋንቋችን ረጅም ዘመናት እንዳሉት መናፍስትን በራሱ ቃል መሰየሙ በቂ ምስክር ነው። ሆኖም የረዓይቶች ስም ለአንዳንድ ግለሰቦችም ይሁን ለአንዳንድ እምነት ተከታዮች እንደ ነውር ቢያዩት አንዳንዶችም እያወቁ እንደ ምስጢር ቢይዙት እኔ ግን ታሪክን ለማወቅ ለሚፈልጉና ለሚመራመሩ ጠቢባን ያውቁት ዘንድ አቅርቤአለሁ›› በማለት

‹‹ለምን የሆነ ነገር አንልም?›› የሚለው የወዳጄ ጥያቄ ትኩረቴን ወደ እርሱ ለመመለስ ምክንያት ባይሆነኝ ኖሮ ከዓመታት በፊት መርከብ ጋዜጣ ላይ ተጽፎ የነበረውና ‹‹ተሻላት ስንላት ባሰባት›› የሚለውን ርዕስ መነሻ አድርጌ ብዙ ነገር እያብሰለሰልኩ ነበር፡፡ ‹‹ምን ዓይነት ነገር ነው የምንለው?›› በሚል ጥያቄ ውይይቱን አሰፋሁትና አንድ ሥራ ለመሥራት ተስማምተን ተለያየን፡፡ ይህን ሐሳብ ይዘንም ብዙ ርቀት አብረን የተጓዝን ቢሆንም የሐሳቡ አመንጪው ወዳጄ በሥራ መደራረብ ምክንያት የመጽሐፍ ዝግጅቱን እኔ ብቻዬን እንድወጣው አደራ አለኝ፡፡

# ገድለ አርሴማ

በአርሴማ ስም የሚጠሩ ሁለት ገድላት አሉ፤ አንደኛው በአማርኛ ቋንቋ ተዘጋጅቶ በ1999 ዓመተ ምሕረት ለንባብ የበቃና አዘጋጁንም ሆነ የታተመበት ማተሚያ ቤት ያልተገለጸ ነው፡፡ ሁለተኛው መጽሐፍ በአማርኛ እና በግእዝ ቋንቋ የተዘጋጀ ሲሆን በውጭ ሽፋኑ ላይ መጋቢ አባ ኃይለ ማርያም

---

ከገጽ 217-220 የወንዶች መናፍስትን ስም ዝርዝር ከነትርጕማቸው አስቀምጠው ገጽ 221 ላይ ደግሞ ‹‹የሴቶች ስም ዝርዝር ከወንድ ጎሊና ላይ የሚያድሩ›› የሚል ርዕስ ከፍተው ሴቶቹን ሲያስቀምጡ በዐሥራ ዘጠነኛ ደረጃ ላይ አርሴማ የሚለውን ስም በሚከተለው መንገድ አስፍረውታል፤ በሲቫ ልሳነ ሰብ ‹‹ሰረቲን›› በግእዝ ‹‹አርሴማ›› በአማርኛ ‹‹ዘማሪት››፡፡ በዚህ ስፍራ ላይ ጸሐፊው አርሴማን (በርግጥ ቅዱሳን ከሚባሉት መካከል ሌሎችንም አንሥተዋል) ያነሷት ቅድስት ናት በማለት ሳይሆን የዛር ውላጅ በማድረግ ነው፡፡ ይህንንም በገጽ 214 እና 215 ላይ እንደሚከተለው አስፍረውታል ‹‹ጅኒ - ዛር ዘር ዘርአመናፍስት አንድ ዓይነት ትርጕም ነው፡፡… የጋይናን የሮሐንያ ልጆች የኒፊሊምም ልጆች ከሰው ልጆች ጋር ስለ ተቀላቀሉ ረጃጆሞችን ረዓይት ሲሉዋች አጫጭሮቹን ከሰው ልጅ ጋር የመሰሉት ጂኒ የዛር ውላጅ አሉአቸው››፡፡ ታዲያ ይህን እያየ አርሴማን ቅድስት ሴት ናት ለማለት ማን ይሞክር ይሆን - (አጽንዖት የግል)?

ስዩም የሚል ያስነብባል፡፡ በውስጥ ሽፋኑ ላይ ደግሞ መሪጌታ ጽጌ ዘርይሁን ከግእዝ ወደ አማርኛ የተረጎሙት እንደሆነና አስተርጓሚዎቹ ማኅበራነ ቅድስት አርሴማ እንዲሁም በ1995 ዓመተ ምሕረት በዐዲስ አበባ የታተመ መሆኑን አስፍሯል፡፡ በአማርኛ ቋንቋ ብቻ የታተመው መጽሐፍ በግእዝና በአማርኛ ከታተመው ላይ አማርኛው ለብቻው ተቀንሶ የታተመ መሆኑን የተርጓሚውና የአዘጋጁ መልእክት የሚለው በሁለቱም መጻሕፍት ውስጥ በመገኘቱ መረዳት ይቻላል፡፡[6]

ይህ መጽሐፍ ገድለ አርሴማ በሚል ስያሜ ወደ ቤተ ክርስቲያን ከቅርብ ዓመታት በፊት የተቀላቀለውን ይህን መጽሐፍ በመፈተሽ የቤተ ክርስቲያን አባቶችን ለምንድን ነው ዝም ያሉት? ለማለት የተዘጋጀ ነው፡፡ በጽሑፍ ዝግጅቱ ወቅት በተቻለ አቅም ከገድሉ ላይ ያሉትን ሐሳቦች በጥንቃቄ ለማስቀመጥ ጥረት ተደርጓል፡፡ ሐሳቡ ምን ያህል የተሳሳተ እንደ ሆነ ለማመልከትም የሚያሳይ ሐሳብ ተያይዞ ቀርቧል፡፡

የግርጌ ማስታወሻዎች በቊጥር ተለይተው ተቀምጠዋል፡፡ አልፎ አልፎ የግርጌ ማስታወሻዎች በጀመሩት ገጽ ሳያልቁ በመቅረታቸው ወደ ቀጣዩ ገጽ ዞረው ይገኛሉ፡፡ እንዲሁ ደግሞ የግርጌ ማስታወሻ ቊጥሩ በቀዳማዊ ገጽ ሆኖ ሐሳቡን የያዘው ቊጥር በተከታዩ ገጽ ያጋጥማል፡፡

አንብበው የሚጠቀሙበት እንዲሆን ጸሎቴ ነው!

[6] እንደ ምንጭ የተጠቀምነው ሁለቱንም የገድል መጻሕፍት ቢሆንም በዋቢ ስር የጠቀስነው በግእዝና በአማርኛ የተዘጋጀውን ገድለ አርሴማ ነው፡፡

# አርሴማ ማን ናት?[7]

[7] በገድለ አርሴማ መጽሐፍ ውስጥ በዐሥራ ሁለት ምዕራፎች የተደራጁ ተኣምራትና በልዩ ልዩ አርዕስት (በአርዕስት የተከፋፈለው በአማርኛ ብቻ የታተመው ገድለ አርሴማ ነው) መልክአ አርሴማ አብረው አሉ። በተአምራት ክፍሎች ከተጻፉት ውስጥ ስለ አርሴማ ቅድስና የሚናገር አንድ ክፍል እንዲህ ይነበባል፤ ‹‹በግብፅ ከተማ በእስክንድርያ ስሙ አንስጣስዮስ የሚባል ቴዎደስዮስ የሚሉት አንድ ንጉሥ ነበር። የጽጽስና ስሙም ይህን ዓለም የናቀና የእግዚአብሔርን መንገድ የተከተለ ብፁዓዊ ሙሴ ነው። ይህቺውም የምንኩስና ሕግ ናት። እርሱ የቅዱሳን ሰማዕታትንና የጻድቃን አጥንቶች ይሰበስብ፣ የገድላቸውን ዜና ይጽፍ፣ ቤታቸውን ይሠራ፣ ታቦቶቻቸውንም ያገባ፣ በየበዓላቸውም ይቀድስ፣ ሁልጊዜም ታቦቶቻቸውን ይጎበኝ ነበር። ከዕለታት በአንድ ቀንም ታቦትን ለማሰናዳት ሜሮን ለመቀባት ወደ ቤተ መቅደስ በገባ ጊዜ ሲዳስስ በወርቅ የተለበጠና በላዩ በሮማይስጥና በጽርዕ ቋንቋ የብፅዕት ቅድስት አርሴማ ስም የተጻፈበት አንድ ጽላት አገኘ። ያን ጊዜም የቅዱሳንን ስማቸውን አሰበ። የገድላቸውንም ዜና መረመረ። የብፅዕት ቅድስት አርሴማን የሞትዋን ዜና አላገኘም። ስለዚህም ነገር በምን ዘመን ሰማዕት እንደ ሆነች የብፅዕት ቅድስት አርሴማን ሥራ ያስረዳው ዘንድ ወደ እግዚአብሔር ለመነ፣ ማለደ። ያን ጊዜም የእግዚአብሔር መልአክ ተገለጠለት። እንዲህም አለው፤ ብፁዓዊ ሙሴ ሆይ የብፅዕት ቅድስት አርሴማን ሥራ እነግርህ ዘንድ ስማ። ይህቺ ሴት ዛሬ አልተፀነሰችም፤ ገና አልተወለደችም። በወርቅ ዓምድ በሕይወት መጽሐፍ ስሟ ተጽፏል እንጂ፤ ነቢዩ በመጽሐፍ ውስጥ ሁሉ ይጻፋል እንዳለው። እርስዋም በኋለኛው ዘመን ሰማዕት ትሆናለች። በዓለም ዳርቻ ሁሉ የገድልዋ ዜና ይታወቃል። የሚበዛውም በነጻ አውጭ አገር (በኢትዮጵያ) ነው። ከዚህ ጊዜ ጀምሮ የብፅዕት ቅድስት አርሴማን የስም መታሰቢያ መጥራት አትተው። ጽላትዋም ከአንተ ጋር ይኑር። የመቅደስም ሕንፃ በሕንፃ ቦታህ ጎን ይኑር። ስምህ በተጠራበትም የስሟ መታሰቢያ ይጠራ። ይህንም ብሎ ያ መልአክ ተሠወረ፤ ወደላከውም ተመለሰ። እርሱም የእግዚአብሔር መልአክ እንዳዘዘው አደረገ›› (ተኣምረ አርሴማ ምዕራፍ ሰባት - አጽንዖት የግል)።

እንደዚህ የታሪክ አቀራረብ ከሆነ ገና ሳትወለድ ብቻም ሳይሆን ሳትፀንስ በስሟ ታቦት ተቀርጾ ተዘጋጅቶ ነበር። ከታቦቱም በላይ ደግሞ ገና ሳትፀነስ ገናም ሳትወለድ ስሟ በሕይወት መጽሐፍ ተጽፏል። ይህ ማለት ደግሞ በገድል መጽሐፉ ‹‹በደሚ ወርቅም መንግሥተ ሰማያትን

# የትውልድ አገሯ ሮም[8] የሆነችው አርሴማ የ15 ዓመት ታዳጊ ሳለች ዲዮቅልጥያኖስ የተሰኘው ዓላዊ ንጉሥ ስለ ወደዳት

---

ተወዳጆች›› ተብሎ የተጻፈው ስሕተት ነው ማለት ነው (መቅድም ቊጥር 13 ይመልከቱ)፡፡ ከዚህም ሌላ ገና ሳትወለድ የገድሏ ዜና በዓለም ዳርቻ የሚታወቅ ይሆናል ተብሎ ትንቢት ተነግሮላታል፡፡ ከዚህም የሚበዛው እንደ ተኣምሩ አጻጻፍ በነጻ አውጪ አገር ብሎ በቅንፍ ኢትዮጵያን በማስቀመጥ በአገራችን እንደ ሆነ ያሳያል፡፡ ኢትዮጵያን ነጻ አውጪ ብሎ ሲያስቀምጥ ማንን፣ ከምን ነጻ እንደምታወጣ ግን የጠቈመው ነገር የለም፡፡ የአርሴማ የገድሏ ዜና የሚበዛው በኢትዮጵያ ለምን እንደሚታወቅም ያስቀመጠው ፍንጭ የለም፡፡

ገድለ አባ ጊዮርጊስ ላይ ‹‹አባ ጊዮርጊስ በማኅፀን የተመረጡና ሀብተ መንፈስ ቅዱስ ያደረባቸው ናቸውና…›› የሚለውንና መሰል ታሪኮችን የሚያወቀው የገድለ አርሴማ ጸሐፊ አርሴማን ከሌሎች ‹‹ቅዱሳን›› ላቅ ያለች ለማድረግ ሳትፀነስ በሕይወት መጽሐፍ ተጽፋለች ይላል፡፡ ይህ ደግሞ የገድላት ጸሐፍት ምን ያህል ፉክክር ውስጥ እንዳሉ ያሳያል (የደብረ ባሕርይ ጋሥጫ አባ ጊዮርጊስና አቡነ በጸሎተ ሚካኤል አንድነት ገዳም፣ ገድለ አባ ጊዮርጊስ ዘጋሥጫ እና ገድለ አቡነ በጸሎተ ሚካኤል ግእዝና አማርኛ (2004) ገጽ 10)፡፡

8 በገድሉ ትረካ መሠረት እናትና አባቷ በሮም ይኖሩ የነበሩ ይመስላል፡፡ እርሷም ምክንያቱ ግልጽ ባልሆነ ምክንያት ከትዳር ውጪ ከሆነች በኋላ በሮሜ በሚገኝ አንድ የደናግላን ገዳም ውስጥ ገብታ እንደ ነበር ይነግረናል፡፡ ምናልባትም ይህን መሠረት በማድረግ አንዳንድ ወንድሞችም የትውልድ አገሯ ሮሜ ነው በሚለው ይስማማሉ (ታፈሰ ለማ (ዲያቆን) በደም የታተመ ክርስትና (መጋቢት 2009) ገጽ 37)፡፡ ነገር ግን ገድሉ መልሶ ‹‹አርሴማ የምትኗት ገሊላዊት ሴት…›› በማለት ከሮሜ ወደ ገሊላ ይወስዳታል (የግንቦት ገድለ አርሴማ ቊጥር 43)፡፡ በገድሉ ላይ በሰፈረው ታሪክ መሠረት ይህን የተናገሩት አጋንንት ቢሆኑም የገድሉ ጸሐፊም ሆነ የትርጒም ሥራውን የሠሩት ሰዎች ያቀረቡት ማስተባበያ የለም፡፡ ምናልባት ይህን ያላደረጉት (አጋንንት ሐሰተኛ በመሆናቸው ገሊላዊት ያሏት ስሕተት ነው የሚለውን ለማስተባበል ያልደፈሩት) ከዚሁ ታሪክ ጋር በተያያዘ በነበልባሏ እንደተቃጠሉ… የቀኝ ጣቷ አጋንንቱን በእርሷ ፊት እንዳይቆሙ እንደሚከለክል ድል የምታደርጋቸው ዛሬ ብቻ ሳይሆን ከሞተችም በኋላ በገድሎቿ መጽሐፍና (ከአንድ በላይ የገድል መጽሐፍ ያለ ይመስላል) በራስዋ ስም መታሰቢያ በኋለኛው ዘመን ድል እንደምታደርጋቸው የሰፈረውንም አብሮ ማስተባበል ስለሚሆንባቸው

ሚስቱ ሊያደርጋት ቢሞክር በዙሪያዋ በነበሩ ሰዎች ምክር ሸሽታ ወደ አርመንያ ትገባለች። ነገር ግን የመልኳን ማማር የተመለከተው የአርመንያ የጦር አዛዥ በተመሳሳይ ሁኔታ ሚስቱ ሊያደርጋት ቢጠይቅ መልሷ አይሆንም የሚል በመሆኑ ወደ አርመንያ ንጉሥ ይዟት ይሄዳል። ንጉሡም በተመሳሳይ ሁኔታ ላግባሽ የሚል ጥያቄ ያቀርባል። እርሷም እንደተለመደው አይሆንም የሚል መልስ ብትሰጠው እርሱ ግን በተለያየ መልኩ በማግባባትና በማስፈራራት እሷን ሚስቱ ለማድረግ የሞከረው ሙከራ ስላልተሳካ እንድትሞት ይፈርድባታል።

በእርሷ ምክር እየተበረታቱ በጽናት አብረዋት ወደ ሰማዕትነት ይጓዙ የነበሩት ሃያ ሰባቱ ሰማዕታት[9] በንጉሡም ሆነ በጦር አዛዡ ፊት ስለ ሃይማኖታቸው ሰማዕት ለመሆኑ የቆረጡ መሆናቸውን በመመስከር[10] የተለያዩ ውጣ ውረዶችን ያልፉና ሰማዕትነትን ይቀበላሉ። አርሴማም ከሃያ ሰባቱ ሰማዕታት በኋላ አንገቷ ተቀልቶ ሰማዕት ትሆናለች። በግእዝና በአማርኛው እትም ገድለ አርሴማ መሠረት 202 ገጽ የሚፈጀው ታሪክ በአጭሩ ይህን ይመስላል። ከዚህ በታች ከገድሉ ላይ ማሳያ የሚሆኑ ክፍሎችን በማንሣት ገድሉ ከመጽሐፍ ቅዱስ እውነትና ከቤተ ክርስቲያን ትምህርት

---

ይሆን? ስለዚህ አርሴማ የየት አገር ተወላጅ ነች? ገሊላዊት ናት ወይስ ሮማዊት?

[9] ወደ ሃያ ሰባቱ ሰማዕታት በኋላ የተቀላቀለች ቢሆንም ገድሉ ወዲያውኑ የመሪነቱን ስፍራ ለእርሷ ሲሰጣት ይታያል።

[10] ስለ ክርስቶስና የማዳን ሥራው ምስክርነት ሊሰጡ የሚችሉበት የተለያየ እድል አግኝተው የነበረ ቢሆንም እድላቸውን ሳይጠቀሙ መቅረታቸው ‹‹እውነትን ለመመስከር ፍላጎት የላትም›› በሚል ርዕስ የቀረበውን ጽሑፍ ይመልከቱ።

እንዲሁም ከራሱ ጋር ያለውን አለመስማማት ለማሳየት ጥረት ተደርጓል፡፡

## ትውልዷ

ገድሉ ላይ እንደሰፈረው ‹‹... ክቡራን ከሆኑ ካህናት፣ ሌዋውያንና ከነያላን ነገሥታት ወገን የሆነ ስሙ ቴዎድሮስ የሚባል አንድ ሰው ነበር፡፡ ከቤተ ክርስቲያን ሹሞች ካህናትና ሃይማኖታቸው የቀና ከሆኑ ከጳጳሳት አለቆች ወገን ስሟ ቡርክት አትኖስያና[11] የምትባል ክብርት የሆነች ሴትን አገባ››፡፡ እነርሱም እግዚአብሔርን የሚፈሩ፣ በጾም በጸሎት፣ በልመናና በስግደት፣ በትጋት የጸኑ ጻድቃን ሰዎች ቢሆኑም ልጅ መውለድ ግን አልቻሉም ነበር፡፡

እስከ እርጅና ድረስ የደረሰው ልጅ ያለማግኘታቸው ችግር አትኖስያናን እንድታዝን፣ እንድታለቅስና ብዙ ኀዘን እንዲሰማት ያደረገ በመሆኑ በትጋት ትጸልይ ነበር፡፡ ምንም እንኳ እርሷ ‹‹በብዙ ልቅሶና ኀዘን በትጋት፣ በትሕትና፣ ለችግረኞችና ለጦም አዳሪዎች በመመጽወት›› ብትጸልይም እግዚአብሔር ‹‹ስሙ ልድዮስ የሚባለውን የቂሣርያ ሊቀ ጳጳሳት ወንድሟን እንዲጸልይላት አዘዘው፡፡[12] እርሱም ስለ እርስዋ ጸለየ፡፡

[11] ስንክሳር በመስከረም 29 ንባቡ ላይ የእናትዋን ስም አጋታ በማለት አስቀምጦታል፡፡ ስንክሳርም ብቻ ሳይሆን ራሱ ገድሉም የእናቷ ስም ዐጋታ መሆኑን ፍንጭ ይሰጣል (የመስከረም ገድለ አርሴማ ቊጥር 23)፡፡ ሌሎችም ይህን ሐሳብ ደግመው አስፍረውት ይታያል (ኃይለ ማርያም ሽመልስ ካሣ፣ ሥዕለ ቅድስት አርሴማ (2008) ገጽ 19)፡፡ ሌሎቹን ትተን ገድሉ አንድ ቦታ ላይ ‹‹አትኖስያ›› ሲላት ሌላ ቦታ ደግሞ ‹‹ዐጋታ›› የሚል ያሰፈረው የአርሴማ እናት ስም የትኛው እንደ ሆነ ለማወቅ ተስኖት ይሆን እንዴ?

[12] ምንም እንኳ በገድሉ ላይ ‹‹እግዚአብሔር የልቧን ብርታት›› እንደተመለከተ የሰፈረ ነገር ቢኖርም የእርሷን ጸሎት ተቀብሎ መልስ

በመልካም ጠባይዋ እጅግ ይወዳታልና ስለዚህም እግዚአብሔር የጳጳሳቱን አለቃ ጸሎትና የቡርክት አትኖስያና ልቅሶን ሰማ››፡፡

በብዙ ጸሎትና ልቅሶ ጥር ስድስት ቀን[13] የተወለደችውን አርሴማን እስከ ሦስት ዓመት ድረስ ካሳደገቻት በኂላ በማርያም ስም ለተሠራ ቤተ ክርስቲያን ታገለግል ዘንድ ሰጠቻት፡፡[14]

---

ከመስጠት ይልቅ ሌላ ሰው እንዲጸልይላት ማዘዙ ምክንያቱ ግልጽ አይደለም፡፡ ምናልባት እርሷ በደለኛ ስለ ሆነች ነው እንዳይባል ቀደም ሲል እርሷም ሆነች ባለቤቷ ቴዎድሮስ ‹‹ጻድቃን›› መሆናቸው ሰፍሯል፡፡ ልድዮስ ከእነርሱ ይልቅ ጻድቅ መሆኑ እንኳ (ምናልባት ሆኖ ቢሆን) የተገለጸ ነገር የሌለ በመሆኑ ልድዮስ እርሷ የጸለየችውን ጸሎት ይደግም ዘንድ ለምን አስፈለገ?

13 ብርሃን ብስራት (መልአከ ብርሃን)፣ ገዳማዊ ሕይወት እና ጌቴሴማኒ (መጋቢት 2004) ገጽ 48፡፡

14 እንዲህ ያለው ታሪክ የአዋልድ መጻሕፍት ባሕርይ እስከሚመስል ድረስ በሌሎች መጻሕፍትም ውስጥ ይታያል፡፡ ለማሳያ ቢሆነን ከዚህ በታች የቀረቡትን መጻሕፍት መመልከቱ መልካም ነው፤ በቅድሚያ ድርሳነ ኢያቄም ወሐና እና ተኣምረ ማርያም፤ የሐና ወላጆች ‹‹ሌዋውያን ካህናት›› ሲሆኑ ባለቤቷ ደግሞ ከነገደ ይሁዳ ነበር፡፡ ይህንንም ተኣምረ ማርያም ‹‹የእመቤታችን ትውልዷ ባባቷ በኩል ከንጉሥ ዳዊት ወገን ነው፤ በናቷም በኩል ከሊቀ ካህናቱ ከአሮን ወገን ነው›› በሚል አስቀምጦታል፡፡ ሐና መካን በመሆኗ ልጅ አልነበራትምና ‹‹ዘር የሌለሽ ዘሩንም ያጠፋሽ መካን›› ይሏት ስለ ነበር በብርቱ ጸሎት ኢያቄምና ሐና እግዚአብሔርን በመጠየቃቸው ‹‹በነጭ ወፍ አምሳል በሐና የተቀመጠችው[ን]›› ማርያምን ሰጣቸው፡፡ በኂላም የማርያም ‹‹ሦስት ዓመት በተፈጸመ ጊዜ›› ሐና ለኢያቄም ‹‹ቤተ እግዚአብሔርን ልታገለግል ነው እንጂ በዚህ ዓለም እኛን ልታገለግል እንዳልተሳልን አስብ›› የሚል ሐሳብ ስለ ሰጠችው ለቤተ መቅደስ ሰጧት›› (ተስፋ ሚካኤል ታከለ (ተርጓሚ) ድርሳነ ኢያቄም ወሐና - በግእዝ እና በአማርኛ (ዐዲስ አበባ፣ 2007) ዘሰኑይ፡፡ ትንሣኤ ዘጉባኤ ማተሚያ ቤት፣ ተኣምረ ማርያም - ግእዝና አማርኛ (ዐዲስ አበባ፣ 1989) የዘወትር መቅድም ቊጥር 15፤ ተኣምር 2)፡፡ ማርያም በተወለደችበት ዘመን እና ማኅበረሰብ ውስጥ ሴት ልጅ ቤተ መቅደስ ውስጥ ምን ዓይነት የአገልግሎት መስክ እንደ ነበራት ተኣምረ ማርያምም ሆነ ድርሳነ ኢያቄም ወሐና ምንም ያሰፈሩት ነገር

‹‹ከዐሥራ ሁለት ዓመትም በኋላ አባትና እናትዋ ከካህናት ወገን የሆነ መልካም ጎልማሳን ያጋቡአት ዘንድ ወደዱ››፡፡[15]

## ትምህርቷ

‹‹... ለብጽዕት ቅድስት አርሴማ ያለ ልክና ያለ አቅም የዕውቀትንና የጥበብን፣ የጸጋንና የረድኤትን መንፈስ ...››[16] እግዚአብሔር አምላክ ሰጣት የሚለው ገድል፥ በሦስት ዓመቷ ለቤተ ክርስቲያን እንደ ተሰጠችና ከዐሥራ ሁለት ዓመት በኋላ

---

የለም፡፡ ነገር ግን ሴት ልጅ በቤተ መቅደሱ ውስጥ የአገልግሎት ድርሻ እንዳላት መጽሐፍ ቅዱስ ፍንጭ አይሰጥም፡፡

‹‹የአቡነ ገብረ መንፈስ ቅዱስ አባቱና እናቱ ከደጋግ ከምእመናን ሰዎች ወገን ነው፤ የአባቱም ስም ስምዖን ይባላል ከነገደ ብንያም ነው፤ የእናቱም ስም አቅሌስያ ትባላለች ወላጆቹም በእግዚአብሔር ፊት ደጋጎች ነበሩ አቅሌስያ መካን ሆና ልጅ አጥታ ልጅ ባለማግኘቷ እያለቀሰች ሠላሳ ዘመን ኖረች›› የሚለው ገድለ ገብረ መንፈስ ቅዱስ አቅሌስያ ወደ ቤተ ክርስቲያን ገብታ ከሥዕል ፊት ቆማ ስትጸልይ ሥዕሉ አፍ አውጥቶ ‹‹ሥልጣኑ ከሰማይ ከፍታ ከፍ የሚል ንጽሕናው ከሚካኤልና ከገብርኤል የሚተካከል ክህነቱ እንደ መልከ ጼዴቅ እንደ መጥምቁ ዮሐንስ እንደ ነቢይ ኤልያስ የሆነ ልጅ እንቺ ተቀበይ›› ይላታል፡፡ እንደተባለችውም በመጋቢት 29 ቀን የጸነሰችውን ልጅ በታኅሣሥ 29 ቀን ወለደችና ከሦስት ዓመት በኋላ እግዚአብሔር መልአኩ ገብርኤልን ልኮ ሕጻኑን ከእናቱ እጅ ተቀብሎ ገዳማውያን ወዳሉበት ገዳም ወስዶ በር ላይ እንዲያስቀምጠው ባዘዘው መሠረት መልአኩ አባ ዘመደ ብርሃን የተባሉ አባት ባሉበት ገዳም በር ላይ አስቀመጠው (ትንሣኤ ዘጉባኤ ማተሚያ ቤት፣ ገድለ ገብረ መንፈስ ቅዱስና ተኣምረ ገብረ መንፈስ ቅዱስ - በግእዝና በአማርኛ (ዐዲስ አበባ፣ 1994) ምዕራፍ ሁለት)፡፡ የእነዚህ መጻሕፍት ተመሳሳይ የታሪክ አቀራረብ አንድ ሰው የተመረጠ የእግዚአብሔር አገልጋይ (እንደ አርሴማ ሰማዕት አልያም እንደ ገብረ መንፈስ ቅዱስ በጸሎት ተጋድሎ የሚኖር) ለመሆን ወላጆቹ የተመረጡ ሰዎች ሆነው መካን መሆን ያለባቸውና በብዙ ጸሎት ሊወለድ የሚገባው ከተወለደም በኋላ በሦስት ዓመቱ ለቤተ ክርስቲያን አልያም ለገዳም መሰጠት ያለበት ይመስላል፡፡

[15] የኅዳር ገድለ አርሴማ ቍጥር 6-16፡፡

[16] የታኅሣሥ ገድለ አርሴማ ቍጥር 75፡፡

(በዐሥራ አምስት ዓመቷ ማለት ነው) ሊድሯት ሠርግ ተሰርጎ[17] እንደ ነበር ካሰፈረው ውጪ ስለ ተማረችው መንፈሳዊ ትምህርት ምንም የሚያስነብበው ነገር የለም። ከዚህ ይልቅ ‹‹የሮምያን፣ የጽርዕን፣ የሶርያንና የኪልቅያን መጻሕፍት ተምራ ልብ አድርጋለች››[18] ይላል።[19]

## ውበቷ

የገድሉ ታሪክ ማዕከል ስለ ክርስቶስ የሚከፈል መሥዋዕትነትን የሚያሳይ ሳይሆን የአርሴማ ውበት የንጉሡንና በዙሪያዋ ያሉ ሰዎችን ትኩረት መያዙንና ውበቷን መሠረት አድርጎ የሚናገሩትና የሚያሳዩት ሁኔታ በስፋት የተተነተነበት መጽሐፍ ነው። ማሳያ ቢሆን አንድ ሁለት ነጥቦችን ከዚህ በታች ለማስፈር ተሞክሯል፤

## ውበቷን ያዩ ሰዎች ልብ ታወከ

የኢትዮጵያ ቋንቋዎች ጥናትና ምርምር ማዕከል ያሳተመው መዝገበ ቃላት ውበት የሚለውን ቃል ‹‹የመልክ፣ የድምጽ፣ የቅርጽ፣ የአቋቋም፣… ቁንጅና፣ ማማር፣ የመሳብ ኃይል፣ ለዛ››

---

[17] በገድሉ ላይ ‹‹ከዐሥራ ሁለት ዓመትም በኋላ አባትና እናትዋ ከካህናት ወገን የሆነ መልካም ጎልማሳን ያጋቡአት ዘንድ ወደዱ። ይህቺ ቅድስት አርሴማ ግን ይህን አልወደደችም ነበር። ነገር ግን እንደ ሕጋቸው ሠርግ አድርገው በእርሷ ሠርግ ቀን ታላቅ ደስታን ተደሰቱ›› ከማለት ያለፈ ስለ ትዳሯ ምንም ነገር ሳያሰፍር (ማለትም ጋብቻው ሳይፈጸም ቀርቶም ይሁን ወይም ከጋብቻ በኋላ ፍቺ ተከናውኖ ወይም ከካህናት ወገን ነው የተባለው መልካም ጎልማሳ በሞት ተለይቷት) ወደ ደናግላን ገዳም ገባች ይላል (የኅዳር ገድለ አርሴማ ቍጥር 16-19)።

[18] ይህን ትምህርት የተማረችው ከሦስት ዓመቷ እስከ ዐሥራ ሁለት ዓመቷ በቤተ ክርስቲያን በነበረች ጊዜ ይሁን ወይም ለጋብቻ ወጥታ ወደ ደናግላን ገዳም ከገባች በኋላ ግልጽ አይደለም።

[19] የመጋቢት ገድለ አርሴማ ቍጥር 14።

በሚል አስቀምጦታል፡፡[20] በገድለ አርሴማ ላይ ግን የውበት መገለጫ ከዚህ የተለየ ሆኖ ይታያል፤

- ‹‹<u>መልኳ</u> ያማረ፤ <u>የምታስፈራ</u> ያችን ልጅ ሰጣት፡፡ ይህችውም ቅድስት አርሴማ ናት››፡፡[21] ቀደም ሲል ያማረ ያለውን መልክ መልሶ የምታስፈራ በሚል አስቀምጦታል፡፡
- ‹‹የብፅዕት ቅድስት አርሴማን <u>የውበቷን ደም ግባትና የፊቷን መልክ በአዩ ጊዜ</u> ሰዎች ከብፅዕትና ከቡርክት ቅድስት አርሴማ የግርማ ልዕልና የተነሣ <u>የሰዎች ሁሉ ልብ ታወከ</u>››፡፡[22] የሰዎቹ ልብ ደስ በመሰኘት ፈንታ የታወከው የውበቷን ደም ግባትና የፊቷን መልክ በተመለከቱ ጊዜ መሆኑን ልብ ማለቱ ተገቢ ነው፡፡
- ‹‹<u>የፊቷን፣ የመልክ ውበት በአየንም ጊዜ ደነገጥን፣ ፈራንም</u>፡፡ በአደባባይም ያየት ሁሉ <u>ፈጽሞ ከሚያስፈራውና ከሚያስደነግጠው</u> የግርማዋ ከፍታ የተነሣ አደነቁ፡፡ ከሰማይ በታችና ከምድር በላይ የፊቷን ውበትና የመልኳን ቀለም በዚያ አገር ውስጥ የሚመስላት የለምና››፡፡[23] ሰዎቹ ራሳቸው እንደተናገሩት የፊቷን የመልክ ውበት ሲመለከቱ ደነገጡ ደግሞም ፈሩ፡፡ እነርሱም ብቻ ሳይሆኑ በአደባባይ የተመለከቷት ሁሉ ተመሳሳይ ስሜት የተሰማቸው መሆኑን ፍንጭ ይሰጣል፡፡
- ‹‹… ቡርክት ቅድስት አርሴማን ወደ ንጉሥ ይወስዱአት ዘንድ፤ የንጉሥ መልእክተኞች መጡ፡፡ <u>በአዩአት ጊዜም</u>

[20] የኢትዮጵያ ቋንቋዎች ጥናት ምርምር ማዕከል፣ ዐማርኛ መዝገበ ቃላት (1993) ገጽ 424፡፡ ባህሩ ዘርጋው ግዛው፣ ዘርጋው ከፍተኛ የዐማርኛ መዝገበ ቃላት (መጋቢት 2006 - ሁለተኛ ዕትም) ገጽ 736፡፡

[21] የኅዳር ገድለ አርሴማ ቍጥር 15 — አጽንዖት የግል፡፡

[22] የታኅሣሥ ገድለ አርሴማ ቍጥር 76 — አጽንዖት የግል፡፡

[23] የመጋቢት ገድለ አርሴማ ቍጥር 9 — አጽንዖት የግል፡፡

ተንቀጠቀጡ፡፡ እንደ ቅጠልም ረገፉ፡፡ እርስዋ ግን በጸሎቷ ኀይል አነሣቻቸው...››፡፡[24] እነዚህ ሰዎች የመጡት ንጉሡ ልኳቸው ሲሆን ሲመለከቷት ግን ተንቀጠቀጡ፡፡ ከዚህም በላይ እንደ ቅጠል ረገፉ፡፡

እነዚህን ያነበቡ የገድሉ አንባቢያን የአርሴማ ውበት ምን ዓይነት እንደ ሆነ እነርሱም በዓይናቸው ለመመልከት እንደሚጓጉ ጥርጥር አይኖርም፡፡ በርግጥስ መልኳ ምን ዓይነት ይሆን? የሚል ጥያቄ ቢኖርዎ ገድሏ በሚከተለው መልኩ መልስ ይሰጥዎታል፤

ከንፈሮችዋ እንደ ሮማን አበባ፣ የልብሶቿም መዓዛ እንደ ነጭ ዕጣን መዓዛ፣ ዓይኖቿ እንደ ኮከብ መውጣትና እንደ ንጋት ጎሕ፣ ቅንድቦችዋም እንደ መላ የውሃ ምንጭ፣ ጉንጮቿ የናርዱስን መዓዛ የተመሉ፣ ዘይት የተጨመረበት የሐር ብርሌ ይመስላል፡፡ ክፍክፍዋም እንደ ጥቊር አሞራ የጠቈረ፣ እጆችዋም የፀሐይ እግሮች በመስኮት እንዳሉበት ብርሌ፣ ጣቶችዋም በመቊረጫ ሽልማት የለዘቡ፣ ጥርሶችዋም እንደ ወርቅና ሉል፣ እንደ በረዶና ወተት የነጹ ከወይን ይልቅ የሚያምረው የአፍዋ መዓዛም እንደ እጣን የሚሸት ነውና፡፡[25]

በዚህ ስፍራ ላይ የተቀመጠው ውበት በእርግጥም የአርሴማ ውበት ከሆነ በመዝገበ ቃላቱ ላይ እንደሰፈረው የመሳብ ኀይል ያለውና ተመልካቹን ሁሉ ደስ የሚያሰኝ እንጂ የሚያውክ፣

[24] የሰኔ ገድለ አርሴማ ቊጥር 22 - አጽንዖት የግል፡፡
[25] የሐምሌ ገድለ አርሴማ ቊጥር 32፡፡

የሚያስፈራ፣ የሚያስደነግጥና ተንቀጥቅጦ እንደ ቅጠል የሚያረግፍ አይደለም። ከላይ የሰፈሩት እና አርሴማን ሲመለከቱ ደስ በመሰኘት ፈንታ ተንቀጥቅጠው የወደቁትም ሆነ ልባቸው የታወከባቸው ሰዎች የመሳብ ኃይል ያላትንና ውብ የሆነችን ይህቺን ሴት ሳይሆን ሌላ መንፈስ ያዩ ሳይሆኑ አይቀሩም።

## ከውበቷ የተነሣ መብራት ወይም ብርሃን አያስፈልጋትም

እግዚአብሔር ሁሉን መልካም አድርጎ የፈጠረ ቢሆንም በሰው ዓይን ሲታይ ግን አንዱ ከሌላው በተለየ ሁኔታ ዓይነ ገብ የሆነ መልከ መልካም ይሆናል። ነገር ግን ምንም ቢያምር ያንኑ የተፈጥሮውን የአዳምን ልጅ ባሕርይ ተከትሎ ነው እንጂ የተለየ ነገር አይኖረውም።

የገድሉ ጸሐፊ ግን፤

> [ንጉሡ] ተነሣና ቅድስት አርሴማ ስለሚሉአት ስለዚህች የምትደነቅና የምትፈራ ሴት፣ እኔ ፈጽሜ አደንቃለሁ አለ። እርስዋን የሚመስል በምድር ሁሉ አላገኘሁምና። ከአባታችን አዳምና ከእናታችን ሔዋን ልጆች በሰማይ በታች፣ ወይም በምድር ላይ፤ ሥራዋ የሚያስደንቅ፤ የመልኳም ውበት ዕፁብ ነውና። በፀሐይ ላይ ያለ የብርሌን መልክ ትመስላለች። ብርሃንን ወይም መብራትን ምንም አትፈልግም። የሥጋዋ ንጽሕና ነጭና የጠሩ ከሆኑ፤ ሁለመናዋ የበራ ነውና አለ

ይላል፡፡[26]

የገድሉ ጸሐፊ ይህን ሲያሰፍር፤ አርሴማን ከፍ ከፍ ለማድረግ በማሰብ መሆኑ ግልጽ ነው፡፡ ነገር ግን በዘመኑ ከነበሩ ሰዎች ብቻ ሳይሆን ከአዳምና ከሔዋን ልጆች ይልቅ የተዋበችና በሥራዋም የምትደነቅ ናት ከማለት አልፎ ከተፈጥሮ ውጭ በሆነ ሁኔታ ‹‹በፀሐይ ላይ ያለ የብርሌን መልክ ትመስላለች›› ብሎ ታላቅ የሆነ የአድናቆትን ሐሳብ ካሰፈረ በኋላ ‹‹ብርሃንን ወይም መብራትን ምንም አትፈልግም›› በማለት ውበቷ ብርሃኗ እንደ ሆነ አስመስሎ አስፍሯል፡፡ ሰው ምን ቢያምር ምን ቢዋብ ውጫዊ ብርሃን (የተፈጥሮም ሆነ ሰው ሠራሽ ብርሃን) የሚፈልግ መሆኑ ግልጽ ነው፡፡

ፀሐይ ወይም ጨረቃ ሳያስፈልጉት በራሱ ብርሃን ይሆናል ተብሎ የተጻፈለት ጌታችን መሆኑን ራእየ ዮሐንስ ‹‹ለከተማይቱም የእግዚአብሔር ክብር ስለሚያበራላት መብራትዋም በጉ ስለ ሆነ፥ ፀሐይ ወይም ጨረቃ እንዲያበሩላት አያስፈልጓትም ነበር›› በሚል ያስቀመጠውን በመመልከት መረዳት ይቻላል (ራእይ 21፥23)፡፡ የገድለ አርሴማ ጸሐፊ በተመሳሳይ መልኩ ምንም ዓይነት ውጫዊ ብርሃን ሳያስፈልጋት በራሷ ብርሃን መሆን ትችላለች ሲል ከክርስቶስ ጋር እያወዳደራት ይሆን?

## ሰማዕት ለመሆን ለምን ፈለገች?

ክርስትና ከሌሎች ሃይማኖቶች ለየት የሚያደርገው መርጠውት የሚመጡ ሰዎች እንዲሞቱለት፣ መከራና ስቃይ እንዲቀበሉ የሚጠይቅ መሆኑ ነው፡፡ ከሐዋርያት ጊዜ ጀምሮ እስከ አሁንም

[26] የሰኔ ገድለ አርሴማ ቍጥር 38፡፡

ድረስ ሰዎች የክርስቶስ ተከታዮች ስለ ሆኑ መከራና ስቃይ ከመቀበል ጀምሮ እስከ ሞት ድረስ ተጉዘዋል፤ ይህም እስከ ጌታ ምጽአት ድረስ የሚቀጥል ነው።

ቀደም ሲል እንደተባለው ለሰማዕትነት ራሳቸውን አሳልፈው የሰጡት ሰዎች ‹‹ለምንድን ነው ሰማዕት ለመሆን የፈቀድከው?›› የሚለው ጥያቄ ቢቀርብላቸው የተጠራነው በክርስቶስ ልናምን ብቻ ሳይሆን መከራን ልንቀበልም ጭምር ነው የሚል መልስ መስጠት ግድ ነው (ፊልጵስዮስ 1፥29)።

አርሴማስ? በገዛ ፈቃዷ ሰማዕት ለመሆን የሄደችው ለምንድን ነው? ማንም ሳያስገድዳትና ማንም ሳይገፋፋት እንዲያውም ክርስቲያኖቹን በማሰቃየት ላይ የሚገኘውና ገድሉ ጨካኝ ነው የሚለው የንጉሡ ሹም ‹አንቺ ከእነዚህ ሰማዕታት ጋር አብረሽ አትሁኚ ይቅርብሽ› እያለ ሲያግባባት አይሆንም ከእነርሱ ጋር ሰማዕት ለመሆን እሻለሁ ብላ ከሃያ ሰባቱ ሰማዕታት ጋር ለምን አብራ ተሰለፈች? በገድሉ ላይ የሰፈረው ታሪክ የሚከተለውን ይመስላል።

አርሴማ ‹‹በአዳራሽዋ ሰገነት››[27] ላይ ሆና ስትጸልይ እና መጻሕፍትን ስታነብ በነበረበት ጊዜ ሰማዕታቱ[28] ሲገረፉ

---

[27] ምንባቡ እንደሚያሳየው አርሴማ ባለ ሰገነት የሆነ አዳራሽ አላት። ቊጥር 35 ላይ እንደ ተገለጸው ‹‹… ከቤቷ አዳራሽ ሰገነት ወረደች›› በማለት ባለ ሰገነቱ ቤት የእርስዋ መሆኑን ያረጋግጣል። ይህ ግን በአገርዋ ሆና ሳይሆን በስደት ላይ በሰው አገር ሆና ነው። ነገር ግን ገድሉ ጥቂት ቊጥሮችን ከፍ ብሎ እርስዋና ከእርስዋ ጋር የነበሩትም ጭምር ‹‹በትልቅ ችግርም ተቀመጡ። ምግባቸውን የሚያገኙ አልነበሩም። ከእነርሱም አንዲትዋ መብራት ትሠራ ነበር። ከዚህች ሴት ሥራም ይመገቡ ነበር›› የሚል አስፍሮ ይገኛል። ከዚህ በኋላ ምን እንዳገኙ፣ የት እንዳረፉ ምንም

ታያቸውና ለምን እንደሚገረፉ ስትጠይቅ ‹‹ስለ ክርስቶስም እንደሚገረፉ ነገሯት፡፡ ያን ጊዜም እንባዋን ከዓይኖቿ በፊቷ ላይ አፈሰሰች፡፡ ስለ እነዚህ ሰማዕታት ትጸልይ ዘንድ በልብ ጭንቀት ወደ ሰማይ አንጋጠጠች››፡፡ ገድሉ ምን ብላ እንደ ጸለየች ግልጽ ባያደርግም ሰማዕታቱ ከዚህ መከራ ነጻ እንዲሆኑ የጸለየች ይመስላል፡፡

ጸሎቷን እንደጨረሰችም ‹‹ከእግዚአብሔር ዘንድ ተገልጦላት የብርሃን አክሊል የያዙ ብሩሀን መላእክት አየች፡፡ ለእነዚህ ሰማዕት ይሰጧቸውና ይሸልሟቸው ዘንድ››፡፡ በመከራ ውስጥ ለነበሩት ሰማዕታት ስትጸለይ የነበረችው አርሴማ ይህን ስትመለከት ያደረገችውን ገድሉ ከዚህ እንደሚከተለው ያስነብባል፤ ‹‹በታላቅ ቃል እየጮኸች ስለ ቅዱስ ስምህ ሰማዕት እሆን ዘንድ ጌታዬና አምላኪዬ ሆይ ርዳኝ እያለች ከቤቷ አዳራሽ ሰገነት ወረደች፡፡ ከዚያም በኋላ ልብሷን ለብሳ ወደ እነርሱ ሄደች››፡፡[29] ለምንድን የሄደችው? ቢባል ሰማዕት ለመሆን የሚል መልስ ነው የሚያገኘው፡፡[30]

---

ያሰፈረው ነገር ሳይኖር ባለ ሰገነት አዳራሽ ያደርጋታል (የኅዳር ገድለ አርሴማ ቍጥር 20)፡፡

[28] እነዚህ ሰማዕታት አብረዋት የመጡት አይመስሉም፡፡ አብረዋት የመጡት ቢሆኑ ኖሮ በእሷ ምክንያት ነውና የተሰደዱት አብራቸው መከራን ለመቀበል እስከ እዚህ ድረስ አትቆይም ነበር፡፡ እንደገናም ደግሞ ለምን እንደሚወገሩ መጠየቋ የማታውቃቸው ሰዎች ስለሆኑ ሊሆን ይችላል፡፡ አብረዋት የመጡት ሰዎች አብረዋት መከራን ለመቀበል የተሰለፉ አይመስልም፡፡ ወደ የት እንደ ሄዱ እንኳ ገድሉ ምንም ፍንጭ አይሰጥም፡፡

[29] የኅዳር ገድለ አርሴማ ቍጥር 32-35፡፡

[30] በገዛ ፈቃዷ ሰማዕት ለመሆን ሄደች የሚለው ገድለ አርሴማ መልሶ ደግሞ ‹‹እግዚአብሔር ባርያውን በእውነት እንደ ጎበኘ አሁን አወኩ አለች፡፡ መከራ ያሳዩኝ ዘንድ ከሚወዱ ጠላቶቼ እጅ አልጣለኝም፡፡ እነሱ

ስለዚህ አርሴማ ሰማዕትነትን የመረጠችው የጌታ ፍቅር ግድ ብሏት ሳይሆን ከሰማዕትነት በኋላ የሚገኘው ሽልማት አጓጉቷት ነው ማለት ይቻላል፡፡ ስለ ክርስቶስ ፍቅር ቢሆን ኖሮ ስለ ክርስቶስ መከራን እንደሚቀበሉ (እየተገረፉ ያሉት ስለ ክርስቶስ ፍቅር እንደ ሆነ) በሰማችበት ሰዓት ስለ እነርሱ በመጸለይ ፈንታ እነርሱን ለመምሰል ወስና በሄደች ነበር፡፡

## በራስዋ መንግሥተ ሰማያትን ተቀዳጀች

ቀደም ሲል በገዛ ፈቃዷ ሰማዕት ለመሆን የሄደችው አርሴማ ሰማዕት ለመሆን ፈቃዷን የሰጠችው ለሰማዕታት የሚሰጠውን ሽልማት (አክሊል) በማየቷ መሆኑን ያሰፈረው ገድሏ በራሷ መንግሥተ ሰማያትን መቀዳጀቷንም እንደሚከተለው ያስነብባል፤ ‹‹ስለ መልካም ሥራዋም የሕይወት ፍሬን አፈራች፡፡ ይኸውም ሰማዕት መሆን ነው፡፡ በደሟ ወርቅም መንግሥተ ሰማያትን ተወዳጀች፡፡ በእጆቿም የገነትን የዛፍ ፍሬ ያዘች፡፡ በውስጥዋም የበረታችና የቀናችን የሃይማኖት ሥር ተከለች››፡፡[31]

---

ግን ደክመው ወደቁ፡፡ ሰይፎቻቸውም ደቀቁ ድቃቂያቸውም ወደ ልባቸው ገባ›› በማለት አመሰገነች ‹‹ያ ወንጀለኛና አመጸኛ ንጉሥ ታስረው ወደ አሉት ይህቺን የተረገመች ሴት ውሰዱአት ሲል የተናገረውን ቃል ሰማ፡፡ ያን ጊዜም ጸለይኩና አንዲት ጊዜ እግዚአብሔርን ለመንኩት በሰጠኝ ችሎት መከራውን እሸከም ዘንድ የተዘጋጀሁ እንዲያደርገኝ ዳግመኛም እንደ ወፍ በርሬ ከገደል አመልጥ ዘንድ ጌታዬን ለመንኩት፡፡ እነሆም ኰብልዬ በራቅሁ፡፡ በምድረ በዳ በኖርሁ እንደ አውሎ ነፋስ ነፍሴን ልብ ከሚያሳጣት የሚያድነኝን እታመነዋለሁ›› ማለቷን ዘግቦ ይገኛል፡፡ እንዲህ ያለው ጸሎትና ንግግር በፈቃዱ ራሱን አሳልፎ የሰጠ ሰው ንግግር አይመስልም፡፡ አልያም ደግሞ የገባበትን ነገር ሳያውቅ ከገባበት በኋላ ወደ ኋላ ለመመለስ የፈለገና የተጸጸተ ሰው ሐሳብ ይመስላል (የመጋቢት ገድለ አርሴማ ቍጥር 35፤ የሚያዝያ ገድለ አርሴማ ቍጥር 11-13)፡፡

[31] መቅድም ቍጥር 13 ይመልከቱ፡፡

በዚህ መሠረት ሰማዕት የሆነችው ለሽልማት ሳይሆን የሕይወትን ፍሬ ለማፍራት ነው፤ እርሱንም አፍራታለች። ከዚህም ሌላ በደሚም[32] መንግሥተ ሰማያትን ለማግኘት ታድላለች። ከዚህም የተነሣ የገነትን የዛፍ ፍሬ ይዛለች።[33] ይህን ምንባብ የተመለከተ የክርስቶስ ደቀ መዝሙር የሆነ ክርስቲያን አርሴማ በገዛ ፈቃዷ መንግሥተ ሰማያትን ለመቀዳጀት ከበቃች የክርስቶስ ደም ሥራ ምንድን ነው? የሚል ጥያቄ ቢያነሣ፣ ሌሎች ሰማዕታትስ በራሳቸው ደም መንግሥተ ሰማያትን እንዳይቀዳጁ ምንድን ነው የከለከላቸው? የሚል ጥያቄ ቢያስከትል ጥያቄህ አግባብነት የለውም የሚለው ማን ይሆን? እንዲህ ያለውን ጸረ ወንጌልና ጸረ ክርስቶስ የሆነ መጽሐፍ ተሳስቷል ለማለት ቤተ ክርስቲያን ምነው አቅም አጣች?

## ለሰው መዳን ያላት ልብ

በገዛ ደሚ መንግሥተ ሰማያትን የተቀዳጀችው አርሴማ ለሌሎችስ መዳን ምን ዓይነት ልብ ይኖራት ይሆን? ቢባል አሁንም ገድሏ ከዚህ በታች ያሉትን ሐሳቦች ያቀርባል፤

[32] ደሚን ለመግለጽ የተጠቀመው ‹‹በደሚ ወርቅም›› የሚለውን ነው። ይህም ደሚ ምን ያህል ዋጋ እንደተሰጠው የሚያሳይ አገላለጽ ነው። የገድሉ ጸሐፊ በገዛ ደሚ ለመዳን ቻለች ካለ የክርስቶስ ኢየሱስ ደም አያስፈልጋትም ማለቱ መሆኑ ግልጽ ነው። ይህ ደግሞ የገድሉ ድብቅ ዓላማ አካል መሆኑ መታወቅ አለበት። አርሴማ በወርቀ ደሚ እንደዳነች መስፈሩ እኛንም ልታድነን ትችላለች ማለቱ ነው። እርሷ እኛን ማዳን ከቻለች ደግሞ የኢየሱስ ሞት (ደም) አስፈላጊያችን አይደለም ማለት ነው። በዚህም መንገድ ከኢየሱስ ጋር እንድንለያይ ያደርጋል ማለት ነው። ይህ ነው የገድሉ ድብቅ ዓላማ።

[33] ይህ የገነት የዛፍ ፍሬ የተባለው ምን ይሆን?

# እውነትን ለመመስከር ፍላጎት የላትም

በመጽሐፍ ቅዱስም ሆነ በታሪክ የምናውቃቸው አባቶች ባገኙት አጋጣሚ ስለ ክርስቶስ የሚመሰክሩና ሰዎችን ሁሉ ወደ መዳን የሚጠሩ ናቸው፡፡ ሰላም በሆኑበት ወቅት ላገኙት ሕዝብም ሆነ ተከሰው ነገሥታት ፊት ሲቀርቡ ስለ ጌታችን መናገርን ቸል አይሉም ነበር፡፡

አርሴማም በተመሳሳይ ሁኔታ በንጉሡና በሌሎችም ባለ ሥልጣናት ፊት የመቅረብ እድሉ ገጥሟት ነበር፡፡ በእነዚህ ሰዎች ፊት ስትቀርብ ስለ ክርስቶስ የመናገር እድሉን አግኝታ የነበረ ቢሆንም እርሷ ግን ከመናገር ይልቅ ተገቢ ያልሆኑ ድርጊቶችን በማድረግ ስትገለጥ ትታያለች፡፡[34]

አንድ ጊዜ ንጉሡ ፊቱ እንድትቀርብ አደረገና ‹‹ስለ አገር ሰዎችና ስለ ቤተ መንግሥት የምታስቢውን እስኪ ንገሪኝ አላት››፡፡ ንጉሡ ለጠየቃት ለዚህ ጥያቄ ግን እርስዋም ‹‹የዚህች አገር ሰዎች ሁሉ ያብዳሉ፡፡ አንተም እንደነሱ ታብዳለህ፡፡ መልክህና ምሳሌህ ይለወጣል፡፡ እንደ እሪያ መልክ ትሆናለህ›› የሚል መልስ ሰጥታዋለች፡፡[35] እዚህ አገር ከገባችበት ጊዜ ጀምሮ ስለ እራሷና አጠገቧ ስላሉት ሰማዕታት እንጂ ስለሌላ ሰው ምንም ስታደርግ (ስለ ሕዝቡ ስትጸልይም ሆነ ለነዋሪዎቹ ስትመሰክር) አትታይም፡፡ እንደ እውነቱ ከሆነ ግን በንጉሡም ሆነ በሕዝቡ ላይ ስለሚደርሰው ሁኔታ ስትጸልይ መታየት ነበረባት (2ኛ ጢሞቴዎስ 2፥1)፡፡

---

[34] ያደረገችው ተገቢ ያልሆነ ነገር ምንድን ነው? የሚለውን ለመመልከት ‹‹ለቸርነቷ ልማድ ወሰን የለውም›› በሚል የርዕስ ሰፈረውን ጽሑፍ ይመልከቱ፡፡

[35] የሐምሌ ገድለ አርሴማ ቊጥር 24፡፡

እርሷ ግን ንስሐ እንዲገባና በክርስቶስ እንዲያምን ከመናገር ይልቅ እንዲህ ያለ የሚርትና የስድብ ንግግር ትናገረው ነበር፡፡ ንጉሡ ‹‹እኔ መልካምን ነገር ስናገርሽ አንቺ ግን የስድብን[36] ነገር በእኔ ላይ ታስቀድሚያለሽ›› በማለቱ ከእርሷ የተሻለ ሆኖ ይታያል፡፡[37] ምናልባት ‹‹ያላመኑበትን እንዴት አድርገው ይጠሩታል? ባልሰሙትስ እንዴት ያምናሉ? ያለ ሰባኪስ እንዴት ይሰማሉ?›› ተብሎ መጻፉን አታውቅ ይሆን (ሮሜ 10፥14)?

## በአምላክሽ ልመን ያላትን ለመርዳት ፈቃደኛ አለ መሆኗ

ሰዎች ሰማዕትነትን ከሚቀበሉባቸው ምክንያቶች ቀዳሚው ስለ ጌታችን በመመስከራቸው ነው (ራእይ 9፥6)፡፡ ምስክርነታቸውን የሚናገሩት ደግሞ ሰዎችን ለማዳን መሆኑ እርግጥ ነው፡፡ በምስክርነታቸው ወቅት የሚደርስባቸውን ማስፈራሪያና ዛቻ ከዚህ አልፍ ሲልም መከራና ስቃይ ከዚህ ባስ ሲልም ሰማዕትነትን በሙሉ ደስታ ይቀበሉታል፡፡ በዚህ ሁሉ ሂደት ወቅት ግን ባገኙት አጋጣሚ ነገሥታት ይሁኑ አገልጋዮች፣ ጣዖት አምላኪ ይሁኑ ወይም ሌላ ከእነርሱ እምነት ጋር ለመስማማት ፈቃደኛ የሚሆኑ ሲያገኙ ማድረግ የሚገባቸውን ሁሉ አድርገው ከእነርሱ እውነት ጋር እንዲስማሙ ለማድረግ ይተጋሉ፡፡

---

[36] ስድቦችዋን በተመለከተ እና እሷ ስትሳደብ የንጉሡ ምላሽ ምን ነበር? የሚለውን ‹‹የስድብ አፍ›› በሚለው ርዕስ ስር የቀረበውን ጽሑፍ ይመልከቱ፡፡

[37] የሰኔ ገድለ አርሴማ ቊጥር 24፡፡

ለዚህ ጥሩ ምሳሌ የሚሆነው ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ ነው፡፡ አግሪጳ ፊት ቀርቦ ሳለ ‹‹በጥቂት ክርስቲያን ልታደርገኝ ትወዳለህ?›› የሚል ጥያቄ ሲቀርብለት ‹‹በጥቂት ቢሆን ወይም በብዙ አንተ ብቻ አይደለህም ነገር ግን ዛሬ የሚሰሙኝ ሁሉ ደግሞ ከዚህ እስራቴ በቀር እንደ እኔ ይሆኑ ዘንድ ወደ እግዚአብሔር እለምናለሁ›› የሚል መልስ ሰጥቷታልና (የሐዋርያት ሥራ 26፥28-29)፡፡

በገድለ አርሴማ ውስጥ እንደሰፈረው ከሆነ አርሴማ ከጳውሎስ የተሻለ እድል አግኝታ ነበር፡፡ ንጉሡ ለአምላክሽ እገዛለሁ የሚል መልካም ነገር ተናግሮ ነበርና፡፡ ምናልባት ገድሉ እንደሚለው ከሆነ ንጉሡ ለአምላክሽ እገዛለሁ ያለው እርሷን ለማግባት መሆኑ ግልጽ ነው፡፡ ይሁን እንጂ እርሷ ይህን ባትፈልግ እንኳ (እርሷን ስለ ወደደ ሳይሆን እግዚአብሔርን ወድዶ መምጣት ያለበት በመሆኑ) ልታስተምረውና እግዚአብሔርን ወድዶ በገዛ ፈቃዱ እንዲከተለው ማድረግ በተገባት ነበር፡፡

> ንጉሡም መለሰላት፤ ማመኔን ብትወጂ ግን፣ ከእኔ ጋር ፍቅርን አድርጊ፡፡ ከትእዛዜም አትተላለፊ፡፡ እኔ ለአምላክሽ እገዛለሁና፡፡ ይህንም ነገር በተናገረ ጊዜ መንፈስ ርኩስ ፊቱን መታው፡፡ ከእናትህ ማኅፀን ጀምሮ ያሳደኩህንና በሥራህ ሁሉ ልብ፣ አፍና ብርታት ስሆንህ፣ በኃይሌ ብርታት የክርስቲያንን ልጆች እንድታስጨንቃቸው፣ እስከ ዛሬ አደረስኩህ፣ እኔን ለምን ተውኸኝ? እያለ፤ ዛሬ ግን በክፋቷ ብዛት ሁል ጊዜ ስለምታስቸግረኝ ስለዚህች ሴት እግዚአብሔር አምላክን ታመልክ ዘንድ ወደድህን?

አለው፡፡ ዳግመኛም ዲያብሎስ ስለዚች ሴት ፍቅር እኔን የረሳኸኝ ለምንድን ነው? አለው፡፡ እሺ ብትዪኝ ለአምላክሽ እገዛለሁ አልሁት፡፡ ያን ጊዜም አፉ እስከሚጣመም ድረስ በምድር ላይ ወደቀ፡፡ አፉንም ከፈተ እንደ ርኩስ በድንም ሆነ፡፡

በዚህ ታሪክ ላይ ርኩሱ መንፈስ በአርሴማ ፊት ንጉሡን እንዲህ ያሰቃየው አርሴማን ስለ መውደዱ አለ መሆኑ ግልጽ ነው፡፡ ምክንያቱም ንጉሡ አርሴማን ወድዶ የራሱ ሊያደርጋት ጥረት ማድረግ ከጀመረ ሰነባብቷልና፡፡ ዲያብሎስ ንጉሡን እንዲህ የማድረጉ ምክንያት አርሴማን ከመውደዱ የተነሣ የአርሴማን አምላክ ለማምለክ ስለ ፈቀደ ነው እንጂ፡፡ አምላኳን የሚያመልክ አግኝታ ነገር ግን ዓይኗ እያየ ዲያብሎስ ንጉሡን ክፉኛ ሲያሰቃየው አርሴማስ ምን አደረገች? የሚለውን ከመመልከታችን በፊት፤ ‹ምንም ልትረዳው አትችልም ምክንያቱም እርሷ ምንም የማድረግ አቅም የላትምና› የሚል ሰው ቢኖር ገድሉ ስለ አርሴማ የሚለውን ማቅረቡ ተገቢ በመሆኑ ሁለት ማሳያዎች ከዚህ በታች ሰፍረዋል፤

- ‹‹የጣዖቱ ካህናትም ስማቸው ቴያጥሮን፣ ህልዋርህ፣ ጌርጋሮ፣ አድዋልህ ነው፡፡ ቡርክት ቅድስት አርሴማን በአዩት ጊዜ ደንግጠው በነፋስ ፊት እንዳለ ቅጠል ተንቀጠቀጡ፡፡ አማልክቶችም አጋንንት በላያቸው እንዳለባቸው አውሬዎችና ላሞች ጩኸት ጮኹ፡፡ አማልክቱም በምድር ወድቀው ጠፉ፡፡ አጋንንት በላያቸው ያለባቸው አማልክትም ይህችን ወንጀለኛ የምታስፈራና ፈጽማ የምታስደንግጥ ሴት ወደ እኛ ለምን አመጣችኋት እያሉ ጮኹ፡፡ እርሷ የክፋትና የተንኮል መምህር ናትና

ዛሬ ብናያት በነበልባሏ አቃጠለችን፡፡ ይህች አርሴማ የምትሏት ገሊላዊት ሴት ወደዚህ ማደሪያችን ብትገባ እኛ መሸሸጊያና መሸሻ የለንም፡፡ ከእርስዋ ጋር እድል የለንም፣ የቀኝ ጣቷ በፊትዋ አያቆመንም፡፡ ወደርስዋም ብንሄድ እንደ እሳት ነበልባል ያቃጥላልና፡፡ በላይዋ ብርቱ ኀይል አለና፡፡ ዛሬ ብቻ ድል የምታደርገን አይደለም፡፡ ከሞተችም በኋላ በገድሎችዋ መጽሐፍና በራስዋ ስም መታሰቢያ በኋለኛው ዘመን ድል ታደርገናለች እንጂ አሁንም ወደ ማደሪያችን እስከ ዘላለም ድረስ ከዚህ አታስገቡአት››፡፡[38]

- ‹‹እሱም በአርጤምስ ልብ ገብቶ የአቴናን ሰዎች ያሳታቸው [ጋኔን] ነው፡፡ እነዚህም መተተኞች እነግራችሁ ዘንድ ስሙኝ፡፡ በዚህ ቦታ ውስጥ በዚህች ቀን ብትጠሩን የምንመጣ አይደለም አላቸው፡፡ ይህቺ ሴት በነበልባሏ አቃጥላናለችና በቃሏ አስደንግጣናለችና፡፡ እኛ በእጇ ገመድ የታሰርን ነን፣ በእርሷ ወጥመድ አጥምዳናለች፡፡ በእርሷስ ላይ ክፉ እናደርግ ዘንድ አይቻለንም፡፡ ከእኛ በሚበልጥና በሚበረታ እጅ ግርማውም በሚያስፈራን ፈጣሪዋ ይጠብቃታልና፡፡… ከእኛም ብዙ ሰራዊት አስጥማለችና፡፡ ስለዚህም ወደ እርስዋና የእርስዋን ስም ወደሚጠራ እኔ አልቀርብም አላቸው››፡፡[39]

በእነዚህ ቦታዎች አጋንንትን በማንቀጥቀጥ የሠራችው ተኣምር አንድም ሰው እንኳ ወደ እግዚአብሔር መንግሥት ያላመጣ ሲሆን እርሷን ግን ሁሉ የሚፈራት ታላቅ ሴት እንድትባል

[38] የግንቦት ገድለ አርሴማ ቍጥር 42-43፡፡ የሰኔ ገድለ አርሴማ ቍጥር 34፡፡ የነሐሴ ገድለ አርሴማ ቍጥር 1፡፡
[39] የነሐሴ ገድለ አርሴማ ቍጥር 10-11፡፡

አድርጓታል። ይህም ደግሞ ክብርን ለእርሷ የሚሰጥ እግዚአብሔርን ግን ቸል ያለ መሆኑን መመልከት ይቻላል።

ከዚህ በተለየ መልኩ የሰው ነፍስ ልትታደግበትና እግዚአብሔርን ልታስከብር እድሉ በነበራት ቦታ ላይ ዲያብሎስ ንጉሡን ለማሰቃየት ችሎ ነበር። የሚገርመው ንጉሡ በእግዚአብሔር ለማመን በማሰቡ እንደዚያ ሲሰቃይ ‹‹ቡርክት ቅድስት አርሴማ ከንፈሮችዋን ሳትገልጥ በመንፈስ ቅዱስ ፈገግ አለች። የምታመልኳቸው አማልክቶቻችሁ ገዳዮች ናቸው፤ ያው የነቢዩ ቃል ተፈጸመብህ››[40] ከማለት በቀር እንደ መንፈሳዊ ሴትነቷ ስትረዳው (ስትጸልይለት) አትታይም።

ይህን ታሪክ እንደ ክርስቲያን ለተመለከተው ሰው ፈገግ የሚያሰኝ ሳይሆን የሚያሳዝን ነው። የንጉሡ መሰቃየት ፈገግ የሚያሰኘው ክርስቲያንን ሳይሆን በጣዖት አምልኮ ውስጥ ያለና ንጉሡ ከጣዖት አምልኮ ወደ ክርስትና ለመሄድ በማሰቡ አጋንንት ትክክለኛ ቅጣት እየቀጣው ነው ብሎ ለሚያስብ ሰው ነው። አርሴማ መጽሐፍ ቅዱሳዊውን እውነት የተረዳችና እርሱ በሚለው መሠረት ለመኖር የወሰነች ሴት ከሆነች ይህን ዕድል ተጠቅማ ንጉሡን ከያዘው ርኩስ መንፈስ ነጻ በማውጣት በአንደበቱ እንደተናገረው በእግዚአብሔር እንዲያምን መርዳት ነበረባት። ከገድሉ እንደምንረዳው ‹‹በመንፈስ›› ፈገግ ያስባላት የንጉሡን በእግዚአብሔር ለማመን መወሰኑ ሳይሆን በዲያብሎስ እጅ ስቃይ መቀበሉና ነጻ መውጣት አለ መቻሉ ነው። ይህን የፈገግታ መንፈስ በእርግጥ ከእግዚአብሔር ነው ማለት ይቻል ይሆን? የክርስቶስ ፍቅር የገባው ሰው በሰው ልጆች ስቃይ እንዴት ይደሰታል? ፈገግ አለች የተባለው ደግሞ

---

[40] የሰኔ ገድለ አርሴማ ቍጥር 30-31።

‹‹በመንፈስ ቅዱስ›› መሆኑ ነገሩን የበለጠ አስገራሚ ያደርገዋል፡፡

## ጸሎቷ

መጽሐፍ ቅዱስ ‹‹የጻድቅ ሰው ጸሎት በሥራዋ እጅግ ኃይል›› እንደምታደርግ ያስተምራል (ያዕቆብ 5፥16)፡፡ በእግዚአብሔር የሚያምን ሁሉ ጸሎትን ወደሚሰማው አምላክ ወደ እግዚአብሔር ሊጸልይ እንደሚገባውም ‹‹ሥጋ ሁሉ ጸሎትን ወደምትሰማ ወደ አንተ ይመጣል›› ተብሎ ተጽፏል (መዝሙረ ዳዊት 64፥2)፡፡

በክርስቶስ የሚያምን ሰው ‹‹ስለሚያሳድዱአችሁም ጸልዩ››፣ ‹‹የሚረግሙአችሁንም መርቁ፥ ስለሚበድሉአችሁም ጸልዩ›› ተብሎ መጻፉን አይዘነጋውም (ማቴዎስ 5፥44-45፤ ሉቃስ 6፥28)፡፡ ስለዚህም ማንም ክፉ ቢያደርግበትም ሆነ በክርስትናው ምክንያት መከራ ቢቀበል ስለ ክፉው ፈንታ በክፉ አይመልስም፡፡ ስለ ሁለቱ ምክንያት ማለትም ጸሎትን ወደ እግዚአብሔር ስለ ማቅረብና ክፉ ስላደረጉ ሰዎች ስለሚኖረው ጸሎት ገድለ አርሴማ ላይ ምን ተብሎ ተጽፏል?

## በጸሎቷ ለሚያምኑ…

አንዱን ጻድቅ ከሌላው የተሻለ ለማስመሰል ከሚደረጉ ሙከራዎች ውስጥ አንዱ ጸሎት ሰሚነታቸው ሲሆን፤ ሌላው ደግሞ በእነርሱ ስም የሚደረጉ ልመናዎች በፍጥነት እግዚአብሔር ዘንድ ደርሰው ምላሽ የሚያመጡ ናቸው መባሉ ነው፡፡

ከእነዚህ ውስጥ ገድለ አርሴማ አንዱ ሲሆን በገድሉ ውስጥ ከሰፈሩትም መካከል ‹‹በጸሎትዋ ኀይልና በረድኤትዋ ለሚያምን መድኀኒት ትሆን ዘንድ ከእናቷ ማኅፀን ከአባቷ አብራክ ለይቶ፣ አክብሮና መርጦ የመንፈስ ቅዱስ ጸጋ በላይዋ ላይ ያደረባትን ብፅዕት አርሴማን እሽ ማሰኘት አልቻሉም›› የሚለው ይገኝበታል፡፡[41]

በገድሉ ሐሳብ መሠረት አርሴማ ከእናትና ከአባቷ አብራክ የተለየችው በጸሎትዋ ረድኤት ለሚያምኑ ሰዎች መድኀኒት ትሆን ዘንድ ነው፡፡ ይህ ደግሞ፣ መጽሐፍ ቅዱስ መድኀኒት እንደ ሆነ የሚናገረው ክርስቶስ ኢየሱስንና የሠራውን የመስቀል ላይ ሥራ የሚያስንቅና ክርስቲያናዊ ያልሆነ ትምህርት ነው፡፡

ጌታችን ለሰው ሁሉ መድኀኒት የሆነው ስለ ሰው ልጅ ሁሉ ራሱን አሳልፎ በመስጠት ይሄውም መከራን በመቀበልና ደሙን በማፍሰስ እንዲሁም በመሞት ነው፡፡ ገድለ አርሴማ ደግሞ አርሴማ መድኀኒት ሆነች የሚለው በጸሎትዋ ነው፡፡ ከዚህ በላይ ኢ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ትምህርት ይኖር ይሆን? እንዲህ ያለውን የስሕተት ትምህርት ቤተ ክርስቲያን ልታሰወግደው ይገባታል፡፡

## ነፍሰ ገዳይ እንዳልባል

አርሴማ በልዩ ልዩ ምክንያቶች የጸለየቻቸውን ጸሎቶች ገድሉ ያስነብባል፡፡ ምክንያቶቹ የተለያዩ እንደ መሆናቸው መጠን ምላሾቹም በዚያ ልክ ልዩ ልዩ ናቸው፡፡ አርሴማ ከጸለየቻቸው ልዩ ልዩ ጸሎቶች መካከል ከዚህ በታች የሰፈረው አንዱ ነው፤

[41] የጥር ገድለ አርሴማ ቍጥር 98፡፡

ጌታዬ ኢየሱስ ክርስቶስ ሆይ፤ በኀይልህ ርዳኝ። በመስቀልህም አጥር እጠረኝ። የእነዚህ ብርቱዎችና ኀይለኞች ሰዎች ኀይል ይቀልጥ ዘንድ በቅዱሳን መላእክትህ ክንፎች ጋርደኝ። ይይዙኝ ዘንድ ይወዳሉና። ያን ጊዜም በራሷ አመድን ነሰነሰች። ቍጥር የሌላቸውን ብዙ ስግደቶችንም ሰገደች። ምድር እስከምትንቀጠቀጥ ድረስ፣ ንጉሡንና ወታደሮችን ያጠፋቸው ዘንድ፣ በታላቅ ግርማ የእግዚአብሔር መላእክት ሚካኤልና ገብርኤል ወረዱላት። ነገር ግን፤ ጌቶቼ ሆይ፤ በእግዚአብሔር ዘንድ ነፍሰ ገዳይ እንዳልባል ተዉአቸው፤ እያለች ስለ እነርሱ ጸለየች። ያን ጊዜም ብፅዕት አርሴማን ይይዙአት ዘንድ የወደዱ ሰዎች ሁሉ ደነገጡ። ተንቀጠቀጡ። ሊቀርባትም የቻለ የለም፤ የልብሶችዋንም ጫፍ ቢሆን፤ የእግዚአብሔር ኀይል ጋርዶአታልና። ኵራትና አሳሳቾችም እንዳይዳስሱአት በንጽሕና ጠብቆአታልና።[42]

በታሪኩ ላይ እንደሰፈረው አርሴማ የጸለየችው ጸሎት ተሰምቶ መልሱ በአግባቡ መጥቷል። ጸሎቷን ለተመለከተው ሰው ግን ይህቺ ሴት በክርስቶስ ኢየሱስ የማዳን ሥራ ያመነች ክርስቲያን ናትን? የሚል ጥያቄ ቢያነሣ አልተሳሳተም።

በዚህ ጸሎት ውስጥ ከሚገኙት ልመናዎች አንዱ ‹‹የእነዚህ ብርቱዎችና ኀይለኞች ሰዎች ኀይል ይቀልጥ ዘንድ በቅዱሳን መላእክትህ ክንፎች ጋርደኝ›› የሚለው ይገኝበታል። ለዚህ ደግሞ ያቀረበችው ምክንያት ‹‹ይይዙኝ ዘንድ ይወዳሉና››

---

[42] የመጋቢት ገድለ አርሴማ ቍጥር 25-28።

የሚለው መሆኑ መያዧን ለምን ፈራችው? የሚል ጥያቄ ያስነሣል። ምክንያቱም ሰማዕት ለመሆን ማንም ሰው ግድ ሳይላት በራሷ ፈቃድ ነው የሄደችው። የንጉሡ ወታደር እባክሽ ከእነዚህ አንዷ አትሁኚ ይቅርብሽ እያለ ቢያግባባትም አይሆንም ብላ ሰማዕት ለመሆን ወዳና ፈቅዳ የተከተለች ሴት ናት።[43] እዚህ ጋር ምን የተለየ ነገር መጥቶ ነው የእግዚአብሔርን ጥበቃና ከለላ የፈለገችው?

ሌላውና በዚህ ጸሎት ውስጥ ያለው አስገራሚው ነገር የእርሷን ጸሎት ሰምተው ‹‹ንጉሡንና ወታደሮችን ያጠፉአቸው ዘንድ›› ሚካኤልና ገብርኤል መጡ መባሉ ነው። አንባቢው ልብ ማለት ያለበት አርሴማ የጸለየችው ከለላ ፍለጋ ቢሆንም መላእክቱ ግን ከንጉሡ ጀምሮ በተዋረድ ያሉትን ወታደሮች ሁሉ ለማጥፋት መምጣታቸውን ነው። ይህ ደግሞ በቤተ ክርስቲያናችን ታሪክ ውስጥ የመጀመሪያዋ ምናልባትም ብቸኛዋ ሰማዕት በማስመሰል የተሠራው ሥራ ከዚህ በፊት የነበሩትን ሰማዕታት የዘነጋ ነው።

ቤተ ክርስቲያን ከእስጢፋኖስ ጀምሮ የበርካታ ሰማዕታትን ታሪክ ይዛለች። እነዚህ ሰማዕታት እግዚአብሔር ጥበቃ እንዲያደርግላቸው አልጸለዩም ይሆን? ታዲያ ምነው ጌታ ሳይረዳቸው ቀረ? አንድ ጊዜ ብቻ አይደለም ተደጋጋሚ ሰማዕትነትን እንደተቀበሉ[44] የሚነገርላቸው ሰማዕታት ባሉባት ቤተ ክርስቲያን ሰማዕትነትን ልትቀበል ወዳና ፈቅዳ የሄደችውን አርሴማን ለመጠበቅ ተደረገ የተባለው ከለላ የተጋነነ ነው።

---

[43] በዚህ መጽሐፍ ‹‹ሰማዕት ለመሆን ለምን ፈለገች?›› በሚለው ርዕስ የሰፈረውን ይመልከቱ።

[44] ገድለ ጊዮርጊስ እንደሚለው ጊዮርጊስ ሦስት ጊዜ ሰማዕት በመሆን በልዩ ልዩ መንገዶች ሰማዕትነትን ተቀብሏል።

በዚህ ጸሎት ውስጥ የሚገርመው ሌላው ነገር ደግሞ ሚካኤልና ገብርኤል ንጉሡንና ወታደሮቹን ሊያጠፉ ሲመጡ እርሷ በድጋሚ ያቀረበችው ልመና ነው። በዚህ ልመናዋ ውስጥ ሰዎቹ እንዳይጠፉ (እንዳይሞቱ) የጠየቀችው ‹‹ነገር ግን፤ ጌቶቼ ሆይ፤ በእግዚአብሔር ዘንድ ነፍሰ ገዳይ እንዳልባል ተዉአቸው፤ እያለች ስለ እነርሱ ጸለየች›› በሚል ነበር (አጽንዖት የግል)። ምንም እንኳ ሰዎቹ በደለኛ ቢሆኑምና በእርሷ ጸሎት ምክንያት ይህ ሁሉ ነገር ቢደረግም እርሷ መልሳ የጸለየችው ግን ‹‹ነፍሰ ገዳይ እንዳልባል›› የሚል መሆኑ ጸሎቷ እኔነት የጎላበት፣ ስሜ ይጠፋል የሚል ስጋት የሞላበት እንጂ ለሰዎቹ ምሕረት እንዲደረግ ከመፈለግና ሰዎቹን ለንስሐ ሞት ለማብቃት ከመሻት የመጣ አለ መሆኑን ያሳያል። ታዲያ እኔነቷ ያልሞተላትን ሴት ሰማዕት (ምስክር) ነች ለማለት እንዴት ይቻላል?

## ሕያው እንደ ሆነ ወደ ሲኦል ይውረድ!

መጽሐፍ ቅዱስ ክርስቲያን እንደ መሆናችን መከራ ሊገጥመን እንደሚችል ያስተምራል (የሐዋርያት ሥራ 9፥16። ሮሜ 8፥17። 2ኛ ቆሮንቶስ 7፥5። ፊልጵስዩስ 1፥29። 1ኛ ተሰሎንቄ 3፥4። 2ኛ ጢሞቴዎስ 1፥8)። በዚህ ጊዜ ‹‹ስለሚያሳድዱአችሁም ጸልዩ››፣ ‹‹የሚረግሙአችሁንም መርቁ፥ ስለሚበድሉአችሁም ጸልዩ›› ተባለ እንጂ የእርግማን ቃል እንድንመልስ አልተፈቀደልንም (ማቴዎስ 5፥44-45። ሉቃስ 6፥28)። ከዚህ በተቃራኒ የቆመው ገድለ አርሴማ ግን ከዚህ የተለየ ነገር አስፍሮ ይገኛል።

በታሪኩ ላይ እንደሰፈረው በንጉሡ ፊት ቆማ ከንጉሡ ጋር በነበራት የቃላት ልውውጥ ወቅት ‹‹በሰማያት ስለ አለው

ቅጣት <u>አስፈራርታና አስደንግጣ</u> ታላቅ ነገርን ያለ ፍርሃት ንጉሡን...›› በተናገረችው ‹‹ያን ጊዜም [ንጉሡ] ቡርክት እናታችንን ቅድስት አርሴማን አፏን ይጸፏት ዘንድ አዘዘ››፡፡ ይህን የንጉሡን ትእዛዝ ለመተግበር ‹‹የጥፋት ልጅ፣ የይሁዳን ዕድል የአደለው›› ተብሎ በመጽሐፉ የተገለጸው አንዱ አፏን መታት፡፡ ‹‹ከሚጣፍጡ ከንፈሮችዋና መልካም መዓዛ ከአላቸው አፍንጫዎችዋ ደም ፈሰሰ፡፡ ከቡርክት ቅድስት መስተጋድልት አርሴማ ፊት የፈሰሰው ደም ከራስዋ[45] እስከ እግርዋ ድረስ ተንጠባጠበ››፡፡

ለዚህ ድርጊቱ ‹‹ቅድስት›› የተባለችው የአርሴማ ምላሽ ምን ይሆን? መጽሐፍ ቅዱስ እንደሚለው ስለ ክፉ ፈንታ በጎ መመለስ ሲገባት ገድሉ የሚያስነብበው ግን ከዚህ በታች ያለውን ነው፤

> ቡርክት አርሴማም መለሰችለት፡፡ እንዲህም አለች፤ ፊቷን በጥፊ ወደ መታት ወደዚህ ወንጀለኛ ላይ፣ በእጇ ጣት በትእምርተ መስቀል እያማተበች፣ ፊቷን በጥፊ የመታት፣ ያ ወንጀለኛ ሕያው እንደ ሆነ ወደ ሲኦል ይወርድ ዘንድ፣ ምድርም አፏን ትከፍትና እንደ ዳታንና አንደ አቤሮን ትውጠው ዘንድ ወደ ፈጣሪዋ ለመነች፡፡ እንደ ብፅዕት አርሴማ ቃልም ሆነ፡፡ በሰጠመበትም ላይ ዘጋችው፡፡ ቅድስት አርሴማ ያደረገችውን ይህን ተኣምር ያዩ ከወታደሮች ብዙዎቹ ሸሹ፡፡ ንጉሡም ይሸሽ ዘንድ

[45] የተመታችው አፏን ነው፡፡ ከዚህም ሌላ ቀደም ብሎ ‹‹ከሚጣፍጡ ከንፈሮችዋና መልካም መዓዛ ከአላቸው አፍንጫዎችዋ ደም...›› መፍሰሱን ነግሮን ነበር፡፡ ታዲያ አፏን ተመታና ከአፍና ከአፍንጫዋ ደም ፈስሶ ሳለ እንዴት ሆኖ ነው ከራስዋ ጀምሮ ደም ፈሰሰ የተባለው?

ከዙፋኑ ተነሣ። ያን ጊዜም ቡርክት አርሴማ ፈገግ አለች። ቅዱሳን ሰማዕትም ስለ እርስዋ ተደሰቱ። መላእክት በላይዋ ሲከቡአት አይተዋልና

የሚል ርግማን የተሞላ ንግግር (ጸሎት) ነው።[46]

ቀደም ሲል በተደጋጋሚ እንደ ተባለው ይህቺ ሴት በራሷ ፈቃድ (ያለ ማንም አስገዳጅ) ሰማዕት ለመሆን የመጣች ሴት ናት። ወደ ሰማዕትነቱ ስትመጣም ‹‹በታላቅ ቃል እየጮኸች ስለ ቅዱስ ስምህ ሰማዕት እሆን ዘንድ ጌታዬና አምላኪዬ ሆይ ርዳኝ›› ብላ የጸለየች ሴት ናት።[47] ይህን ጸሎት ያደረገችው ደግሞ የመጣው ሁሉ ቢመጣ እስከ ሰማዕትነት ድረስ ልትሄድ በመወሰኗ መሆኑ ግልጽ ነው።

ሰማዕት ለመሆን (እስከ ሞት ድረስ ለመሄድ) ወስና የመጣች ሴት ገና ለገና አፏን የመታትን ሰው ‹‹ሕያው እንደ ሆነ ወደ ሲኦል ይወርድ ዘንድ›› መጸለይዋ ግን ለሰማዕትነት እንደ ተዘጋጀች አያሳይም። ስለ ክርስቶስ ስም ሰማዕት ለመሆን የተሰለፈ ሰው ክርስቶስ የሞተለትን ሰው ‹‹ሕያው እንደ ሆነ ወደ ሲኦል…›› አውርዶ ደስ በመሰኘት ፈገግ አይልም። በሰው ልጅ መጥፋት (ሞት) ደስ የሚሰኘው ጥንተ ጠላታችን ዲያብሎስ እንጂ የመንፈስ ቅዱስ ማደሪያ እንደ ሆነ የሚነገርለት ‹‹ቅዱስ›› ሰው ይኖራል ተብሎ አይጠበቅም።

‹‹የእምነታችን ጀማሪና ፈጻሚ›› የሆነው ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ አፉን የመቱትንም ሆነ ከዚያ የበዛ መከራና ስቃይ ያበዙበትን ሰዎች ማጥፋት ሲቻለው ‹‹የሚያደርጉትን

[46] የሚያዝያ ገድለ አርሴማ ቍጥር 70-88 - አጽንዖት የግል።
[47] የኅዳር ገድለ አርሴማ ቍጥር 32-35።

አያውቁምና ይቅር በላቸው›› በማለት ምሕረትን ለመነላቸው (ሉቃስ 23፥34)። የጌታን አሠረ ፍኖት የተከተለው ቀዳሜ ሰማዕት ቅዱስ እስጢፋኖስም በድንጋይ እየወገሩ ወደ ሞት እንዲሄድ ሲያደርጉት በተመሳሳይ ሁኔታ ‹‹ጌታ ሆይ ይህን ኀጢአት አትቍጠርባቸው›› አለ እንጂ ፍጃቸው፣ ጨርሳቸው አላለም (የሐዋርያት ሥራ 7፥60)። ቅድስት ናት የተባለላት አርሴማ ከጌታና ከደቀ መዛሙርቱ መማር ሲገባት አፏን በጥፊ የመታትን ሰው ከነነፍሱ ወደ ሲኦል እንዲገባ መጸለይዋ (ጸለየች መባሉ) ቅድስናዋን ጥያቄ ውስጥ የሚያስገባው ነው፤ ይህ የቅዱሳን ተግባር አይደለምና። ታዲያ እንዲህ ያለችውን ሴት ቅድስት ለማለት እንዴት ይቻላል? ርኅራኄ የጎደላት ሴት መሆኗንም አጠቃላይ ገድሉ በልዩ ልዩ መልኩ ያሳያል። ታዲያ በየትኛው ርኅራኄዋ ነው በበዛ ኀጢአት የተጨማለቁ ሰዎችን አማልዳ መንግሥተ እግዚአብሔርን እንደምታስጥ ተስፋ የተደረገው?

## ስግደት

## ሚካኤልና ገብርኤል ‹‹ነፍሴን እጅ ነሷት››

ስለ እኛ ትጸልያለች በሚል በምልጃዋ እንድንታመን የሚነገርላት አርሴማ ‹‹ከሰይጣን ጠብና ከክፋዎች አጋንንት እድን ዘንድ እንዲጸልዩልኝ መላእክት ሚካኤልና ገብርኤልን ለመንኋቸው። ለይቅርታ ተዘጋጅተው ከአየኋቸው የምሕረት መላእክት ረድኤትና ኀይልን ይልክልኝ ዘንድ›› ብላ እንደ ጸለየች መስፈሩ እንኳን ለሌላ ልትተርፍ ለራሷም ሌላ አማላጅ እንደሚያስፈልጋት የሚያሳይ ነው።

ገድለ አርሴማ ከዚህ አለፍ ብሎ ደግሞ ጸሎትዋ እንደተሰማና መልስ እንደ መጣላት ሲያበስር እንዲህ ይላል፤ ‹‹ያን ጊዜም

ስለ እኔ ጸለዩ፡፡ ነፍሴንም እጅ ነሱአት፡፡ እኔም ስለ አየሁት ሁሉ አደንቅሁ››፡፡[48] እዚህ ላይ ደግሞ ሚካኤልና ገብርኤል ለእርሷ እጅ የሚነሡ (የሚሰግዱ) እሷ ከእነርሱ ላቅ ያለች በመሆኗም ስግደታቸውን በመደነቅ ስትቀበል ያሳያል፡፡

ይህ ሐሳብ ደግሞ እርስ በእርሱ የሚጣረስ ነው፡፡ መላእክቱ ‹‹ከሰይጣን ጠብና ከክፉዎች አጋንንት እድን ዘንድ›› ይጸልዩልኝ ስትል ከእኔ ይበልጣሉ በማለቷ መሆኑ ግልጽ ነው፡፡ መልሳ ደግሞ እነርሱ ለእርሷ ያቀረቡትን ስግደት ትቀበላለች፡፡ ይህ ማለት ደግሞ እርሷ ከእነርሱ የተሻለች ነች ማለት ነው፡፡

የእግዚአብሔር መላእክት የሆኑት ሚካኤልና ገብርኤል እንዲህ ያለውን ነገር አያደርጉትም እንጂ ቢያደርጉት ዕጣ ፈንታቸው የቀድሞው መልአክ የአሁኑ ጠላታችን የሆነውን በሆኑ ነበር፡፡ እነርሱ ግን ሊሰገድለት የሚገባው አንድዩ ብቻ መሆኑን አስረግጠው ስለሚያውቁ ስግደታቸውን ለማንም አይሰጡም፡፡ ታዲያ ገድለ አርሴማ እንዲህ ያለውን ሐሰት ማስፈር ለምን አስፈለገው? ቢባል ምክንያቱ ሊሆን የሚችለው ሚካኤልና ገብርኤል የሰገዱላት ቅድስት ሴት ስለ ሆነች ሁላችንም ልንሰግድላት ይገባል ለማለት ተፈልጎ ነው፡፡ መመሪያቸውን መጽሐፍ ቅዱስ ያደረጉ ክርስቲያኖች ግን ዘጸአት ምዕራፍ 20 ይከለክላቸዋልና ከእግዚአብሔር በቀር ለማንም አይሰግዱም፡፡

## ትሰግድላቸዋለች… ይሰግዱላታል

ስግደት ለወደድነውና ደስ ላለን ሁሉ የምንሰጠው ነገር አይደለም፡፡ ስግደት (የጉልበታችን መሥዋዕት) የሚገባው የጉልበታችን ጌታ የሆነው ሁሉን ቻይ አምላክ ብቻ ነው፡፡

[48] የሚያዝያ ገድለ አርሴማ ቁጥር 15-17፡፡

ለዚህ ነው በቅዱስ ቃሉ ላይ ደግሞና ደጋግሞ ሊሰገድለት የሚገባው እርሱ ብቻ መሆኑን የተናገረው (ዘጸአት 20፥4-6፤ 34፥14። ማቴዎስ 4፥10። ራእይ 19፥10)።

በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ያሉና የኑፋቄ ትምህርት በመርጨት ላይ የሚገኙ አንዳንድ መጻሕፍት ግን ለአምላካችን ብቻ የሚገባውን የስግደት መሥዋዕት ለፍጡራንም እንድንሰጥ ሊያግባቡን ሲሞክሩ ይታያሉ። ከእነዚህም መካከል ገድለ አርሴማ አንዱ ነው። ገድሉም በአንደኛው ምንባቡ ላይ እከከኝ ልከክህ ዓይነት ነገር ያስነብባል፤

> ብፅዕት ቅድስት አርሴማ ግን ይህን ሁሉ መብልና መጠጥ አልወደደችም። ከቅዱሳን መስተጋድል ሰማዕት እግር በታች እጅ ትነሣቸውና ትሰግድላቸው ነበር እንጂ።... ከዚህ በኋላም ቅዱሳን ሰማዕት ሁሉ ለብፅዕትና ቡርክት ቅድስት አርሴማ ሰገዱላት፤ እጅም ነሷት።[49]

አርሴማ ቀድማ የሰገደችላቸው እነርሱም እንዲሰግዱላት ማግባቢያ ይሆን ዘንድ ይሁን ወይም እነርሱ ከእርሷ በላይ የሆነ ‹‹የቅድስና ማዕረግ›› ላይ ደርሰው ግልጽ ባይሆንም፤ እርሷ ለእነርሱ የሰገደችውም ሆነ እነርሱ ለእርሷ የሰገዱት ከቅዱሱ መጽሐፍ አስተምህሮ የተለየ እንግዳ ልምምድ ነውና ወገኔ እንዲህ ካለው ኢ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ልምምድና ትምህርት ራስህን ትጠብቅ ዘንድ በክርስቶስ ፍቅር ትጠየቃለህ።

---

49 የታኅሣሥ ገድለ አርሴማ ቊጥር 13-20።

## በልቤ ጉልበት እንጂ በሥጋዬ ጉልበት አልሰግድልህም

ቀደም ሲል እንደቀረበው አርሴማ ሰዎች እንዲሰግዱላት ማድረግ ብቻም ሳይሆን ሚካኤልና ገብርኤልም እንደ ሰገዱላት መናገሯ ሰፍሯል፡፡ ከዚህም አለፍ ሲባል ለሰዎች (ለሰማዕታቱ) ስትሰግድም ታይቷል፡፡ ወደ ሕይወቷ መጨረሻ አካባቢ ክርስቶስ ይመጣና ልዩ ልዩ ቃል ኪዳናትን ከገባላት በኂላ ‹‹ቡርክት ቅድስት አርሴማ ተንበርክካ ሰገደችና ጌታዬና አምላኪዬ ሆይ በልቤ ጉልበት እሰግድልሃለሁ፡፡ እኔን የሚያዩኝ ጠላቶቼ ሁሉ እንዳይዘባበቱብኝ በሥጋዬ ጉልበት አይደለም፤ አለች፡፡ ዳግመኛም ዛሬ ግን ፈቃድህን ያደረግሁና መልእክትህን የፈጸምኩ መሰለኝ›› ትለዋለች፡፡[50]

እዚህ ጋር ሁለት ነገሮችን መመልከት ይቻላል፤ በመጀመሪያ ጸሐፊው ‹‹ቡርክት ቅድስት አርሴማ ተንበርክካ ሰገደችና›› ያለውን ዘንግቶት ይሁን ወይም እንደ ስግደት ስላልቈጠረው በሥጋዬ ጉልበት አልሰግድልህም እንዳለች አድርጎ ያስቀመጠውን መመልከት ይቻላል፡፡ ይህ ደግሞ መጽሐፉ በአንድ ስፍራ ላይ እንኳ እርስ በእርሱ የማይግባባ መሆኑን ያሳያል፡፡

ሁለተኛው ደግሞ የአርሴማ ችግር ነው፤ በርግጥ ቀደም ሲል ከሰው ልጆች መዳንም ሆነ ከእግዚአብሔር ክብር ይልቅ ቅድሚያ ለእኔ፣ መጀመሪያ እኔ የሚል ልብ ያላት መሆኑ ቀርቦ ነበር፡፡ ይህ ችግሯ አሁንም ተደግሞ ይታያል፡፡ በዚህኛው ምንባብ ላይ ችግሯን ከፍ ያደረገው ለራሷ ክብር (‹‹እኔን የሚያዩኝ ጠላቶቼ ሁሉ እንዳይዘባበቱብኝ›› ከሚለው ንግግሯ በመነሣት ነው እንዲህ የተባለው) ስትል ሊሰገድለት

[50] የመስከረም ገድለ አርሴማ ቍጥር 45፡፡

የሚገባውንና በሞቱ ሞቷን ያጠፋላትን የፍቅር ጌታ በሥጋዌ ጉልበት አልሰግድልህም ትለዋለች፡፡ ይህ ንግግርዋ ደግሞ አፍርብሃለሁ የሚል ሐሳብ ያለው ነው፡፡ ታዲያ እንዴት ነው ይህቺን ሴት ስለ ክርስቶስ ፍቅር ሰማዕት ሆነች ለማለት የሚቻለው?

## የስድብ አፍ

የገድለ አርሴማ ጸሐፊ አርሴማን ‹‹ፈጣሪዋን ለማመስገን ካልሆነ በቀር አፍዋን አትከፍትም፡፡ እግዚአብሔር ለአፍዋ ሕግንና ሥርዓትን ወስኖላታልና፡፡ ከአንደበቷም የመንፈስ ቅዱስ ኃይል አለ፡፡ በላይዋም የመልካም ሴት ውበትን እንደሚያሳምር ያለ የጸጋ ብርሃን ለብሳለች››፣ ‹‹የመጽሐፍን ቃል በምትናገርበት ጊዜ፣ ከቃሏ የጽድቅ ቃል ይወጣል፡፡ በምትሰግድበትና በምትጸልይበት ጊዜም፣ መንፈስ ቅዱስ በላይዋ ላይ በርግብ አምሳል ይጋርዳል››[51] በሚል ቃል ‹‹ቅድስት›› አድርጎ ማስቀመጡ የሁሉም ገድላት ባሕርይ ነውና ምንም አይገርምም፡፡ የሚገርመው ነገር ቅድስት አድርጎ የጻፈላትን ሴት ተሳዳቢ፣ ምራቋን በሰው ፊት ላይ የምትተፋ ከዚህ ባስ ሲል ደግሞ በጥፊ የምትማታ እንደ ሆነች መግለጡ ነው፡፡ ይህንም ደግሞ ዙሪያዋን ያሉት አካላትም በሚገባ የተረዱት መሆኑን ከዚህ በታች በሰፈረው መልኩ አስቀምጦት ይገኛል፤

- <u>ጣዖት አምላኪው የንጉሡ መኰንን</u>፤ ‹‹ከዚህም በኋላ መኰንኑ በዓለም ዳርቻ ሁሉ ክቡርና ኀይለኛ በሆነው ንጉሥ <u>የስድብ ነገር ስታስቀድሚ ከንጉሡ ፍርድ የተነሣ በልብሽና በሐሳብሽ ፍርሃት የለምን?</u> ብሎ ብፅዕት ቡርክት ቅድስት አርሴማን አናገራት፡፡ እኔ ግን የአንቺን ፊት ስለ

[51] መቅድም ቊጥር 17 ተመልከት፡፡ የታኅሣሥ ገድለ አርሴማ ቊጥር 77፡፡

አየሁና ደም ግባትሽን ስለ ወደድሁ የአማርሽና የከበርሽ ቅድስት አርሴማ የሴቶች እመቤት ሆይ ድፍረትሽንና ስድብሽን እታገሣለሁ። አንቺን ከመውደዴ ብዛት ሳልገርፍሽና ሳላስርሽ ወደ ንጉሡ አደርስሻለሁ። እኔም ከሚጣፍጥ ቃል በቀር ምንም የክፋት ነገርን አልናገርሽም››።[52]

- ሰማዕታቱ፤ ‹‹በማይጠቅምህ ለምን ፊጽመህ ትደክማለህ ነገር ግን ስትሰድብህና ስትቈጣህ እንድንሰማ፣ በአንተ ላይ የሚሆነውን ተኣምር እንድናይ አንተ ንገራት…››።[53] ይህን የሚሉት አብረዋት ሰማዕትነት ለመቀበል በዝግጅት ላይ ያሉት ሰማዕታቱ ናቸው። ለዚህ ንግግራቸው ምክንያት ደግሞ ንጉሡ እናንተን እንድተው እና ሰማዕትነቱ ቀርቶባችሁ ወደ ወደዳችሁት እንድትሄዱ ለአርሴማ ደግ ትሆን ዘንድ (እሺ ትለኝ ዘንድ ማለቱ ሳይሆን አይቀርም) ንገሯት ባላቸው ጊዜ ነው። በሰማዕታቱ ንግግር መሠረት አርሴማ የታወቀች ተሳዳቢ ነች ማለት ነው።
- ጣዖት አምላኪው ንጉሥ፤ ‹‹ንጉሡም መለሰ እኔ መልካም ነገር ስናገርሽ አንቺ ግን የስድብን ነገር በእኔ ላይ ታስቀድሚያለሽ።… ንጉሡ መለሰ እንዲህ አላት ቡርክት አርሴማን ይህን ሁሉ ስድብሽን እኔ እቀበለዋለሁ። እኔ እወድሻለሁ አልጠላሽምና።… ስለ ክብርሽ ብዛት ከሩቅ የሚያይ ዓይን ሳለኝ የልብ ዕውር ስትዪኝና ስትሰድቢኝ ይህንን ሁሉ በጸጋ እቀበለዋለሁ። በትዕግሥትም አልፈዋለሁ አላት››።[54]

---

52 የታኅሣሥ ገድለ አርሴማ ቍጥር 6-9 — አጽንዖት የግል።
53 የሰኔ ገድለ አርሴማ ቍጥር 17 - አጽንዖት የግል።
54 የሰኔ ገድለ አርሴማ ቍጥር 24-28 - አጽንዖት የግል።

- ጣዖት አምላኪው ንጉሥ፤ ‹‹… መኳንንቶቹንና ሠራዊቱን ይህቺን ሴት የማደርጋትን መልካም ምክርን እስቲ ንገሩኝ ምከሩኝ። በፊቴ ምራቋን ብትተፋብኝ ጉንጬን ብትመታኝ በፍቅሯ ልቤ ተቃጥሎ ኩላሊቴ ጠፍቷልና እርሷን መጥላት ስለ አልቻልኩ በዚህም ሁሉ አልተቈጣኋትም።… ያን ጊዜም ብታዋርደኝና ብትሰድበኝ ፊቴንም በጥፊ ብትመታኝ እርሷን ስለ ወደድሁ ሰውነቴን አልታወቀኝም››።[55]
- ጣዖት አምላኪው ንጉሥ፤ ‹‹ንጉሡም መለሰ መጻሕፍቶቻችሁ እኛን ኃያላንና ብርቱዎች ወንዶችን ትሰድቡ ዘንድ እንደዚህ ያዛሉን አላት››።[56] ለዚህም ጥያቄ የተሰጠው መልስ ስድብ መሆኑን ማንበብ ምንኛ ልብን ያሳዝን ይሆን?
- ጣዖት አምላኪው ንጉሥ፤ ‹‹ንጉሡም መለሰ ቡርክት አርሴማን ሦስት ጊዜ ሦስት እጅ በላይ ስትሳደቢ እስከ መቼ ድረስ ትዕግስትን እታገስሻለሁ፤ መልክሽንና የፊትሽን ውበት ስለ ወደድሁ አንቺንም ከመውደዴ ብዛትም መንግሥቴን እተውና ከአንቺ ጋር አከተል ዘንድ እፈቅዳለሁ… በእኔና በአማልክቶቼ ላይ ስትሳደቢ በሁሉ ሥራ እንደ ታገስኩሽ አታውቂምን፤ እኔ ግን በእጄ እገድልሻለሁ››።[57] አንባቢው እዚህ ጋር ልብ ይል ዘንድ ተገቢ የሚሆነው ነገር እርሷን ከመውደዱ የተነሣ ተከትሏት መንግሥቱንና ክብሩን ጥሎ ለመሄድ ሲወስን የጌታዬ ፍቅር ገብቶኛል የምትለዋና ለክርስቶስ ሰማዕት (ምስክር) ለመሆን እፈቅዳለሁ ብላ ለሰማዕትነት ራሷን

[55] የሐምሌ ገድለ አርሴማ ቍጥር 34-36 - አጽንዖት የግል።
[56] የሐምሌ ገድለ አርሴማ ቍጥር 55 - አጽንዖት የግል።
[57] የሐምሌ ገድለ አርሴማ ቍጥር 57፡ 61 - አጽንዖት የግል።

ያዘጋጀችው አርሴማ ግን በብዙ ተሳዳቢነት መገለጧ በእውነት አስገራሚ ነው፡፡

ለመሆኑ ምን ምን ብላ ብትሳደብ ነው እንዲህ የተባለችው? ከዚህ በታች ከስድቦቿ ውስጥ ጥቂቱን ለማቅረብ ተሞክሯል፡፡ አንባቢ ሐሳቡን እንዲያገኘው ስለተፈለገ መጽሐፉ እንዳሰፈረው ቃል በቃል ማስፈር ተገቢ በመሆኑ በመጽሐፉ ላይ ያለውን ሐሳብ በትክክል እንዲሰፍር ተደርጓል፤

- ‹‹ገዥውንም ትሰድበው ጀመር፡፡ እንዲህ እያለች፤ አንተ ዝንጉና ወንጀለኛ እነዚህን የጨከኑ የክርስቶስን ሰማዕታት ስለ እኔ በምን ትተዋቸዋለህ…››፡፡[58]
- ‹‹ሰነፍ ንጉሥ ሆይ… አንተ የዓይን ትዕቢተኛ የልብ ስስታም የሆንህ… የተሰደብክ ርኩስ ሆይ››፡፡[59]
- ‹‹ቡርክት ቅድስት አርሴማ ግን፤ በስድብ ቃል እየሰደበችና እየተቆጣች መለሰችለት፡፡ አንተ ውሻ እኔ ከአንተ ጋር አልነጋገረም››፡፡[60]
- ‹‹ቡርክት ቅድስት አርሴማም መለሰችለት፤ በልብህ ውስጥ መልካም ሥራ የለም አንተ የምድር አውሬ ጉድጓድ፣ የትናንሾች ቀበሮዎች መሮጫ፣ የርኩሳን አጋንንት መጠጊያና የጅቦች ማደሪያ ነህ፡፡ ያለ አንተ ማደሪያ የላቸውምና››፡፡ ይህን ያህል የተናገረችው ‹‹ንጉሡም መለሰ እኔ መልካም ነገር ስናገርሽ አንቺ ግን የስድብን ነገር በእኔ ላይ ታስቀድሚያለሽ›› በማለቱ ነው፡፡[61]

---

[58] የኅዳር ገድለ አርሴማ ቊጥር 42፡፡
[59] የሚያዝያ ገድለ አርሴማ ቊጥር 70፡ 73፡ 74፡ 76፡፡
[60] የሰኔ ገድለ አርሴማ ቊጥር 23፡፡
[61] የሰኔ ገድለ አርሴማ ቊጥር 24፡፡

- ‹‹ያን ጊዜ ቡርክት ቅድስት አርሴማ እንደ ወፍ በርራ የስድቡን ቃል ሳይፈጽም የንጉሡን ፊት በጥፊ መታችው፡፡ ዳግመኛም በፊቱ ምራቋን ተፋችበት፡፡ ሰነፍ ሆይ ያፈርህ፣ ወንጀለኛ፣ ጎስቋላ፣ የሰይጣን መልእክተኛ፣ የርኩስ ዲያብሎስ ባሪያ፣ ከአፍህ የሚወጣው ቃልህ ልብን ያደፈርሳል፡፡ የክርፋቱ ሽታ የተላና የሸተተ ነውና››፡፡[62]

እነዚህ ሁሉ ተገቢ ያልሆኑ ድርጊቶችና የስድብ ቃላት የወጡት ቀደም ሲል በተደጋጋሚ እንደተባለው በራሷ ፈቃድ ሰማዕት ለመሆን ከሄደችና ‹‹ቅድስት›› የሚል ማዕረግ ከተሰጠት ሴት መሆኑ ይህቺ ሴት ክርስቲያን ናት ለማለት የሚከብደን ከዚህ በታች ከሰፈሩት የመጽሐፍ ቅዱስ ምንባባት በመነሣት ነው፡፡

- 🕮 ‹‹ለገዦችና ለባለ ሥልጣኖች የሚገዙና የሚታዘዙ፥ ለበጎ ሥራ ሁሉ የተዘጋጁ፥ ማንንም የማይሰድቡ፥ የማይከራከሩ፥ ገሮች፥ ለሰው ሁሉ የዋህነትን ሁሉ የሚያሳዩ እንዲሆኑ አሳስባቸው›› (ቲቶ 3፥1)፡፡
- 🕮 ‹‹ከአፍ የሚወጣ ግን ከልብ ይወጣል፥ ሰውንም የሚያረክሰው ያ ነው፡፡ ከልብ ክፉ አሳብ፥ መግደል፥ ምንዝርነት፥ ዝሙት፥ መስረቅ፥ በውሸት መመስከር፥ ስድብ ይወጣልና›› (ማቴዎስ 15፥18-19)፡፡
- 🕮 ‹‹አሁን ግን እናንተ ደግሞ ቍጣንና ንዴትን ክፋትንም፥ ከአፋችሁም ስድብን የሚያሳፍርንም ንግግር እነዚህን ሁሉ አስወግዱ›› (ቈላስያስ 3፥8)፡፡
- 🕮 ‹‹በትዕቢት ተነፍቶአል አንዳችም አያውቅም፥ ነገር ግን ምርመራን በቃልም መዋጋትን እንደ በሽተኛ ይናፍቃል፤ ከእነዚህም ቅንዓትና ክርክር ስድብም ክፉ አሳብም እርስ

[62] የሐምሌ ገድለ አርሴማ ቍጥር 31፡፡

በርስ መናደድም ይወጣሉ፥ አእምሮአቸውም በጠፋባቸው እውነትንም በተቀሙ፥ እግዚአብሔርን መምሰል ማትረፊያ የሚሆን በመሰላቸው ሰዎች ይገኛሉ። እንደነዚህ ካሉት ራቅ›› (1ኛ ጢሞቴዎስ 6፥4-5)።

- 🕮 ‹‹ክፉን በክፉ ፈንታ ወይም ስድብን በስድብ ፈንታ አትመልሱ በዚህ ፈንታ ባርኩ እንጂ፥ በረከትን ልትወርሱ ለዚህ ተጠርታችኋልና›› (1ኛ ጴጥሮስ 3፥9)።

ንጉሡ ወይም የንጉሡ አገልጋዮች ቢሳደቡ ምንም አይገርምም፤ አይደለም ስድብ ከስድብም የከፋ ነገር ቢያደርጉ (ለእሳት አሳልፈው ቢሰጡ፣ የአውሬ መጫወቻ ቢያደርጉ…) የሚጠበቅባቸው ነው። ምክንያቱም በውስጣቸው ያለው መንፈስ ክፉ በመሆኑ ክፉ ያሠራቸዋልና ነው። ነገር ግን መንፈስ ቅዱስ በውስጧ አለ፤ ከዚህም የተነሣ ከአንደበቷ ፈጣሪን የሚያመሰግን ንግግር እንጂ ክፉ ነገር አያወጣትም፤ እየተባለች የተወደሰች፣ ቅዱሱን ቃል ሰምታና ተቀብላ እርሱ በሚለው መንገድ እሄዳለሁ ብላ የወሰነች ‹‹ቅድስት›› ሴት ጣዖት አምላኪያኑ እንኳ እኔ አልሰደብኩሽም፣ ታገስኩሽ፣… እያሏት እሷ ግን ትእግስት በማጣት ያን ያህል የስድብ ቃላት መወርወሯ ቅድስናዋ የት ገብቶ ይሆን?

## ለቸርነቷ ልማድ ወሰን የለውም

መጽሐፍ ቅዱስ በቸርነቱ ወደር የሌለው እግዚአብሔር መሆኑን ‹‹ቸርነትህና ምሕረትህ በሕይወቴ ዘመን ሁሉ ይከተሉኛል፥ በእግዚአብሔርም ቤት ለዘላለም እኖራለሁ››፣ ‹‹የእግዚአብሔር መንገድ ሁሉ ቸርነትና እውነት ነው። ቃል ኪዳኑንና ምስክሩን ለሚጠብቁ››፣ ‹‹በአንተ ለሚያምኑ በሰው ልጆች ፊት ያዘጋጀሃት ለሚፈሩህም የሰወርሃት፥ ቸርነትህ

እንደ ምን በዛች!›› በማለት ያስነብባል (መዝሙረ ዳዊት 23፥6፤ 25፥10፤ 31፥19)፡፡

ቸር የሚለው ቃል ትርጉም ‹‹የሚሰጥ፣ ለጋስ፣ አባ መስጠት፣ እጀ ሰፊ››[63] የሚል ነው፡፡ ከሰዉ ልጆች መካከል በልዩ ልዩ ቸርነት ውስጥ ሊገለጡ የሚችሉ ሰዎች ሞልተዋል፡፡ ነገር ግን ሰው በመሆናቸው ቸርነታቸው ፍጹም አይደለም፡፡ በአንዱ ቸር ቢሆኑ በሌላው ንፉግ (ስስታም) ሆነው ይታያሉና፡፡ ለቸርነቱ ወሰን የሌለው እግዚአብሔር አምላክ ብቻ በመሆኑ ነው ‹‹ከአንዱ ከእግዚአብሔር በቀር ቸር ማንም የለም›› የተባለው (ሉቃስ 18፥19)፡፡

የገድለ አርሴማ ጸሐፊ ግን ይህን የእግዚአብሔርን ባሕርይ ለፍጡር ለመስጠት እጁ የታዘዘለት ሰው ነው፡፡ ሐሳቡንም ‹‹ቅዱሳን ሰማዕት በምድር እንደሚወርድ እንደ ዝናብ ነጠብጣብ ስለ ሆነው ስለ ሥቃይዋና ግፍዋ ብዛት ይደሰቱባታል፡፡ ለግፍዋ መጠን ቍጥር የለውም፡፡ ለቸርነቷ ልማድም ወሰን የለውም፡፡ የእግዚአብሔር ነገሩንማ ጥበቡ ዕፁብ ድንቅ ነውና›› በማለት አስፍሮታል፡፡[64]

ጸሐፊው በዚህ ስፍራ ወደ ምድር በሚወርድ የዝናብ ነጠብጣብ የመሰለው ስቃይዋና የደረሰባት ግፍ ብሎ ያስቀመጠው ምን እንደ ሆነ ግልጽ አይደለም፡፡ መጽሐፉን ባነበብኩበት ወቅት

---

[63] ባህሩ ዘርጋው ግዛው፣ ዘርጋው ከፍተኛ የዐማርኛ መዝገበ ቃላት (መጋቢት 2006) ገጽ 445፡፡ የኢትዮጵያ ቋንቋዎች ጥናትና ምርምር ማዕከል ዐዲስ አበባ ዩንቨርስቲ፣ የዐማርኛ መዝገበ ቃላት (1993) ገጽ 272፡፡ ተሰማ ሀብተ ሚካኤል ግጽው፣ ከሣቴ ብርሃን ተሰማ የዐማርኛ መዝገበ ቃላት (2005) ገጽ 636፡፡

[64] መቅድም ቍጥር 17 ተመልከት፡፡

በዚህ መጠን የሚገለጽ ሥቃይና ግፍ ቀርቶ ሰማዕትነትን ከመቀበሏ ውጪ የደረሰባት ነገር አላየሁም፡፡ ከዚህ ይልቅ ግን ምንም እንኳ ሥቃይና ግፍ ደረሰባት ቢባልም ሥቃይና ግፍ ስታደርስ የምትታየው እርሷ ናት፡፡ ለዚህም በገድሉ ላይ በሚከተለው መልኩ የሰፈረውን መመልከት ይቻላል፤

- ቡርክት አርሴማም መለሰችለት በጌታዬ ላይ <u>የስድብ ቃል ከምሰማ፤ ልገድልህ በወደድሁ ነበር</u>፡፡ ወይም ሞት በተሻለኝ ነበር፡፡[65]
- ድርጣድስም ልጇን ስታበረታታ በሰማ ጊዜ የእናትዋን የዐጋታንና የቅድስት አርሴማን ጥርሶች ይሰብሩ ዘንድ አዘዘ፡፡ እግዚአብሔር ግን በንጉሥ ድርጣድስ ላይ ኀይልንና ብርታትን ሰጣት፡፡ እርሱ በፀብ ኀይለኛና የታወቀ፣ ፈጽሞም የበረታ ሲሆን፣ <u>ወደ ኋላው ጣለችውና በምድርም ጎተተችው</u>፡፡ ያን ጊዜም ንጉሥ ድርጣድስ በወታደሮቹ ፊት በብፅዕት ቅድስት አርሴማ ስለ ተሸነፈ አፈረ፡፡[66]
- ቡርክት አርሴማም መለሰለችለት፡፡ እንዲህም አለች፤ ፊቷን በጥፊ ወደ መታት ወደዚህ ወንጀለኛ ላይ፣ በእጇ ጣት በትእምርተ መስቀል እያማተበች፣ ፊቷን በጥፊ የመታት፣ ያ ወንጀለኛ ሕያው እንደ ሆነ ወደ ሲኦል ይወርድ ዘንድ፣ ምድርም አፏን ትከፍትና እንደ ዳታንና አንደ አቤሮን ትውጠው ዘንድ ወደ ፈጣሪዋ ለመነች፡፡ እንደ ብፅዕት አርሴማ ቃልም ሆነ፡፡ በሰጠመበትም ላይ ዘጋችው፡፡ ቅድስት አርሴማ ያደረገችውን ይህን ተኣምር ያዩ ከወታደሮች ብዙዎቹ ሸሹ፡፡ ንጉሡም ይሸሽ ዘንድ

[65] የሐምሌ ገድለ አርሴማ ቍጥር 54 - አጽንዖት የግል፡፡
[66] የመስከረም ገድለ አርሴማ ቍጥር 23 - አጽንዖት የግል፡፡

ከዙፋኑ ተነሣ፡፡ ያን ጊዜም ቡርክት አርሴማ ፈገግ አለች፡፡ ቅዱሳን ሰማዕትም ስለ እርስዋ ተደሰቱ፡፡ መላእክት በላይዋ ሲከቡአት አይተዋልና፡፡[67]

በእነዚህ ምንባባት ውስጥ ‹‹ልገድልህ በወደድሁ›› በማለቷ እሷ እየተሰቃየች ሳይሆን ዛቻ እያቀረበችና እየተሳደበች መሆኑን፣ ከዚህም በላይ ንጉሡን መሬት ላይ ጥላ እንደጎተተችው እና የንጉሡን ወታደር ‹‹ሕያው እንደ ሆነ ወደ ሲኦል ይወርድ ዘንድ›› ቃል በማውጣት ‹‹ሕያው እንደ ሆነ›› ምድር እንድትውጠው በማድረግ ደስ እንደ ተሰኘች (‹‹ያን ጊዜም ቡርክት አርሴማ ፈገግ አለች›› ተብሎ ተጽፏልና) የተመለከተ ልባም አንባቢ እንደ ዝናብ ነጠብጣብ የሆነው መከራዋ የቱ ነው? ደግሞ እንዲህ ብዙ የሆነ ሥቃይና ግፍ ሲያደርጉባት ወሰን የለውም የተባለው ቸርነቷ ምንድን ነው? ብሎ ይጠይቃል፡፡

## ወደ ዘላለም ሕይወት የምትመሪ

መጽሐፍ ቅዱስ የዘላለም ሕይወት ስለሚገኝበት መንገድ ሲናገር ‹‹እግዚአብሔርም የዘላለምን ሕይወት እንደ ሰጠን ይህም ሕይወት በልጁ እንዳለ ምስክሩ ይህ ነው፡፡ ልጁ ያለው ሕይወት አለው፤ የእግዚአብሔር ልጅ የሌለው ሕይወት የለውም›› ይላል (1ኛ ዮሐንስ 5፥11-12)፡፡ ቃለ እግዚአብሔር በየትኛውም ስፍራ ከዚህ ውጪ የዘላለም ሕይወት ስለሚገኝበት መንገድ አያሳይም፡፡ ከዚህ ውጪ የሆነ ትምህርት የሚያስተምሩ በፍጡር እንድንታመን በማደረግ እንግዳ ትምህርት ወደ ቤተ ክርስቲያን ያስገቡ መጻሕፍት ናቸው፡፡

[67] የሚያዝያ ገድለ አርሴማ ቍጥር 70-88፡፡

ከእነዚህ መጻሕፍት መካከል አንዱ በሆነው በገድለ አርሴማ ውስጥ ከዚህ የሚከተለው ሐሳብ ይገኛል፤ ‹‹እንዲህም አላት፤[68] ቡርክትና ብፅዕት አርሴማን፣ የረድኤት መንፈስ ትሆኚን ዘንድ እግዚአብሔር አንቺን በእውነት ላከልን፡፡ ወደ ዘላለም ሕይወት የምትመሪና የወንጀለኞችን ነገሥታት ስንፍናን የምትገልጭ፣ በእውነት የምታስተምሪ አንቺ ነሽ፡፡ ከሚከራከሩንና ከሚያሠቃዩን ክፉ ሰዎች፣ አንቺ በገድልና በሰማዕትነት እንደምትበረቺ አሁን አወቅን አላት፡፡… ዳግመኛ ከእነሱ የሚበልጥ ጌርሎስ[69] ተነሥቶ በእውነት ለዘላለም ሕይወት መራሒት የሆንሽ ብፅዕት አርሴማ አንቺ ነሽ፡፡ ስምሽን የሚጠሉ በእግዚአብሔር ዘንድ የተጠሉ ይሆናሉ፡፡ የሚጣፍጠውን ስምሽን የሚያጠፉ በእሳት መካከል እንዳለ ሰም ይጠፋሉ፡፡ ብሩህና የተሸለመውን ፊትሽን የሚመቱ በረግረግ ውስጥ ይወድቃሉ፡፡ ሕያው እንደ ሆኑ ወደ ሲኦል ይወርዳሉ፡፡ በእሳት ምድጃ ይጥሉሽ ዘንድ የሚወዱም በሲኦል በታች

[68] ከዚህ በኋላ ያለውን ንግግር የሚያደርገው ዕድሜው 15 ዓመት የሆነ ጤሜልዮስ የሚባል ዲያቆን ነው፡፡ መጽሐፉ ስለዚህ ታዳጊ ‹‹በዕድሜው ከእነሱ ያንሣል በጥበብና በዕውቀት ግን ይበልጣል፡፡ መንፈስ ቅዱስ በላዩ አድሮአልና›› ይላል፡፡ ከጤሜልዩስ ንግግር በፊት ይህን ማስፈር ያስፈለገው በመቀጠል ዲያቆኑ የተናገረውን ለማጽናትና ወደ ዘላለም ሕይወት የምትመራ መሆኗን የገለጸለት መንፈስ ቅዱስ ነው ለማለት መሆኑ ግልጽ ነው፡፡

[69] አሁን ደግሞ በዕድሜ አንጋፋ የሆነውን የጌርሎስን ምስክርነት ያቀርባል፡፡ ምናልባት እንዲህ ያደረገው ትልቁም ትንሹም የሚመሰክርላት ቅድስት ናት ለማለት ሊሆን ይችላል፡፡ የጌርሎስን ንግግር ለየት የሚያደርገው አርሴማ የዘላለም ሕይወት መሪ እንደ ሆነች መናገሩ ብቻ ሳይሆን እርሷን የሚጠሉ፣ ስሟን የሚያጠፉ፣ ፊቷን የሚመቱ በእሳት ምድጃ ሊጥሏት የሚያስቡ በእግዚአብሔር የተጠሉ፣ እንደ ሰም ቀልጠው የሚጠፉ በረግረግ ውስጥ የሚወድቁና ሕያው እንደ ሆኑ ወደ ሲኦል የሚወርዱ በሲኦል በታች የሚሰጥሙ ናቸው ማለቱ ነው፡፡ ይህ ሁሉ ማስፈራሪያ ያስፈለገው ለምን ይሆን?

ይሰጥማሉ አለ››[70] የሚል ሐሳብ ሲያስተላልፍ ተኣምረ ማርያምም በበኩሉ ‹‹የቀደሙ አባቶች ከሞት ወደ ሕይወት የተሸጋገሩባት ዛሬም ምእመናን ሁሉ በልጅዋ በኢየሱስ ክርስቶስ አምነው በቃል ኪዳንዋ ተማፅነው መንግሥተ ሰማያትን ለመውረስ ተስፋ የሚያደርግዋት ቅድስት ድንግል ማርያም ናት›› በማለት ሌላ የዘላለም ሕይወት መንገድ ያሳያል፡፡[71]

ከእነዚህ መጻሕፍት ውጪ ሌሎችም፤

> ... ለእናንተ ተድላ ደስታችሁ ነውና፤ ለሥጋችሁ መጠበቂያ ለነፍሳችሁ መዳኛ ነውና፡፡ ኀጢአታችሁን የሚያነጻ ለወጣኒነታችሁ ከፍጹምነት መድረሻ ነውና፡፡ ለመርከብ ሰውነታችሁ ጸጥታ ነውና፡፡... ለነፍሳችሁ መድኀኒት ለሃይማኖታችሁ መጽኛ ለሀገራችሁ አጽር ቅጽር ነውና፡፡ ይህ አባታችን [ተክለ ሃይማኖት] ለተበደሉት መማጸኛ ነውና፡፡ ይህ አስተማሪያችን ይህ መድኀኒታችን ይህ አለኝታችን ይህ ነጻ አድራጊያችን ይህ የመንግሥተ ሰማያት ፈለማችን በታረዝን ጊዜ ልብሳችን በተራብን ጊዜ እውነተኛ ምግባችን በተጠማን ጊዜ የሕይወት መጠጣችን በደከምን ጊዜ ምርኩዛችን ነውና፡፡... እነሆ ይህ አባታችን ስለ እኛ ነፍስ ይዋጋልናልና፡፡ ምንድን

70 የሚያዝያ ገድለ አርሴማ ቊጥር 104-111፡፡

71 ትንሣኤ ዘጉባኤ ማተሚያ ቤት፣ ተኣምረ ማርያም (1989) የዘወትር መግቢያውን ይመልከቱ፡፡

ናችሁ? የሚለን የለም፡፡ ድል የሚነሣን የለም፡፡ የመንፈስ ቅዱስ ኃይል አድሮብናልና፡፡[72]

ወንድሞቼ ሆይ ስሙኝ ልንገራችሁ በእዝነ ልቡናችሁም በማስተዋልም አዳምጡኝ ክቡር ገናና የመላእክት አለቃ የሆነ የቅዱስ ሚካኤልን መታሰቢያ አድርጉ፡፡ ፍጻሜ የሌለው ደስታንና የዘለዓለም ሕይወት ታገኙ ዘንድ፡፡[73]

በማለት የዘላለም ሕይወት ዋስትና እኛ ጋር አለን በማለት ሕዝብ እያታለሉ ይገኛሉ፡፡ ይህ ሁሉ ለምንድን ነው? ቢባል ጠላት ዓይናችንን ከጌታችን ላይ አንሥተን ማየት የሚገባንን ሳይሆን ምንም የማይጠቅመንን እንድንመለከት ለማድረግ በሚል የሠራው ሥራ ነው፡፡

## ‹‹መድኀኒታቸው ነሽ››

መጽሐፍ ቅዱስ መድኀኒተ ነፍስ መድኀኒተ ሥጋ የሆነን ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ መሆኑን ‹‹ዛሬ በዳዊት ከተማ መድኀኒት እርሱም ክርስቶስ ጌታ የሆነ ተወልዶላችኋል›› በማለት ይገልጸዋል (ሉቃስ 2፥11)፡፡ ራሱ ጌታችንም መድኀኒት መሆኑን ‹‹ሕመምተኞች እንጂ ብርቱዎች ባለ መድኀኒት አያስፈልጋቸውም ኀጢአተኞችን እንጂ ጻድቃንን ልጠራ አልመጣሁም›› ሲል ገልጦ ነበር (ማርቆስ 2፥17)፡፡ በዓይኖቻቸው ያዩት፣ በእጆቻቸው የዳሰሱትና በእግሩ ሥር ቁጭ ብለው የተማሩት ደቀ መዛሙርቱም የሚመሰክሩት

[72] ተስፋ ገብረ ሥላሴ ማተሚያ ቤት፣ ገድለ ተክለ ሃይማኖት (1984) ምዕራፍ 2 ቊጥር 14-16፡ 20 - አጽንዖት የግል፡፡

[73] ትንሣኤ ዘጉባኤ ማተሚያ ቤት፣ ድርሳነ ሚካኤል በግእዝና በአማርኛ (1989) የኅዳር ድርሳን ገጽ 43፡፡

‹‹እኛም አይተናል አባትም ልጁን የዓለም መድኀኒት ሊሆን እንደ ላከው እንመሰክራለን›› በማለት ነው (1ኛ ዮሐንስ 4፥14)።

ከዚህ ውጪ የሆነ ትምህርት የሚያስተምረው ገድለ አርሴማ ግን ‹‹በአገሮች ሁሉ የገድልሽ ዜና ይታወቃል። በጾምና በጸሎት አንቺን ለሚታመኑ መድኀኒታቸው ነሽ›› በማለት ላይ ይገኛል።[74] ይህን ንግግር ያደረጉት ‹‹ቅዱሳን›› የተባሉቱ ናቸው። ይህም የ‹‹ቅዱሳኑ›› ንግግር ቀደም ሲል ከቀረበውና ከቅዱሱ መጽሐፍ የሚለይ መሆኑ ብቻ ሳይሆን ከአንድ በላይ መድኀኒት እንዳለ በማስመሰል ሰዎችን የሚያሳስት መልእክት ነው።[75] ‹‹እኛ አገራችን በሰማይ ነውና፥ ከዚያም ደግሞ የሚመጣ መድኀኒትን እርሱንም ጌታን ኢየሱስ ክርስቶስን እንጠባበቃለን›› እንጂ ሌላ መድኀኒት አንናፍቅም (ፊልጵስዮስ 3፥20)።

---

[74] የሚያዝያ ገድለ አርሴማ ቍጥር 22።

[75] በርግጥ በቤተ ክርስቲያናችን ትምህርት መድኀኒት የተባሉ ብዙዎች አሉ። ከእነርሱም መካከል ማርያምንና አቡነ ተክለ ሃይማኖትን ማግኘት ይቻላል። ስለዚህ አንድ ሰው ለመዳን ከፈለገ ወደ መድኀኒቱ መምጣት ግድ ይለዋል። በዚህ መሠረት አንድ በሽተኛ ወደ የትኛው መድኀኒት ነው መሄድ የሚኖርበት? ወደ አርሴማ ወይስ ወደ ማርያም ወይስ ወደ ተክለ ሃይማኖት (ትንሣኤ ዘጉባኤ ማተሚያ ቤት፣ ተኣምረ ማርያም (1989) የዘወትር መቅድም ቍጥር 33፡ 34 እና ተኣምር 12 ቍጥር 62 ይመልከቱ። ተስፋ ገብረ ሥላሴ ማተሚያ ቤት፣ ገድለ ተክለ ሃይማኖት (1984) ምዕራፍ 2 ቍጥር 15-16)? መዘንጋት የሌለበት ዋናው ነገር ግን ‹‹የሚያድነው መድኀኒት የተባለውን ሁሉ መሞከር ሳይሆን ትክክለኛውን መድኀኒት ማግኘት ነው፤ አሊያ ‹መድኀኒትን ያበዛሽው በከንቱ ነው፤ መዳንም የለሽም› እንደተባለችው መሆን (ኤርምያስ 46፥11)›› መሆኑን ነው (የአብ ሥራ ግሩም፣ ለተኣምረ ማርያም አትከራከር (2003) ገጽ 39)።

# አፏን ሳመቻት

ጾታቸው ተመሳሳይ ሆኖ አፍ ለአፍ የሚሳሳሙ ሰዎች ቃለ እግዚአብሔር በማይፈቅደው ወሲባዊ ሕይወት ውስጥ ያሉ ሰዎች መሆናቸው መሆኑን ምስክር መጥራት አያስፈልግም። እንዲህ ያለው ድርጊት በተለይም በዚህ ዘመን በአደባባይ ላይ ወጥቶ እንደ ጽድቅ ሥራ የሚሰበክ ከመሆንም በላይ በክርስቲያኖችም መካከል ድጋፍ እያገኘ ያለ ኢ ክርስቲያናዊ ድርጊት ነው።

ቤተ ክርስቲያን ይህን እና ይህን መሰል ድርጊት በአደባባይ የምታወግዝ በመሆኑ በዚህ መልኩ ያላት ጥንካሬ እግዚአብሔር እስከ መጨረሻው እንዲያጸናው ጸሎታችን ነው። ድርጊቱን በአደባባይ ስታወግዝ ግን በጉያዋ የተቀመጠውንና ‹‹ከዚህም በኋላም ብፅዕት አርሴማ የወለደቻትን ተሰናበተቻት። እናቷ ቡርክት አትኖስያናም አፏን ሳመቻት፣[76] ሰውነቷንም ሁሉ ዳሰሰች፣ ዓይኖቿንም አየች፣ በእጆቿም አንገቷን አቀፈች፤ ከዓይኖቿም እንባዋን አፈሰሰች››[77] የሚለውን ገድለ አርሴማንም በማሰብ ጭምር መሆን ይኖርበታል።[78]

---

[76] ገድለ አባ ጊዮርጊስ ዘጋሥጫ እና ገድለ አቡነ በጸሎተ ሚካኤል የተሰኘው መጽሐፍ ላይም ‹‹... የብርሃን እናት እርስዋን እንደ ተዋዳጁ ልጅዋ ትወደዋለች በልብስዋ ትሸፍነዋለች <u>በአፉም ትስመዋለች</u>...›› የሚል ተጽፎ ይገኛል። የዚህኛውን ደግሞ ለየት የሚያደርገው በአፉ ትስመዋለች ተብላ የተገለጸችው ቅድስት ማርያም ስትሆን ተሳሚው ደግሞ አባ ጊዮርጊስ ዘጋስጫ መሆኑ ነው (ገጽ 112 - አጽንዖት የግል)።

[77] የየካቲት ገድለ አርሴማ ቍጥር 16።

[78] በዚህ ሐሳብ ላይ ከአንድ ወንድም ጋር በነበረን ውይይት ወቅት ገድለ አርሴማን እንዲደግፍለት በ2ኛ ነገሥት ምዕራፍ 4 ቍጥር 24 ላይ የሚገኘውንና ‹‹መጥቶም በሕፃኑ ላይ ተኛ አፉንም በአፉ፥ ዓይኑንም በዓይኑ፥ እጁንም በእጁ ላይ አድርጎ ተጋደመበት፤ የሕፃኑም ገላ ሞቀ››

# በአርሴማ ስም... ያደረገ... የዘላለም ሕይወትን ይወርሳል

እንደ ገድላትና ድርሳናት ትምህርት ከሆነ የዘላለም ሕይወትን መውረስ ቀላል ነው፡፡ አንድ ሰው ማድረግ የሚኖርበት ነገር ቢኖር ለዚያ ቅዱስ የተገቡለትን ቃል ኪዳን ማወቅና ከእነርሱም መካከል የሚችለውን መርጦ መተግበር ነው፡፡ እንዲህ ያለው በቃል ኪዳን የዘላለም ሕይወት ማውረስ በገድለ አርሴማ ውስጥ ከዚህ በታች ሰፍሮ ይገኛል፤

- ‹‹ስለ ሰማዕት ቅድስት አርሴማ እንጀራንና ጽዋ ውሃን የሚሰጥ ብፁዕ ነው፡፡ በዚህ ዓለም በሥጋ መዳንን ዕጽፍ ድርብ ያገኛል፡፡ በሚመጣውም ዓለም መልካም ዋጋንና የማያልፍ ሕይወትን ፈጽሞ ያገኛል፡፡ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በወንጌል ቃል በነቢይ ስም፣ ነቢይን የተቀበለ የነቢይን ዋጋ ያገኛል ብሎአልና፡፡ በጻድቅም ስም፣ ጻድቅን የተቀበለ የጻድቅን ዋጋ ያገኛል፡፡ በስሜና በደቀ መዝሙሬ ስም ከታናናሾች ለአንዱ ቀዝቃዛ ጽዋ ውሃ ያጠጣ በሰማያት ዋጋውን አያጣም ብሎአል፡፡ ስለዚህ እኛ ሁላችን ለችግረኞችና ለጦም አዳሪዎች እንራራላቸው››፡፡[79]

---

የሚለውን ቃለ እግዚአብሔር ጠቅሶልኝ ነበር (2ኛ ነገሥት 4፥34)፡፡ ነገር ግን ምንባቡ ከሰላምታም ሆነ ከተቃራኒ ጾታ ግንኙነት ጋር የተያያዘ ምንም ነገር የሌለው መሆኑን ልብ ማለት አስፈላጊ ነው (ገድለ አርሴማ ላይ ያለው ከንፈር ለከንፈር መሳሳም ከሰላምታ ጋር በተያያዘ ነው)፡፡ ከዚያ ይልቅ የሞተው ህፃን ልጅ ለማስነሣት ወደ እግዚአብሔር ከጸለየ በኋላ በልጁ ላይ መተኛቱን ነው የሚነግረን፡፡ ይህንንም ሰባት ጊዜ ያደረገ ሲሆን በሰባተኛው ልጁ ዓይኑን ገልጾ መነሣቱን ማንበብ ይቻላል፡፡ የሞተውን ከማስነሣትም ሌላ ልብ መባል ያለበት ኤልሳዕ የተኛበት ልጅ ሕፃን ልጅ መሆኑን ነው፡፡

[79] መቅድም ቁጥር 25-26 ተመልከት፡፡

- ‹‹... የገድልሽን ዜናና ተኣምርሽን የሚጽፍም የመከራን እሳት አያይም። ስሙ በሕይወት መጽሐፍ ይጻፋል። ከልቡ በኪዳንሽ የታመነ፣ ያጻፈ፣ ያነበበ፣ ዳግመኛም በመታሰቢያሽ ቀን ችግረኛን ያጠገበ፣ የተራቈቱትን ያለበሰ፣ የተጠሙትን ያጠጣ ወይም ለቤተ ክርስቲያን ስንዴንና ዕጣንን የሰጠ ወይም ሥጋ ወደሙን የተቀበለ ዳግመኛም በምስጋናና በማኅሌት፣ በጸሎትና በስግደት፣ ራሱንና አንገቱን ወይም ጎኑንና ጉልበቱን ያስገዛና ያዘነበለ እግዚአብሔር ቃል ኪዳንን እንደሰጠሽና ዛሬም ከመልአክ አፍ በሌሊት ራእይ እንደሰማነው[80] በግልጽ ከአንቺ ጋር ወደ መንግሥተ ሰማያት ያልፋል››።[81]
- ‹‹ዳግመኛም በማይዋሽ ቃሉ ለቡርክት ቅድስት አርሴማ ቃል ኪዳን ሰጣት። በአንቺ ጸጋ ያመኑ ብዙ ሰዎች ይድኑ ዘንድ ማልኩልሽ። የመንገድሽን ድካምና ተጋድሎሽን አስበው ይህንን ዓለም የናቁትን ገድላቸውን እስከሚጨርሱ ድረስ እኔ እጠብቃቸዋለሁ። ድንግልናቸውንም እጠብቃለሁ። እስከ ሽምግልናም አደርሳቸዋለሁ። ዳግመኛም ከክርስቲያን ወገኖች በጸሎትሽና በልመናሽ ቢታመኑ አረማውያንም ቢሆኑ ስለ አንቺ በመንግሥተ ሰማያት አስደስታቸዋለሁ። ያልተጠመቁትንም በሕይወት ውሃ አጠምቃቸዋለሁ››።[82]

---

[80] ይህን የሚናገረው ከሃያ ሰባቱ ሰማዕታት መካከል በዕድሜ አንጋፋ የሆነው ጌርሎስ የተባለው ሰማዕት ነው።

[81] የሚያዝያ ገድለ አርሴማ ቍጥር 115-116።

[82] የነሐሴ ገድለ አርሴማ ቍጥር 30-31።

- ‹‹ጌታችንም[83] ቡርክት አርሴማን ሰላምታ ይገባሻል፡፡ ስለ እኔ ፍቅር ይህንን ዓለምና የከሐዲውን ንጉሥ ፍቅር የናቅሽ ወዳጄና የፈቃዴ ፈጻሚት ሆይ! ዛሬ በልብሽ ውስጥ ያለውን ምኞትሽን አደርግልሽ ዘንድ ምን ትወጃለሽ? አላት፡፡ ቡርክት አርሴማ ቅድስትም መለሰች፤ ወደ ፈጣሪ ወደ እግዚአብሔር እንዲህ አለች፤ ጌታዬና አምላኪዬ ኢየሱስ ክርስቶስ ሆይ በፊትህ ባለሟልነትን ካገኘሁ፤ መታሰቢያዬን ያደረገውን ሁሉ፤ ስሜን የጠራውን፤ ወይም ቤተ ክርስቲያንን በስሜ የሠራውን፣ ወይም የተራበውን ያጠገበ፣ ስለ እኔ የተጠማውን ያጠጣ ወይም የገድሌን መጽሐፍ የጻፈውንና ያጻፈውን ወይም ያነበበና የተረጎመውን ወይም ሰምቶ በልቡ ያሰበውን አቤቱ አንተ መልካምን ዋጋ ክፈለው፤ አለችው፡፡ ከዚህ በኊላም ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በክብር ቃል ቡርክት ብፅዕት ቅድስት አርሴማን በመላእክቶቼ ሁሉ ፊት፣ በእናቴ በማርያም፣ በነቢያትና በሐዋርያት፣ በጻድቃንና በሰማዕታት፣ ዳግመኛም በተመረጡና ንጹሐን በሆኑ ደናግልና መነኰሳት ፊት ከአፌ የወጣውን እንዳልዋሽ ማልኩልሽ አላት፡፡ ቤትሽን (ቤተ ክርስቲያንሽን) የሠራውን ወይም መታሰቢያሽን ያደረገውን፣ ስምሽን የጠራውን ወይም የተራበውን በበዓልሽ ቀን ያጠገበ፣ የተጠማውን ያጠጣ ወይም የተራቄተውን ያለበሰ ወይም ከንቱ ከሆነ ምስጋና ሥጋውን በማራቅ በፍርሃትና በመንቀጥቀጥ በበዓልሽ ቀን የዘመረውንና ያመሰገነውን፣ በገድልሽ ታምኖ የጠጣውንና የታጠበውን ወይም በመንገድሽ ድካም

[83] እንደ ገድሉ ትረካ እዚህ ቦታ ላይ ጌታችን የመጣው እሷ ሰማዕትነትን የመቀበያዋ የመጨረሻ ሰዓት ላይ በመድረሷ ምክንያት መጸለይ በጀመረችበት ሰዓት ነው፡፡

ይህንን ዓለም የናቀውን እኔም የልቡን ምኞት እፈጽምለታለሁ፡፡ ያለ ጉስቁልና በንጽሕና ድንግልናውን እጠብቅለታለሁ፡፡ በመንግሥተ ሰማያትም እንደ አንቺ የክብር አክሊልን እሰጠዋለሁ፡፡ ሥዕልሽን አሥሎ በቤትሽ ውስጥ ቢያስቀምጥ ወይም በክብርና በንጽሕና በቤቱ ቢያስቀምጥ ወይም የሰገደና የተማለደ ወይም በላዩ መልካም የሆነ የናርዶስ ሽቶ የረጨ እኔ ልብን የሚመስጥ ጣፋጭ ከሆነ ገነት መዓዛ አሸተዋለሁ፡፡ ወንድ ልጁንና ሴት ልጁን በአንቺ ስም የጠራውን በመንግሥተ ሰማያት የበለጠና የከበረ ስምን እኔ እሰጠዋለሁ፡፡ ዕጣንንና ቊርባንን ወይም መብራትን ቢያበራ እኔ በሰማያት መብራትን አበራለታለሁ፡፡ ለቤተ ክርስቲያንሽ ልብስን ወይም መጋረጃን ቢሰጥ እኔ በሞቱ ቀን የብርሃንን ልብስ አለብሰዋለሁ፡፡ እንደ መላእክት ክንፎችን ከጎኖቹ አበቅላለሁ፡፡ ያለጭንቅ የእሳት ባሕርን ይሻገራል፡፡ እንደ ወፍም ይበራል፡፡ የገድልሽን መጽሐፍ በጥንቃቄ ቢጽፍና ቢያጽፍ ወይም በምድር ሀብት ይልቅ በገንዘቡ የገዛውን የጽድቅ ብርሃን በሆነ ዓምድ በወርቅ ቀለም ከስምሽ ጋር ስሙን እኔ እጽፋለሁ፤ አላት፡፡ ጌታችን ቡርክት አርሴማን መጀመሪያ እስከ ኋላ ያሰብናቸው ሁሉ በመንግሥተ ሰማያት በግልጽ ይለፉ አላት፡፡ ቡርክት ቅድስት አርሴማም አሜን አለች፡፡ እኛም እንደ እርስዋ አሜን ማለት ይገባናል››፡፡[84]

ከዚህ በላይ በሰፈሩትና ገድለ አርሴማ በየስፍራው በሚያስነብባቸው ልዩ ልዩ ቃል ኪዳኖች በአርሴማ በኩል መዳን

[84] የመስከረም ገድለ አርሴማ ቅጥር 37-44፡፡

የፈለገ ሰው ምን ያህል አማራጭ መንገዶች እንዳሉት በቀላሉ ይመለከት ዘንድ ከዚህ በታች ‹‹የመዳኛ መንገዶቹን›› ለይቶ በማውጣት ለማሳየት ተሞክሯል፤

1. እንጀራንና ጽዋ ውሃን የሚሰጥ
2. ከልቡ በኪዳንሽ የታመነ
3. በመታሰቢያሽ ቀን ችግረኛን ያጠገበ፣ የተጠሙትን ያጠጣ፣ የተራበውን ያጠገበ
4. ሥጋ ወደሙን የተቀበለ
5. ለቤተ ክርስቲያን ስንዴንና ዕጣንን የሰጠ
6. በምስጋናና በማኅሌት፣ በጸሎትና በስግደት፣ ራሱንና አንገቱን ወይም ጎኑንና ጉልበቱን ያስገዛና ያዘነበለ
7. በእርሷ ጸጋ ያመኑ
8. የመንገድሽን ድካምና ተጋድሎሽን አስበው ይህንን ዓለም የናቁትን
9. ከክርስቲያን ወገኖች በጸሎትሽና በልመናሽ ቢታመኑ
10. አረማውያንም ቢሆኑ ስለ አንቺ በመንግሥተ ሰማያት አስደስታቸዋለሁ
11. ስሟን የጠራውን
12. ቤተ ክርስቲያንን በስሟ የሠራውን
13. የገድሏን መጽሐፍ የጻፈውንና ያጻፈውን ወይም ያነበበና የተረጐመውን ወይም ሰምቶ በልቡ ያሰበውን
14. ከንቱ ከሆነ ምስጋና ሥጋውን በማራቅ በፍርሃትና በመንቀጥቀጥ በበዓልሽ ቀን የዘመረውንና ያመሰገነውን
15. የተራቈተውን ያለበሰ
16. በገድልሽ ታምኖ [ጠበል] የጠጣውንና የታጠበውን
17. በመንገድሽ ድካም ይህንን ዓለም የናቀውን

18. ሥዕልሽን አስሎ በቤትሽ ውስጥ ቢያስቀመጥ ወይም በክብርና በንጽሕና በቤቱ ቢያስቀምጥ ወይም የሰገደና የተማለደ ወይም በላዩ መልካም የሆነ የናርዱስ ሽቶ የረጨ
19. ወንድ ልጁንና ሴት ልጁን በአንቺ ስም የጠራውን
20. ዕጣንንና ቊርባንን ወይም መብራትን ቢያበራ
21. ለቤተ ክርስቲያንሽ ልብስን ወይም መጋረጃን ቢሰጥ

መጽሐፍ ቅዱስ የመዳኛ መንገዱ አንድ እሱም ጌታችን መሆኑን አስረግጦ ሲናገር (ዮሐንስ 3፥16። 1ኛ ዮሐንስ 5፥11) ገድለ አርሴማ ግን ሃያ አንድ አማራጭ መንገዶችን ይዞ መቅረቡ በርግጥም ከቅዱሱ መጽሐፍ ጋር የማይስማማ ተረት መሆኑን አሳይቷል።

ገድሉ ገንዘብ ያለውና የቻለ ድሆችን አብልቶና አጠጥቶ አልብሶም ጭምር ገነትን መውረስ እንደሚችል ሲገልጽ ገንዘብ የሌለው ደሃ ደግሞ ምንም ወጪ የማያስወጡትን በመምረጥ (የልጁን ስም በአርሴማ ስም በመሰየም ወይም የአርሴማን ስም በመጥራት ወይም የገድሏን መጽሐፍ በመጻፍ ወይም በማንበብ ወይም ሰምቶ በልቡ በማሰብ) ወደ እግዚአብሔር መንግሥት ሰተት ብሎ የመግባት መብት አለው ይላል።

ከእነዚህ ሁሉ ለየት የሚለውና አስገራሚው ደግሞ በተራ ቊጥር 10 ላይ የሰፈረውና ‹‹አረማውያንም ቢሆኑ ስለ አንቺ በመንግሥተ ሰማያት አስደስታቸዋለሁ›› የሚለው ነው። በዚህ ስፍራ ላይ የተገለጹት ሰዎች ክርስትናን የማያውቁ፣ ንስሐ በመግባት ጌታችንን የማያምኑ ሆነው ሳለ ስለ አርሴማ በመንግሥተ ሰማያት ደስታን እንደሚያገኙ መነገሩ ቅዱሳን አባቶች ያስተማሩትን ትምህርት ከንቱ የሚያደርግ በመሆኑ

የቤተ ክርስቲያንን አንገት የሚያስደፋ ነው፡፡ ወገኖቼ ከዚህ በላይ የክርስቶስን ሞት መናቅና ደሙን ከንቱ ማድረግስ ከወዴት ይመጣ ይሆን? ይህ መጽሐፍ ‹‹የተረገመ ወንጌል›› መባልስ አይገባው ይሆን?

ይህን መሰሉን ትምህርት ድጋፍ እንዲሆን ተብሎ የሚጠቀሰው ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ለደቀ መዛሙርቱ የተናገረው ‹‹እናንተን የሚቀበል እኔን ይቀበላል፥ እኔንም የሚቀበል የላከኝን ይቀበላል፡፡ ነቢይን በነቢይ ስም የሚቀበል የነቢይን ዋጋ ይወስዳል፥ ጻድቅንም በጻድቅ ስም የሚቀበል የጻድቁን ዋጋ ይወስዳል›› የሚለውን ነው (ማቴዎስ 10፥40-41)፡፡[85]

ይህ ምንባብ ግን እነርሱ እንደሚሉት ያለ ትርጉም የሌለው መሆኑን ለመረዳት ሙሉውን ምዕራፍ መመልከት ጠቃሚ ነው፡፡[86] ከቍጥር 1 ጀምሮ ስናነብ፣ ጌታ ዐሥራ ሁለቱን ደቀ መዛሙርቱን በስማቸው ጠርቶ፣ በበሽታና በእርኩሳን መናፍስት ላይ ሥልጣንን ሰጥቶ *‹‹መንግሥተ ሰማያት ቀርባለች ብላችሁ ስበኩ››* (ቍ. 7) ብሎ ላካቸው፡፡ ወደማን መሄድ እንደሚገባቸው፣ ምን ማድረግ እንዳለባቸው፣ ምን ዓይነት ነገሮች ሊያጋጥሟቸው እንደሚችሉ እና የመሳሰሉትን ጉዳዮች በተመለከተ የተለያዩ መመሪያዎችን ሰጣቸው፡፡ ምንም ዓይነት ስንቅም ሆነ ትጥቅ እንዳይዙ አዘዛቸው (ቍ. 10)፡፡ በዚህ

---

[85] ይህን ጥቅስ ለተዝካር ድጋፍ ይሆናቸው ዘንድ የሚያቀርቡት መሆኑን ለመመልከት ‹‹ሰማንያ አሐዱ በእግዚአብሔር ቃል ሲመዘን›› የሚለውን መጽሐፍ ‹‹ለሞተ ሰው ተዝካር ማውጣት አትተው›› የሚለውን ርዕስ ይመልከቱ፡፡

[86] ከዚህ በታች የሰፈረው ጽሑፍ የተወሰደው ‹‹ሰማንያ አሐዱ በእግዚአብሔር ቃል ሲመዘን›› ከተሰኘውና በ2010 ከታተመው መጽሐፍ ከገጽ 105-106 ላይ ነው፡፡

ሁኔታ ከላካቸው በኋላ ‹‹እናንተን የሚቀበል እኔን ይቀበላል›› (ቊ. 40) አለ፡፡ በርግጥም ጌታ የላከውን ደቀ መዝሙር የጌታ ደቀ መዝሙር ነው ብሎ እንደ ደቀ መዝሙር የተቀበለ ሰው፣ ደቀ መዝሙሩ አገልግሎ የሚያገኘውን ዋጋ ያገኛል ማለት ነው (ቊ. 41)፡፡ ከዚህ በመነሣት ነው ጌታ ‹‹ከእነዚህ ከታናናሾቼ ለአንዱ ቀዝቃዛ ጽዋ ውሃ ብቻ በደቀ መዝሙሩ ስም የሚያጠጣ፣ እውነት እላችዋለሁ፣ ዋጋው አይጠፋበትም›› ያለው፡፡ ‹‹ከእነዚህ›› የሚለው ቃል የሚያመለክተው ደቀ መዛሙርቱን ብቻ ነው፡፡ ቀዝቃዛ ጽዋ ውሃ የሚሰጠውም ለደቀ መዛሙርቱ እንጂ ለሌሎች ድሆች አይደለም (ማርቆስ 9÷41)፡፡[87] ቀዝቃዛ ጽዋ የሰጠውም ቢሆን የሚያገኘው ጽድቅና ቅድስና ወይም የምልጃ ሥራ አልያም የዘላለም ሕይወትና መዳን ሳይሆን ያንን ያደረገበትን ዋጋ ነው፡፡

ልባቸው ለቃሉ እውነት ለመሸነፍ ፈቃደኛ ያልሆኑ ሰዎች መጽሐፉ ‹‹የክርስቶስ ስለሆናችሁ በስሜ ጽዋ ውሃ የሚያጠጣችሁ ዋጋው እንዳይጠፋበት እውነት እላችኋለው›› (ማርቆስ 9÷41) የሚለውን እያነበቡ ‹‹ጴጥሮስን የት አግኝተን ጳውሎስን የት አግኝተን ነው የምንሰጠው?››[88] ዓይነት ጥያቄ ያቀርባሉ፡፡

ጴጥሮስም ሆነ ጳውሎስ ሰዎች እንደመሆናቸው መጠን በዚህ ምድር ላይ ሊቆዩ የሚችሉት ለተወሰነ ጊዜ ብቻ ነበርና አሁን ልናገኛቸው አንችልም፡፡ ነገር ግን እግዚአብሔር በእነዚህ ባሪያዎቹ ለሕዝቡ እንዲደርስ ሲያደርግ የነበረው የጽድቅ ቃሉ

---

[87] ራእይ አሳታሚ፣ የዐዲስ ኪዳን ማብራሪያ (2006) ገጽ 123 እና 166፡፡
[88] ዘበነ ለማ (መምህር)፣ የአሜሪካን ፕሮቴስታንቶች ድንግል ማርያምን ተቀበሉ የስብከት ቪሲዲ፡፡

(ወንጌል) አሁንም እየተሰበከ ነው፣ ማለትም የጴጥሮስንና የጳውሎስን ሥራ እየሠራ ያለ የክርስቶስ ደቀ መዝሙር አሁንም አለ ማለት ነው። ስለዚህ እርሱ የክርስቶስ ደቀ መዝሙር በመሆኑ የሚደረግለት አነስተኛው መስተንግዶ በእግዚአብሔር ዘንድ ዋጋ እንዳለው ማወቅ አስፈላጊ ነው።

## ኑ እናመስግናት

ልበ አምላክ ቅዱስ ዳዊት ‹‹ምስጋና የሚገባውን እግዚአብሔርን እጠራለሁ፥ ከጠላቶቼም እድናለሁ›› በማለት ‹‹ምስጋና የሚገባውን›› እግዚአብሔርን ሲያመሰግን ሃያ አራቱ ሽማግሌዎች በዙፋን ላይ በተቀመጠው ፊት ወድቀውና በዙፋኑ ፊት አክሊላቸውን እያኖሩ ‹‹ጌታችንና አምላካችን ሆይ፥ አንተ ሁሉን ፈጥረሃልና ስለ ፈቃድህም ሆነዋልና ተፈጥረውማልና ክብር ውዳሴ ኃይልም ልትቀበል ይገባሃል›› በማለት ያመሰግኑታል (መዝሙረ ዳዊት 18፥3። ራእይ 4፥10-11)።

የገድለ አርሴማ ጸሐፊ ግን ከዚህ በታች በሰፈረው መልኩ ፍጡር ሲያመሰግን ይታያል፤

- ‹‹ለብፅዕት ቅድስት አርሴማ ክብር ይገባታል። ትውልድና ፍጥረት ሁሉ ያድንቁአታል››።[89]
- ‹‹በቅዱሳን ሰማዕት ማኅበርና በገነት በሮች ፊጽማ ትመሰገናለች››።[90]
- ‹‹ስለዚህ ነገር ብፅዕት ሰማዕት አርሴማን ኑ እናመስግናት፤ እግዚአብሔር ከእናቷ ማኅፀን ጀምሮ አመስግኖአታልና። ኑ ከፍ ከፍ እናድርጋት፤

[89] መቅድም ቁጥር 10 ተመልከት።
[90] መቅድም ቁጥር 12 ተመልከት።

እግዚአብሔር ከፍ ከፍ አድርጓታልና፡፡ ኑ! እናክብራት እግዚአብሔር አክብሯታልና››፡፡[91]

- ‹‹… ፈጣሪያቸውን እግዚአብሔርንም አመሰገኑት፡፡ ቡርክትና ብፅዕት ቅድስት አርሴማንም አመሰገኗት፤ አከበሯትም፡፡ ፈጽመውም ከፍ ከፍ አደረጉአት››፡፡[92]

በተለይ በመጨረሻ ላይ በቀረበው ምስጋና ክፍል ላይ አርሴማ ክብርና ምስጋና የወሰደችበት ምክንያት ምን እንደ ሆነ ግልጽ አይደለም፡፡ ታሪኩ ላይ እንደ ሰፈረው ለሰባት ቀናት ምግብ ባለ መመገባቸው ምክንያት ተርበው በነበረበት ሰዓት በእሷ መሪነት ጸሎት አቀረቡና ሰማያዊ ኅብስትና ጽዋ መጣላቸው፡፡ እሱንም ‹‹በሉ ፈጽመውም ጠገቡ ጠጡ ረኩም››፡፡ ከዚህ በኋላ ‹‹ፈጣሪያቸውን እግዚአብሔርንም አመሰገኑት››፡፡ እግዚአብሔርን ባመሰገኑት በዚያው ምስጋና እሷን ማመስገናቸውን ምንባቡ ያሳያል፡፡ እግዚአብሔር በርሃባቸው ደርሶ ስለ መገባቸው ያመሰገኑት ሲሆን አርሴማን ያመሰገኑበት ምክንያት ግን ግልጽ አይደለም፡፡ አንዳንዶች ለፈጠሪ የባሕርይው የሆነ ለቅዱሳን ደግሞ የጸጋ ምስጋና ነው የምናቀርብላቸው ይላሉ፡፡ ለአርሴማና ለእግዚአብሔር ምስጋና በቀረበበት በዚህ ምንባብ ውስጥ የጸጋ እና የባሕርይ ተብሎ ሊከፈል የሚችለው የትኛው ይሆን? በሁለቱ ምስጋናዎች መካከል ምንም ዓይነት ልዩነት የሌለ መሆኑ አንዱን ምስጋና ለፈጣሪና ለፍጡር በመስጠት የማጋራት ሥራ መሠራቱን መመልከት ይቻላል፡፡

---

[91] መቅድም ቍጥር 31 ተመልከት፡፡

[92] የግንቦት ገድለ አርሴማ ቍጥር 64፡፡

ከዚህ በፊት እንደሰፈረው አርሴማና ሰማዕታቱ ለቀናት ተርበው ከነበሩበት ነጻ ያወጣቸው የእግዚአብሔር በረከት ነው። ምግቡን የላከላቸው እርሱ ነውና። የገድሉ ጸሐፊ ይህን ታሪክ ሲዘጋው ግን ‹‹ቡርክትና ብፅዕት ቅድስት አርሴማ ሆይ ለዘላለሙ ከማያልቀው በረከትሽ ለሁላችን ሕዝበ ክርስቲያን እንዲሁ አጥግቢን አሜን›› በማለት የበረከት ምንጭ አድርጎ የሚያስቀምጠው ፈጣሪን ሳይሆን ፍጡሯን ነው።[93] ይህ ደግሞ ‹‹ምግባቸውን በየጊዜው ትሰጣቸው ዘንድ እነዚህ ሁሉ አንተን ተስፋ ያደርጋሉ›› ተብሎ ከተጻፈው ውጪ የሆነ እንግዳ ትምህርት መሆኑ ግልጽ ነው (መዝሙረ ዳዊት 103፥27)።

## ማርያምና አርሴማ

የገድላት ጸሐፊዎች አንዱን ቅዱስ ከሌላው የተለየ እና ታላቅ ለማድረግ ልዩ ልዩ ዘዴዎችን ይጠቀማሉ።[94] እንዲህ ሲያደርጉ ግን የሌላውን ቅዱስ ስም ሳያነሡ የገድሉን ባለቤት ብቻ ታላቅነት በማጉላት ነው። አብዛኛው ገድላት ይህን መንገድ ሲከተሉ ማርያምን በተመለከተ ግን ከሁሉ የበላይ መሆኗን ሳያወሱ አያልፉም። ገድለ አርሴማ ከእነዚህ ገድላት የተለየ ይመስላል። እንደ ሌሎቹ ገድላት ሁሉ አርሴማን ከሁሉ የበላይ እንደ ሆነች በተደጋጋሚ አስፍሯል። ከዚህ ጋር በተያያዘ ምንም እንኳ ማርያም ከእርሷ በላይ እንደ ሆነች ቢያስነብብም ማርያምንና አርሴማን ለማወዳደር ሲሞክርም ይታያል፤

- ‹‹የብፅዕት ሰማዕት አርሴማን ዜና የሰማ ፍጥረት ሁሉ ከፍ ከፍ አደረጋት። ብዙዎች ሴቶች ልጆች የዚህን

[93] የግንቦት ገድለ አርሴማ ቍጥር 64።

[94] በዚህ መጽሐፍ በግርጌ ማስታወሻ ቍጥር 7 ላይ የሰፈረውን የመጨረሻውን አንቀጽ ይመልከቱ።

ዓለም ሀብት ገዙ። ነገር ግን ኀይልንና ተኣምርን አላደረጉም። ብፅዕት አርሴማ ግን መልካም መሥራትን ሁሉ አበዛች። ከእመቤታችን ከድንግል ማርያም በቀር፣ ከሴቶች ሁሉ ትበልጣለች እያሉ እርስዋ ለጥበብና ለትዕግስት ተዘጋጅታለችና››።[95]

- ‹‹[አርሴማ] ከፀሐይና ከጨረቃ ታምራለች። በሰማያት ከሚኖሩት ፍጥረት ሁሉ ትበልጣለች። በምድርም ከሚኖሩት ቢሆን፤ ከዚህም ሁሉ ይልቅ ደም ግባት፣ በባለሟልነት፣ በልዕልና፣ በክብር፣ ከእመቤታችን ከእመቤትዋ ማርያም በታች የሚተካከላት የለም። እርሷ [ማርያም] ጌታችን፣ አምላካችን፣ መድኀኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስን በመውለዷ ከፍጥረት ሁሉ ከሴቶችም ሁሉ ትከብራለች››።[96] በዚህ ስፍራ ላይ የማርያም የመላቅ ምክንያት ጌታችንን በመውለዷ ነው እያለ ይመስላል።[97]
- ‹‹… የብፅዕት ቅድስት አርሴማ የፊት ውበት ዕፁብ ድንቅ ነውና። በዚያን ዘመን በዚያ አገር ውስጥ ከፊትም ሆነ ከኋላዋ በመልክና በውበት የሚመስላት የለም። ይህን ዓለም በመናቅ ክርስቶስን ከተከተሉት ቅዱሳት ደናግል አንስት እመቤትና የእውነት ፀሐይ ከሆነችው ከእመቤታችን ማርያም በቀር››።[98] በዚህ ስፍራ ላይ ደግሞ ቅድስት ማርያም ከአርሴማ ልቃ የተገኘችው በውበት መሆኑን ነው ሊያሳየን የሞከረው።

---

95 መቅድም ቍጥር 19 ተመልከት።

96 መቅድም ቍጥር 33 ተመልከት።

97 በድርሳነ ኢያቄም ወሐና ላይም በተመሳሳይ ሁኔታ ‹‹ድንግል ማርያምን በመውለዷ [ምክንያት ሐና] ከሴቶች ሁሉ ትበልጣለች›› ተብሎም ተጽፏል (ተስፋ ሚካኤል ታከለ (መምህር) (ተርጓሚ)፣ ድርሳነ ኢያቄም ወሐና (2007) ገጽ 27)።

98 የኅዳር ገድለ አርሴማ ቍጥር 17።

- ‹‹ቡርክት ቅድስት አርሴማን ከፍጥረቱ ሁሉ እመቤት ከድንግል ማርያም በቀር፣ ከሴቶች ልጆች ሁሉ የሚመስላት የለም…››፡፡[99]

ከዚህ በተለየ ሁኔታ በሌሎች ነጥቦቹ ላይ ከማርያም ጋር ሊያፎካክራት የሚሞክርበት ምንባባት አስቀምጦ ይታያል፡፡ ለአብነትም፤

- ማርያም ንግሥተ ሰማይ ወምድር የምትባል ሲሆን[100] የገድለ አርሴማ አዘጋጅም ‹‹አንቺ በእውነት ንግሥትና ክብርት ነሽ፡፡… በመንግሥተ ሰማያትም ትነግሻለሽ የዘላለም ሕይትንም ትወርሻለሽ›› በማለት ከማርያምም ሌላ ንግሥት ልትባል ይገባታል የሚላትን አርሴማን ሲያስቀምጥ ይታያል፡፡[101]
- አንዳንዶች በዐሥራ አምስት ዓመቷ እንደ ወለደች ሲያስነብቡ[102] ገድለ አርሴማ ደግሞ ‹‹ዐሥራ አምስት ዓመት ከሆናት በኋላ ከሐዲውን ንጉሥ ዲያቅልጥያኖስን ሰይጣን አነሣሣው፡፡… ንጉሥም ሥዕሏን በአየ ጊዜ ፈጽሞ ተደሰተ፡፡ ስለ ሠርጉ ወደ እርሱ እንዲመጡ ሕዝቡን ይጠሩአቸው ዘንድ ወደ ነገሥታቱና ወደ መኳንንቱ ላከ›› በማለት ዐሥራ አምስት ዓመት ሲሆናት ንጉሥ ለጋብቻ ጋብዟት የነበረ ቢሆንም እርሷ ግን

---

[99] የነሐሴ ገድለ አርሴማ ቊጥር 29፡፡
[100] አንዱ ዓለም ዳግማዊ (መምህር)፣ ወላዲተ አምላክ በነገረ ድኅነት (ዐዲስ አበባ፣ ሚያዝያ 1998) ገጽ 347፡፡
[101] የሚያዝያ ገድለ አርሴማ ቊጥር 115፡ 117፡፡
[102] አያሌው ታምሩ (አለቃ)፣ ወላዲተ አምላክ በኢትዮጵያ (ዐዲስ አበባ፣ ሐምሌ 1979) ገጽ 44፡፡

ፈቃደኛ አለመሆኗንና ይህም ታላቅ ውሳኔና ትክክለኛ ርምጃ መሆኑን ለማሳየት ይሞክራል።[103]

- በቤተ ክርስቲያን ትምህርት ማርያም ሰማያዊ ምግብና ሰማያዊ መጠጥ እየተመገበችና እየጠጣች ያደገች ነች።[104] ይህም ከሌሎች ቅዱሳን እንድትለይ የሚያደርጋት ይሆናል። ገድለ አርሴምም ከማን አንሼ በሚል መንፈስ ይመስላል አርሴማና በዙሪያዋ የነበሩ ሰዎች[105] ሰማያዊ ምግብ ተመግበዋል ለማለት የሚከተለውን አስፍሮታል ይገኛል። ‹‹ያን ጊዜም[106] ብርሃንና ብሩህ የሆነ የደመና ምሰሶ ወረደ። በእሥር ቤት ውስጥ ለአሉት ሁሉ አበራላቸው። በውጭም ለአሉት የፀሐይ ነፀብራቅ ታያቸው። በመላእክትም እጅ እንጀራን አወረደላቸው። እነሱም ብርናኤልና አቅናኤል ናቸው።[107] በእጃቸው ኅብስተ መና ይዘው ነጭና የጠራ

---

[103] የኅዳር ገድለ አርሴማ ቁጥር 18።

[104] ትንሣኤ ዘጉባኤ ማተሚያ ቤት፣ ወንጌል ቅዱስ ንባቡና ትርጓሜው የሉቃስ ወንጌል ምዕራፍ 1 ቁጥር 27 ማብራሪያ (ዐዲስ አበባ፣ 1997)።

[105] በዚህ ስፍራ ላይ ምንም እንኳ ሰማዕታቱ ከአርሴማ ጋር አብረው ሰማያዊውን ማዕድ የተቋደሱ ቢሆንም ማዕዱ የመጣበት ምክንያት አርሴማ መሆኗን በሁለት መንገድ ሰፍሯል። መንገዶቹም፤ አንደኛው ሰማዕታቱን እንጸልይ ስትላቸው አንቺ ጸልይልን በማለታቸውና እሷም በመጸለይዋ ምክንያት የመጣ ነው በሚለው ሲሆን ሁለተኛው ደግሞ ከእግዚአብሔር እኩል ምስጋናን በመቀበሏ ነው።

[106] በአርሴማ መሪነት ቅዱሳኑ ሲጸልዩ ነበርና ነው ‹‹ያን ጊዜም›› የተባለው።

[107] መሪ ራስ አማን በላይ እነ ጥምጥማኤል (ፀብኡለዓለም - ጸላኤ ሰብእ) እነ ሰደድኤል (አስታደድ - አዳል ሞቴን) እነ አጥያኤል (አስተማስል - ጠቋሬ አረሩ ጨዋር) እነ ሶርቅናኤል (ፀባጤ - አብደርቃድ) እነ ቆስጤ ቤኤልዘቡል (ቆስጤ ቤልሆር - አዶየ አዶከብሬ) እነ ሎግያ (ሌጌዎን - ጉለም ሽት) እነ አዛዝኤል (ጸላኤሰብእ - ሻንቆ) እና መሰል መናፍስትን በጻፉበት ስፍራ ላይ ብርናኤልን አስቀምጠውታል (አማን በላይ (መሪ ራስ) መጽሐፈ ብሩክ - ዢንሸዋ ቀዳማዊ (2000) ገጽ 119-120)።

የገነት ውሃ ያለበት የወርቅ ጽዋም በመካከላቸው ነበር፡፡ እነዚህም እንጀራዎች ያን ጊዜውን እንደ ተጋገረ የሞቁ ነበሩ፡፡ እንደ ፀሐይ መልክ የሚያበሩ ነበሩ፡፡ እንደ ነጭ በረዶም የፀዱ ነበሩ፡፡ ሽታቸውም ልብን ይሰልባል፡፡ ሳይበሉት ያጠግባል፡፡ ከጣዕሙና ከመልኩም መዓዛው ብዛት ሳይጠጡት ፈጽሞ ያረካል፡፡ ከእርሱም ይበሉ ዘንድ የሚወዱ ከግርማው ከፍታ ከመልካም መዓዛው የተነሣ ፈጽመው አደነቁ፡፡ ይህንስ አንቁረሰው፣ አንክፈለው ተባባሉ፡፡ በዓይናችን እንየው፤ በእጃችን እናንቀሣቅሰው እንጂ፡፡ እንደ መብረቅ ብርሃን በፊታቸው የሚያበራና ልባቸውንም የሚያስደስት ሆኖአልና፡፡ ካህን ኢያሴኖስም በዚህ ኅብስት ላይ የምስጋና ጸሎት አደረገ፡፡ ከዚህም ኅብስት ሁሉም ተቀበሉ በሉ ፈጽመውም ጠገቡ ጠጡ ረኩም ብዙ ቍርስራሾችም አተረፉ፡፡ ፈጣሪያቸውንም እግዚአብሔርን አመሰገኑት፡፡ ቡርክትና ብፅዕት ቅድስት አርሴማንም አመሰገኑአት አከበሩአትም ፈጽመውም ከፍ ከፍ አደረጓት፡፡ የተረፈው የኅብስት ቍርስራሽና ጥሩ

በጸሐፊው አቀራረብ መሠረት እነዚህና ሌሎችም ስሞች የተቀመጡት ከቅዱሳን ዝርዝር ውስጥ ሳይሆን ከርኩሳን መናፍስት ነው፡፡ የተዘረዘሩትም ቢሆኑ የሚታወቁት በርኩሳን መናፍስትነታቸው መሆኑ ግልጽ ነው፡፡ ይህ የሚያሳየው ደግሞ ለአርሴማና ለሰማዕታቱ ተገለጡ የተባሉቱ ቅዱሳን መናፍስት ሳይሆኑ ርኩሳን መናፍስት ናቸው ማለት ነው፡፡ ከዚህም ሌላ ደግሞ ማርያምን ሲመግብ የነበረው መልአክ አንድ መልአክ እርሱም ‹‹ፋኑኤል›› ሲሆን (ትንሣኤ ዘጉባኤ ማተሚያ ቤት፣ ወንጌል ቅዱስ ንባቡና ትርጓሜው የሉቃስ ወንጌል ምዕራፍ 1 ቍጥር 27 ማብራሪያ (ዐዲስ አበባ፣ 1997)) በገድለ አርሴማ ላይ ግን ሁለት መላእክት መውረዳቸውና ቅዱሳኑን መመገባቸው ስለ የአርሴማ ክብር የተሻለ እንደ ሆነ ለማመልከት መሆኑ ግልጽ ነው፡፡

> የጽዋ ውሃ ቅዱሳን ሰማዕትና ብፅዕት ቅድስት አርሴማ እያዩት በደጋግ መላእክት እጅ ወደ ገነት ወጣ››፡፡[108]

‹‹<u>ከፍጥረት ሁሉ ይልቅ</u> ለብፅዕት አርሴማ ሰማዕት ክብርንና ልዕልናን ስለ ሰጣት ለእግዚአብሔር ፍጹም ምስጋናን እናቅርብ››[109] በሚለውና ከዚህ በላይ በሰፈሩት ምንባባት የገድለ አርሴማ አዘጋጅ አርሴማንና ማርያም በማፎካከር ላይ ይመስላል፡፡ በዚህ ስፍራ ላይ ማንንም ከማንም ሳይለይ ከፍጥረት ‹‹ሁሉ›› ይልቅ አርሴማ ክብርና ልዕልና እንዳላት እየተነገረ ያለ ሲሆን ከዚህ በላይ ባሉት ደግሞ ማርያም ብቻ የምትታወቅባቸውን እና ለእሷ የተሰጡትን ነገሮች ለአርሴማ በማጋራት ላይ ነውና፡፡

## ማርያምን ያመሰግኗታል

ምንም እንኳ ገድለ አርሴማ ከዚህ በላይ የሰፈሩትን ነገሮች በማቅረብ አርሴማን ከማርያም ጋር ለማወዳደር እየሞከረ ያለ ቢሆንም፤

> ከሔዋን ጀምሮ እስከ ሶፍያ ልጆች ድረስ በሮሜ አገር[110] ከእናታቸው ጋር ሰማዕት የሆኑ፣ ቅዱሳት አንስት ሁሉ [ማርያምን] ያመሰግኗታል፡፡ ከእርስዋም ጋር ይጫወታሉ፡፡ በትንቢት ቃላቸውና በስብከት ሕጋቸው የነቢያትና የሐዋርያት ማኅበር ሁሉ ያመሰግኗታል፡፡ እርሷ ባለሟላቸው ናትና፡፡ ቅድስት አርሴማም ነፍሴ ሆይ ፊታቸውን በማየት

---

108 የግንቦት ገድለ አርሴማ ቍጥር 62-64፡፡

109 መቅድም ቍጥር 29 ተመልከት - አጽንዖት የግል፡፡

110 በዚህ ምንባብ ላይ ሮሜን ያነሣው ምናልባት አርሴማ የሮሜ ተወላጅ በመሆኗ ይሆን?

> ተረጋጊ፤ ተደሰቺ። የመልካቸው ውበት የሚያስደንቅ ነውና። መድኀኒታቸው እመቤታችን ማርያም ዘወትር በመልካም ቃሏና በሚጣፍጥ ከንፈሮችዋ ታረጋጋቸዋለችና።[111]

በማለት ደግሞ ማርያም ምስጋና የሚገባት መሆኑን ያስነብባል። በዚህ ስፍራ ላይ ማርያምን ከፍ ከፍ ማድረግ የፈለገው ጸሐፊ ከመጽሐፍ ቅዱስ ሐሳብ ጋር የማይስማሙና ከዚህ በታች የሰፈሩትን ስሕተቶች ሠርቷል፤

‹‹ቅዱሳት አንስት ሁሉ ያመሰግኗታል››

ጸሐፊው ይህን ሐሳብ ያስቀመጠው ማርያም ምስጋና ይገባታል ለማለት ሊሆን ይችላል። እንዲህ ያለው ትምህርት ከቅርብ ጊዜያት ወዲህ ወደ ቤተ ክርስቲያን ገብቶ ትክክለኛ ትምህርት በመምሰል ብዙዎችን እያሳሳተ ያለ ትምህርት ነው። ማርያም በነበረችበት ዘመን የተጻፉት የዐዲስ ኪዳን ቅዱሳት መጻሕፍት ላይ እንዲህ ያለ ፍጡርን የማመስገን ነገር እንዳለ ፍንጭ የሚሰጥ ሐሳብ ማግኘት አይቻልም።

‹‹የነቢያትና የሐዋርያት ማኅበር ያመሰግኗታል››

ቀደም ሲል እንደ ተባለው ምንም እንኳ ማርያምን ማመስገን የሚባለው እንግዳ ትምህርት በቅዱሱ ቃል ያልተደገፈ ቢሆንም ነቢያትና ሐዋርያት አመስግነዋታልኮ ለማለት ጥረት የሚያደርጉ ሰዎች ሞልተዋል። እነዚህ ሰዎች ነቢያትና ሐዋርያት ያመሰገኗት መቼና በየትኛው ምንባብ ላይ ነው?

---

[111] የሐምሌ ገድለ አርሴማ ቍጥር 22።

የሚል ጠያቂ ሲመጣ መልስ መስጠት ግድ ስለ ሆነባቸው አንዳንድ ምንባባትን ያለ ዐውዳቸው በማናገር ላይ ይገኛሉ።

ይደግፈናል ብለው ከሚያጣምሟቸው ጥቅሶች መካከል በዋናነት ሉቃስ ወንጌል ምዕራፍ 1 ላይ ያሉ ሁለት ቍጥሮች ተጠቃሽ ናቸው። ምስጋና አቀረቡ የሚባሉትም ቅዱስ ገብርኤልና ቅድስት ኤልሳቤጥ ናቸው። በቅድሚያ ምስጋናውን አቀረበ ተብሎ የሚጠቀሰው ቅዱስ ገብርኤል ነው። እርሱ ከተናገረው ላይም የሚወሰደው ‹‹መልአኩም ወደ እርስዋ ገብቶ ደስ ይበልሽ፥ ጸጋ የሞላብሽ ሆይ፥ ጌታ ከአንቺ ጋር ነው፤ አንቺ ከሴቶች መካከል የተባረክሽ ነሽ አላት›› ያለው ሲሆን (ቍጥር 28) ይህን የገብርኤልን ንግግር መሠረት በማድረግም ‹‹መጋቤ ዐዲስ ቅዱስ ገብርኤል ‹ተፈሥሒ ኦ ምልዕተ ጸጋ እግዚአብሔር ምስሌኪ፤ ምልዕተ ጸጋ፣ ምልዕተ ክብር ድንግል ሆይ ደስ ይበልሽ› (ሉቃስ 1፥28) ሲል ወላዲተ አምላክ ድንግል ማርያምን ያመሰገነበት ልዩ ምስጋና ከፍጡር ሁሉ በላይ የሆነውን ንጽሕናዋንና ቅድስናዋን፣ ክብሯንና ልዕልናዋን በግልጥ ይመሰክራል›› የሚሉ ሰዎች አሉ።[112]

በዚህ ስፍራ ላይ የሰፈረው የመልአኩ ንግግር ምስጋና ነው ወይ? የሚለውን የሚመልስልን የማርያምን ሁኔታ መመልከቱ ነው። መጽሐፉ እንደሚለው ማርያም ‹‹ባየችው ጊዜ ከንግግሩ በጣም ደነገጠችና፦ ይህ እንዴት ያለ ሰላምታ ነው? ብላ አሰበች››። የሀገሩን ባህል የሚያውቀው ሉቃስ የገብርኤል ንግግር ሰላምታ ሳይሆን ምስጋና እንደ ሆነ ጠፍቶት ይሆን ማርያም ‹‹ይህ እንዴት ያለ ሰላምታ ነው? ብላ አሰበች›› ብሎ

[112] አንዱ ዓለም ዳግማዊ (መምህር)፣ ወላዲተ አምላክ በነገረ ድኅነት (1998) ገጽ 288።

ያስፈረው? ቀደም ሲል የቀረበው መጽሐፍ አዘጋጅ ሉቃስ ሰላምታ እንደ ሆነ ያስፈረውን እያዩ ንጽሕናዋ፣ ቅድስናዋ፣ ክብሯ፣ ልዕልናዋ ያሉት ከየት አምጥተው ይሆን? በርግጥ የመልአኩ ንግግር እንዲህ ላለው ትምህርት የሚሆን አይደለም። ሰዎቹ ግን መጽሐፉ የማይለውን በማለታቸው ጥብቅናቸው ለቅዱሱ መጽሐፍ ሳይሆን ለልማዳዊው ትምህርት መሆኑን አሳይተዋል።

በቀጣይ አመስጋኝ ሆና የምትጠቀሰው ቅድስት ኤልቤጥ ስትሆን እሷም ‹‹በኤልሳቤጥም መንፈስ ቅዱስ ሞላባት፥ በታላቅ ድምፅም ጮኻ እንዲህ አለች፦ አንቺ ከሴቶች መካከል የተባረክሽ ነሽ፥ የማኅፀንሽም ፍሬ የተባረከ ነው። የጌታዬ እናት ወደ እኔ ትመጣ ዘንድ እንዴት ይሆንልኛል? እነሆ፥ የሰላምታሽ ድምጽ በጆሮዬ በመጣ ጊዜ ፅንሱ በማኅፀኔ በደስታ ዘሎአልና። ከጌታ፤ የተነገረላት ቃል ይፈጸማልና ያመነች ብፅዕት ናት›› ያለችው ንግግር ይወሰዳል (ሉቃስ 1፥41-45)። የእርሷን ንግግር መነሻ በማድረግም

> ቅድስት ኤልሳቤጥ ‹ከእግዚአብሔር ተልከው የነገሩሽን የምታምኚ ብፅዕት ነሽ› በማለት አመሰገነቻት።... የእመቤታችን ቃል በሰማች ጊዜ መንፈስ ቅዱስ ሞላባት ምሥጢርም አናገራት እንጂ። በዚህም በመንፈስ ቅዱስ በመሞላቷ... ከሴቶች ተለይተሽ መርገመ ሥጋ መርገመ ነፍስ የሌለብሽ፤ በረከተ ሥጋ በረከተ ነፍስን እያማለደሽ የምታሰጭ ነሽ... ‹ወቡሩክ ፍሬ ከርሥኪ፦ የማኅፀንሽ ፍሬ ኢየሱስ ክርስቶስ ቡሩክ ነው› የሚለውን በማከል ከተናገረች በኋላ ይህ የማኅፀንዋ

ፍሬም ከእግዚአብሔር ተልከው የነገርዋትን በማመንዋ የተገኘ እንደ ሆነ ተገልጾላት ብፅዕነትዋን በመገለጽ አወድሳታለች

የሚል ማብራሪያ የሚሠሩ ሰዎች አሉ፡፡[113] ቀደም ሲል የቀረበውን የመጽሐፍ ቅዱስ ምንባብ አሁን ጸሐፊው ካሰፈሩት ሐሳብ ጋር ጎን ለጎን በማድረግ የተመለከተ ልባም አንባቢ ጸሐፊው ይህን ሁሉ ለማለት የሚያስችል ምንም ዓይነት መሠረት እንደሌላቸው መረዳት ይችላል፡፡ ይህን ሁሉ ያመጣው ቀደም ሲል እንደተባለው ልማዳዊው የቤተ ክርስቲያን ትምህርት እንጂ የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት አይደለምና፡፡

‹‹<u>መድኀኒታቸው እመቤታችን ማርያም</u>››

እዚህ ጋር ደግሞ ሌላ እንግዳ ትምህርት የሚያስተምረው ማርያምን መድኀኒት አድርጎ በማቅረብ ነው፡፡ ይህ ትምህርቱ ግን ‹‹እኛም አይተናል አባትም ልጁን የዓለም መድኃኒት ሊሆን እንደ ላከው እንመሰክራለን›› ከሚለው ከሐዋርያቱ ትምህርት ጋር የማይስማማ በመሆኑ ቤተ ክርስቲያን እንዲህ ያለውን እንግዳ ትምህርት በግልጽ ልታወግዝ ይገባታል (1ኛ ዮሐንስ 4፥14)፡፡ ምክንያቱም ለሁሉ ዋጋ ከፍሎ የዓለም መድኀኒት የሆነው አንድ እርሱም ጌታችን መድኀኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ብቻ ነው ‹‹አንዱ ስለ ሁሉ ሞተ›› ተብሎ ተጽፏልና (2ኛ ቆሮንቶስ 5፥14)፡፡

[113] በጽሐ ዓለሙ (መምህር)፣ ታአዶከስ (ጎንደር፣ ሚያዝያ 2009) ገጽ 225-226፡፡

# አርሴማ፤ ለኑሮ ሀብት የምታሰጥ…

ለኑሮ የሚያስፈልገንንም ሆነ ሀብት የሚሰጠን ሁሉን ቻዩ አምላካችን ሆኖ ሳለ እርሱን ለማስረሳት በረከት መስጠት የማትችል ፍጡር ላይ በመደገፍ ከፈቃደ እግዚአብሔር ውጪ እንድንሆን የተሠራው የተንኮል ሥራ እንዲህ ይላል፤

- ‹‹እመቤቴ ቅድስት አርሴማ ሆይ! ንጽሕት ነሽ፡፡ የበረከት ሀብት ነሽ፡፡ እመቤቴ ቅድስት አርሴማ ሆይ የሰማይ ውዱድ ምሳሌ የሆነው የበረከትሽ ሀብት እንደ ንጹሕ ዝናም በራሴ ላይ ይውረድ፡፡ እንደ ብሩህ ደመናም በላዬ ይዙር››፡፡[114]
- ‹‹በዚህች ቦታ ዛሬ የተሰበሰብነውን ዘወትር ጠብቂን፡፡ በላዩ የሞት እንክርዳድ እንዳይበቅል የእርሻችንን ፍሬ ባርኪልን፡፡ የመቅሠፍትን ሞት ከእኛ ላይ አስወግጂ፡፡ አንበጣና በረድ በምድራችን እንዳይቀርብ፤ የበደልና የኀጢአት ጨለማ ከላያችን ይባረር፡፡ ጠላት (ዲያብሎስ) ይፍራ፤ ይንቀጥቀጥ፡፡ አውሬም ድል ይነሣ፡፡ በዘመኑ ሁሉና በልጅ ልጅ ሁሉ፡፡ የሰማዕት ቅድስት አርሴማ በረከት ከሁላችን የአንድነት ልጆች ጋር ለዘላለሙ ይኑር››፡፡[115]
- ‹‹የእግዚአብሔር አገልጋዩ ቡርክት ቅድስት አርሴማ ሆይ፤ በየጊዜውና በሰዓቱ ሁሉ ለዘላለሙ በረከትሽና ረድኤትሽ በሁላችን ሕዝበ ክርስቲያን ላይ ይደር››፡፡[116]

---

[114] መቅድም ቍጥር 36 ተመልከት፡፡
[115] መቅድም ቍጥር 37 ተመልከት፡፡
[116] የሐምሌ ገድለ አርሴማ ቍጥር 70፡፡

ከዚህ በላይ በተደረደሩት ምንባባት ውስጥ አርሴማ በረከትና ረድኤት በምልጃ ሥራዋ የምታሰጥ ሳትሆን እርሷ ራሷ የበረከትና የረድኤት ምንጭ እንደ ሆነች መስፈሩን ማስተዋል ተገቢ ነው። ለዚህም ‹‹የበረከት ሀብት ነሽ››፣ ‹‹የበረከትሽ››፣ ‹‹ባርኪልን››፣ ‹‹የሰማዕት ቅድስት አርሴማ በረከት››፣ ‹‹በረከትሽና ረድኤትሽ›› በሚል የሰፈሩት ቃላት ምስክር ናቸው። ታዲያ ከዚህ በላይ እግዚአብሔርን መዳፈር ይኖራል? ከዚህስ በላይ ‹‹የዕለት እንጀራችንን ዛሬ ስጠን››፣ ‹‹የእግዚአብሔር በረከት ባለ ጠጋ ታደርጋለች፥ ኀዘንንም ከእርስዋ ጋር አይጨምርም››፣ ‹‹በጎ ስጦታ ሁሉ ፍጹምም በረከት ሁሉ ከላይ ናቸው፥ መለወጥም በእርሱ ዘንድ ከሌለ በመዞርም የተደረገ ጥላ በእርሱ ዘንድ ከሌለ ከብርሃናት አባት ይወርዳሉ›› ተብሎ የተጻፈውን ቃለ እግዚአብሔር አልቀበልም ባይነት ከወዴት ይመጣል (ማቴዎስ 6፥11። ምሳሌ 10፥22። ያዕቆብ 1፥17)?

## አርሴማ፤ ከእሳት ባሕር የምታድን

መጽሐፍ ቅዱስ ስለ እሳት ባሕር የሚናገር ክፍል ያለው በመሆኑና ማንም ወደዚያ መግባት ስለማይፈልግ ሰዎችን ከእሳት ባሕር የሚያድን እንዳለ መረዳት ታላቅ መታደል ነው (ራእይ 19፥20)። ትልቁ ቁም ነገር ግን ከእሳት ባሕር ማዳን የሚችለው ማን ነው? በምን ኃይሉ ነው ይህን ማድረግ የሚችለው? የሚለው ነው።

ገድለ አርሴማ በምን ኃይል ይህን እንደምታደርግ ባያሳውቅም አርሴማ ከእሳት ባሕር ማዳን ትችላለች ለማለት ‹‹ብፅዕት ቅድስት እመቤቴ አርሴማ ሆይ! እነሆ የሕይወቴ መርከብ እልሻለሁ። ነፍሴን ከእሳት ባሕር የምታሻግሪያት አንቺ ነሽና››፣

‹‹በብፅዕት ቅድስት አርሴማም የረድኤት ኀይል ከገሃነም እሳት ያድነን›› በማለት ሐሳቡን አስቀምጧል።[117]

ከእሳት ባሕር ማዳን ማለት ከጥፋት መታደግና ወደ ዘላለማዊ ሕይወት ማስገባት ማለት ነው። ዋጋ የሚያስከፍል ነገር ነውና። ሰዎችን ወደ ዘላለማዊው ሕይወት ለመውሰድና ከእሳት ባሕር ለመታደግ ደግሞ ሥልጣንና ኃይል ካለው ከመድኅነ ዓለም ከክርስቶስ በቀር የሚችል ማንም የለም ወደፊትም አይኖርም።

## ስለ አርሴማ ሰይጣን የሰጠው ምስክርነት

ብዙዎች በተለይ በዘመናችን ያሉ አገልጋዮች አገልግሎታቸው ትክክል እንደ ሆነና ሰዎች በአገልግሎታቸው ላይ ጥያቄ እንዳያነሡ እንደ ጥሩ ማረጋገጫ አድርገው እያቀረቡ ያሉት ሰይጣን የያዘቻውን ሰዎች በማስለፍለፍ ሰይጣኑ ስለ አገልግሎታቸው እንዲናገር በማድረግ ነው። ምናልባት ይህን ልምምድ ያገኙት ከገድላት ውስጥ ሳይሆን አይቀርም።[118] አንዳንድ ገድላት አጋንንት ቅዱሳኑ ፊት መቆም እንደማይችሉና እነሱ ባለቡት ቦታ ላይ ሲሆኑ ዕቅም እንደሚያንሣቸው

---

[117] መቅድም ቍጥር 14 ተመልከት። የኅዳር ገድለ አርሴማ ቍጥር 45።

[118] በገድላት ውስጥ የሚታየው የአጋንንትን ምስክርነት የመቀበያ መንገድ እና በዘመናችን ባሉ አገልጋዮች ነን ባዩች ያለው የአጋንንትን ምስክርነት የመቀበያ መንገድ ልዩ ልዩ መሆኑ ግልጽ ነው። በገድላት ውስጥ የሚታየው ወይም ቅዱሳኑና አልያም የቅዱሳኑን ስም መጥራት ወይም ደግሞ የቅዱሳኑን ምስል አጋንንቱ ባለቡት ቦታ (ምናልባት ጣዖት አምልኮ ባለበት ቦታ ላይ ወይም ራሳቸው አጋንንቱ በመገለጥ…) ይሆናል። አጋንንት በያዘቸው ሰዎች በኩል የሚኖር የአጋንንት ምስክርነት በገድላት ውስጥ አልፎ አልፎ የሚያጋጥም ቢሆንም በዚህ ዘመን እንዳሉ አገልጋይ ነን ባዩች ግን በብዛት የሚገኝ አይደለም። በዘመናችን ያለው ግን አጋንንትን ፊት ለፊት በማግኘት የሚደረግ የቃላት ለውውጥ ሳይሆን በሰው ላይ ያደሩ ናቸው የተባሉትን አጋንንትን ማስለፍለፍ ነው።

ይናገራሉ፡፡ ገድለ አርሴምም በዚህ መስመር ላይ ተሰልፎ ይገኛል፡፡ ሐሳቡም ከዚህ በታች ሰፍሯል፤

> …መተተኞች መልካቸው የየራሳቸው የሆኑ ከላሞችና ከፍየሎች ስብ ያቀረብንላችሁን መሥዋዕታችንን ትቀበሉ ዘንድና እስከ የልጅ ልጅ እናንተን ለአመንባችሁ ለእኛ ቅድስት አርሴማ በሚሉአት በዚያች ሴት ላይ የሥልጣናችሁን ከፍታ ታሳዮ ዘንድ በባሕርና በየብስ በአየርም ያላችሁ በደመናዎችና በነፋሳት ክንፍ የምትሮጡ አገሌና እገሊት ሁላችሁ አማልክቶቻችን ወደ እኛ ኑ፡፡ እርሷ አውካናለችና እናንተንም አውካለች ገፍታለችምና፤ እያሉ በየስማች ጩኸው እያለቀሱ ይጠሯቸው ነበር፡፡ የእነዚህንም መተተኞች የጩኸት ብዛት በሰማና ባየ ጊዜ፣ ያን ጊዜ ስሙ ጋውል የሚባል ከአርመንያ አጋንንት አንዱ በምሽት ወደ እነርሱ መጣ፡፡ እርሱም በአርጤምስ ልብ ገብቶ የአቴናን ሰዎች ያሳታቸው ነው፡፡ እነዚህንም መተተኞች እነግራችሁ ዘንደ ስሙኝ፡፡ በዚህ ቦታ ውስጥ በዚህች ቀን ብትጠሩን የምንመጣ አይደለንም አላቸው፡፡ ይህቺ ሴት በነበልባሏ አቃጥላናለችና፣ በቃሏም አስደንግጣናለችና፡፡ እኛ በእጇ ገመድ የታሠርን ነን፡፡ በእርስዋ ወጥመድም አጥምዳናለች፡፡ በእርስዋ ላይ ክፉ እናደርግ ዘንድ አይቻለንም፡፡ ከእኛ በሚበልጥና በሚበረታ እጅ፣ ግርማውም በሚያስፈራን ፈጣሪ ይጠብቃታልና፡፡ ይኸውም የጥንት ጠላታችንና በአለቃችን በዲያብሎስ

> መንግሥት አጠገብ የሚቀመጡት የወንድሞቻችን ጠላት የመላእክት አለቃ ሚካኤል ነው። በንጉሥ ድርጣድስ ከተማ ያሉትን ቢሆን፤ በገሃነም ጥልቅ አስጥሞአቸዋል። እኛም ወደ ሲኦል ጥልቅ እንዳታወርደን ወደዚህች ሴት መቅረብን እንፈራለን። ከእኛም ብዙ ሠራዊትን አስጥማለችና። ስለዚህም ወደ እርሷና የእርስዋን ስም ወደሚጠራ እኔ አልቀርብም አላቸው።... ቅድስት አርሴማ በሚሷት ግን በእርስዋ ላይ የምንከፋበትና የምናጠፋበት ሥልጣንና ችሎታ የለንም አለ። በግርማዋ ኀይል እፈራለሁ፣ እደነግጣለሁ። ዛሬም በፊቴ ስሟን አትጥራ። በእሳት ነበልባል ሥጋዬ ይቃጠላልና። ምድርም ታሰጥመኝ ዘንድ ትወዳለች። ደመናትም በላዬ የመባርቅትን ብልጭታ ያወርዱ ዘንድ ይወዳሉ። አሁንም ወደ ማደሪያዬ ባሕር እገባ ዘንድ ተወኝ...።[119]

ሰይጣን የአርሴማን ቅድስናና ክብር ተናገረ በተባለበት በዚህ ምንባብ ውስጥ ያሉ አንዳንድ ነገሮች በማሳየት ጸሐፊው ሰዎች እግዚአብሔርን ትተው ሌላ ፍጡር ላይ እንዲደገፉ የሠራውን ሥራ ግልጽ ማድረግ ያስፈልጋል።

- ‹‹በነበልባሏ አቃጥላናለችና፣ በቃሏም አስደንግጣናለችና፣ በእጇ ገመድ የተሠርን ነን፣ ወጥመድም አጥምዳናለች፣ በግርማዋ ኀይል እፈራለሁ። እደነግጣለሁ›› - በእነዚህ አባባሎች የተገለጸው ነገር አርሴማ አጋንንቱን ድል የምትነሣቸውም ሆነ የምታስፈራቸው በራሷ ኀይልና

[119] የነሐሴ ገድለ አርሴማ ቍጥር 9-16።

ብርታት እንደ ሆነ ነው፡፡ እነዚህ ቃላት ባሉበት ስፍራ ላይ አንባቢው በሚገባ ቢመረመር የእግዚአብሔር ርዳታም ሆነ አብሮነቱ አይታይም፡፡ እርሷ ‹‹በቃሏ›› ራሷ ‹‹በእጇ›› የምታስደንግጥና የምታስፈራ ናትና፡፡

- ‹‹በእርስዋ ላይ ክፉ እናደርግ ዘንድ አይቻለንም፡፡ ከእኛ በሚበልጥና በሚበረታ እጅ፣ ግርማውም በሚያስፈራን ፈጣሪ ይጠብቃታልና፡፡ ይኸውም የጥንት ጠላታችንና በአለቃችን በዲያብሎስ መንግሥት አጠገብ የሚቀመጡት የወንድሞቻችን ጠላት የመላእክት አለቃ ሚካኤል ነው›› - በዚህ ስፍራ ላይ ደግሞ ጥበቃ እንዳላት ያሳይና ጠባቂዋ ግን በሁለት ዓይነት መልኩ ተገልጿል፡፡ በመጀመሪያው ‹‹ፈጣሪ ይጠብቃታል›› በሚል ሲሆን ‹‹ይኸውም›› በሚል ጥበቃ እያደረገ ያለው ማን መሆኑን ሲያሳይ የአጋንንቱ ጥንተ ጠላት የሆነው ‹‹የመላእክት አለቃ ሚካኤል ነው›› ይላል፡፡ ጸሐፊው በዚህ ቦታ ላይ እየሰበከን ያለው ደግሞ የሚካኤልን ጠበቂነት መሆኑ ግልጽ ነው፡፡ ይህ ሐሳቡ ደግሞ ‹‹እግዚአብሔር ጠባቂዬ ነው፥ በእርሱም እታመናለሁ፤ ጋሻዬና የረድኤቴ ቀንድ፥ መጠጊያዬና መሸሸጊያዬ፥ መድኃኒቴ ሆይ፥ ከግፍ ሥራ ታድነኛለህ››፣ ‹‹እግዚአብሔር ሕያው ነው፥ ጠባቂዬም ቡሩክ ነው፤ የመድኃኒቴ ጠባቂ አምላኬ ከፍ ከፍ ይበል›› ከሚለው ቅዱስ መጽሐፍ የራቀ መሆኑ ግልጽ ነው (2ኛ ሳሙኤል 22፥3፡ 47)፡፡ መላእክት የእግዚአብሔር የሆኑትን መጠበቃቸው እውነት ነው፡፡ ይህን የሚያደርጉት ግን ክብሩንና ውዳሴውን ለራሳቸው ለመውሰድ ሳይሆን የሥራ ኀላፊነታቸው በመሆኑ ነው፡፡
- ‹‹ወደ ሲኦል ጥልቅ እንዳታወርደን፣ ብዙ ሠራዊትን አስጥማለችና›› - እዚህ ጋር ደግሞ የአርሴማ ኃይል

ብርታት እንኳን የሰው ልጆችን አጋንንትንም ወደ ሲኦል የማውረድ አቅም ያለው ብርቱ ነው የሚለውን ለማሳየት የተሞከረ እንደ ሆነ ግልጽ ነው። ይህም ደግሞ ‹‹እግዚአብሔር ይገድላል ያድናልም፤ ወደ ሲኦል ያወርዳል፥ ያወጣል›› የሚለውን ቃለ እግዚአብሔር በሚቃወም መልኩ የቀረበ ሐሳብ ነው (1ኛ ሳሙኤል 2፥6)። መጽሐፍ ቅዱስ እንደሚያስተምረው ለሁሉ እንደ ሥራው የመክፈል ሥልጣን ያለው ጌታችን ብቻ ነው (ሮሜ 2፥6። 1ኛ ጴጥሮስ 1፥17። ራእይ 22፥12)። መልካም ያደረጉትም ሆነ ክፉ ያደረጉትም ከእርሱ የፍርድ ዙፋን ፊት የሚቆሙበት ጊዜ አላቸው። አርሴማም ከእነዚህ አካላት አንዷ ትሆናለች እንጂ እርሷ ማንንም ወደ ሲኦል ጥልቅ የማውረድ አቅሙም ሥልጣኑም የላትም።

- ‹‹የእርስዋን ስም ወደሚጠራ አልቀርብም፣ ዛሬም በፊቴ ስሟን አትጥራ››[120] - ይህ ደግሞ ‹‹የጌታን ስም

[120] ይህን የገድሉን ሐሳብ ሳነብ አንድ ታሪክ ትዝ አለኝ። በሰንበት ትምህርት ቤታችን ውስጥ በትጋት ታገለግል የነበረችና ጥሩ ምሳሌነት ያላት አንዲት እኅት ሰይጣን ያዛት ተብሎ ሲወራ ሰማንና ቤቷ ስንሄድ ከእኛ ቀድመው የሰሙ የሰንበት ትምህርት ቤት አገልጋዮች ደርሰው የጸሎት መጽሐፍ እያነበቡ ይጸልዩላት ነበር። ከእነርሱም መካከል አንዱ በጸሎት መጽሐፍ ግንባሯን መታ መታ እያደረገ በሚካኤል ስም አዝሃለሁ ይላል። መንፈሱም ‹‹እባክህ ይህን ስም አትጥራብኝ ተቃጠልኩ›› ይላል። አገልጋዩም መልሶ ‹‹ብል በሚካኤል ስም አዝሃለው ልቀቃት›› ይላል ‹‹መንፈሱም ትቀልዳለክ እንዴ? እንዴት ነው የምለቃት?›› በሚል ሙግት ይገጥማል። በዚህ ሁኔታ አገልጋዩ የብዙ ቅዱሳንን ስም ይጠራል። መንፈሱም የቅዱሳኑ ስም ሲጠራ ‹‹እባክህ ይህን ስም አትጥራብኝ›› ይላል። አትጠራብኝ ያለው ስም ተጠርቶ ልቀቅ ሲባል ግን መልሱ ‹‹እንዴት ነው የምለቃት?›› የሚል ነበር። በኋላ በጸሎት መጽሐፍ እየጸለየላት ያለው ሰንበት ተማሪ ክፉኛ ተናዶ በጸሎት መጽሐፉ በኃይል እየመታት ‹‹ለምንድን ነው የማትለቀው? ልቀቅ እንጂ››

የሚጠራ ይድናል›› የሚለውንና ጉልበት ሁሉ የሚሰግድለትን ስም ለማደብዘዝ እና የፍጡርን ስም በውስጣችን ቀርጾ ለማስቀመጥ የተሞከረ ሙከራ ነው። አጋንንት መቼም ይሁን መቼ የፍጡር ስም ቢጠራባቸው ፈርተውም ሆነ ተንቀጥቅጠው አያውቁም። ‹‹ከእርስዋ እንድትወጣ በኢየሱስ ክርስቶስ ስም አዝሃለሁ›› የሚለውን ድምጽ ሲሰሙ ግን መጽሐፉ እንደሚለው በዚያው ሰዓት ይወጣሉ (የሐዋርያት ሥራ 16፥18)። ለዚህስ አይደል እንዴ ደቀ መዛሙርቱ ከተላኩበት ሲመለሱ ‹‹ጌታ ሆይ፥ አጋንንትስንኳ በስምህ ተገዝተውልናል›› ያሉት (ሉቃስ 10፥17)።

- ‹‹በእሳት ነበልባል ሥጋዬ ይቃጠላልና›› - አስገራሚው የሰይጣን ምስክርነት ደግሞ በአርሴማ ምክንያት ሥጋው በእሳት ነበልባል እየተቃጠለ መሆኑን መናገሩ ነው። መጽሐፍ ቅዱስ ሰይጣን መንፈስ ስለመሆኑ እየተናገረ (ኤፌሶን 6፥12) መናፍስት ደግሞ ሥጋና አጥንት የሌላቸው መሆኑ እየታወቀ ሥጋዬ ይቃጠልብኛል የሚለውን ሐሰተኛ ምስክርነት የሰዎች አእምሮ በውሸት ሞልቶ እውነተኛውን ትምህርት ቦታ ለማሳጣት የተዘራ አረም ነው። በዚህም መለኪያነት ከዚህ በላይ የሰፈሩትን ነጥቦች ሁሉ ሐሰተኛ ንግግሮች መሆናቸውን መገንዘብ

---

ይላል። መንፈሱም ‹‹ከመቼ ወዲህ ነው በዚህ ስም ማስለቀቅ የጀመርከው?›› የሚል ስላቅ የተሞላበት ጥያቄ ይጠይቃል። እስከዚህ ሰዓት ዝም ብሎ ይመለከት የነበረ ሌላ አገልጋይ ተነሥቶ ‹‹በኢየሱስ ዝም አዝሃለሁ ውጣ›› ይለዋል። መንፈሱም ክፉኛ መጮህ ይጀምራል። ልጁም ደጋግሞ ‹‹በኢየሱስ ስም አዝሃለሁ ውጣ›› ይለዋል፤ መንፈሱም ይለቃታል። ይህን ክንውን በዝምታ ይከታተሉ የነበሩ ብዙዎች ‹‹በሉ ጴንጤዎች ይጸልዩላት (የዚያን ጊዜ ተሐድሶ የሚለው ስም ብዙም አልገነነም ነበር)›› ብለው ከቤቱ ወጡ።

ይቻላል፡፡ ለነገሩስ ጌታችን ሰይጣንን ‹‹የሐሰት አባት ሐሰትን ሲናገር ከራሱ ይናገራል›› ብሎት የለ (ዮሐንስ 8፥44)? እውነት የሌለውንና የሐሰት አባት የሆነውን የሰይጣንን ምስክርነት ሰምቶ እንደ እውነተኛ ትምህርት መቀበል ምን የሚሉት የዋህነት ይሆን?

## የገነት ፍሬን እንዳፈራ ክብሯን ልናገር

የመጽሐፍ ቅዱስ አማኞች እንደ መሆናችን መናገር የሚገባን ክብር የማንን እንደ ሆነ መጽሐፉ የሚለውን ማወቅ ግዴታ ነው፡፡ መጽሐፉ ደግሞ ‹‹አፌን ምስጋና ምላ ሁልጊዜ ክብርህንና ግርማህን እዘምር ዘንድ››፣ ‹‹ሰማያት የእግዚአብሔርን ክብር ይናገራሉ፥ የሰማይም ጠፈር የእጁን ሥራ ያወራል››፣ ‹‹የአምላክ ልጆች ሆይ፥ ለእግዚአብሔር አምጡ፥ ክብርንና ምስጋናን ለእግዚአብሔር አምጡ››፣ ‹‹ለስሙም ዘምሩ፥ ለምስጋናውም ክብርን ስጡ››፣ ‹‹ክብር ለእግዚአብሔር በአርያም ይሁን ሰላምም በምድር ለሰውም በጎ ፈቃድ አሉ›› በሚል ክብሩን ልንናገርለትና ልንዘምርለት የሚገባው አንድ እርሱም ሰማይንና ምድርን የሠራው ጌታ መሆኑን ደጋግሞ ያስተምራል (መዝሙር 71፥8፤ 19፥1፤ 29፥1፤ 66፥2፡፡ ሉቃስ 2፥14)፡፡

ከዚህ ውጪ ግን የፍጡርን ክብር ከፍ ከፍ እንድናደርግና በዚህም ገነትን እንድንወርስ የሚመክር የቅዱስ መጽሐፍ ምክር የለም፡፡ የገድለ አርሴማ ጸሐፊ ግን ‹‹የገነትን ፍሬ አፈራ ዘንድ በቅድስት ብፅዕት ሰማዕት አርሴማ ያለውን ልዕልናዋንና ክብሯን እንድናገርና የልቧን የሃይማኖት ፍሬ እንዳፈራ አድርገኝ›› በማለቱ ቀደም ሲል ከቀረቡት ቅዱሳት መጻሕፍት የተለየና በየትኛውም የእግዚአብሔር ቃል ሊረጋገጥ የማይችል

የስሕተት ትምህርት ወደ ቤተ ክርስቲያን በማስገባቱ ፍርድ የሚጠብቀው ሆኖ ይታያል፡፡[121]

ጸሐፊው በዚህ ቦታ ላይ ጸሎት እያቀረበ መሆኑ ግልጽ ነው፡፡ ጸሎቱንም እያቀረበ ያለው የገነት ፍሬን ለማፍራት ነው፡፡ የሚገርመው ደግሞ የገነት ፍሬን ለማፍራት እንደ መለኪያ አድርጎ ያስቀመጠው የአርሴማን ክብሯን፣ ልዕልናዋን በመናገር መሆኑ ነው፡፡ የፍጡራንን ክብርና ልዕልናን በመናገር የገነትን ፍሬ ማፍራት ይቻላል የሚለው የገድለ አርሴማ አዘጋጅ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ግንዛቤ የሌለውና ደስ ያለውን ሁሉ የሚጽፍ ሰው መሆኑን ከዚህ መረዳት ይቻላል፡፡

## የመጽሐፍ ቅዱስ ምንባባት ያለ መልእክታቸው እንዲናገሩ ማስገደድ

በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ያሉ ምንባባት የየራሳቸው መልእክትና ሐሳብ አላቸው፡፡ ለዚህም ደግሞ ምክንያቱ የተጻፉበት ዘመን ልዩ ልዩ መሆን፣ ጸሐፊዎቹም በእውቀት በሙያ… አንድ አለ መሆናቸው፣ የተጻፉበት ምክንያት ተመሳሳይ አለ መሆኑ፣ የተጻፉበትም ቦታ አንድ አለ መሆኑ፤ ታሪኮቹ፣ ትምህርቶቹ፣ ምክሮቹም ሆነ ሌሎች ሐሳቦች የየራሳቸው ይዘት እንዲኖራቸው ምክንያት ሆኗል፡፡ ይህ ማለት ግን አንዱ ከሌላው ጋር አይስማማም ማለት አይደለም፡፡ እርስ በእርሳቸው ፍጹም ተስማሚ ናቸው፡፡ መጽሐፉ ሲጻፍ ላልነበርን የዚህ ዘመን አንባቢዎች ግን ከሕይወታችን ጋር

---

121 መቅድም ቊጥር 6 ተመልከት፡፡

ስናዛምድም ሆነ ስናስተምር መጽሐፉን የምንፈታበት መንገድ እንደ መጽሐፉ ይዘት ሊሆን ይገባል፡፡[122]

አንዳንዶች ግን ከዚህ ፈቀቅ በማለት ጥቅሶችን ያለ መልእክታቸው እንዲናገሩ በማድረግ ለተሳሳተው ትምህርታቸው ድጋፍ እንዲሆኗቸው ለማድረግ ጥረት ያደርጋሉ፡፡ ከእነዚህ መካከል የአርሴማ መጽሐፍ አዘጋጅ አንዱ ነው፡፡ ይህንንም ከዚህ በታች በሰፈሩት ልዩ ልዩ የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅሶች ውስጥ ለማሳየት ጥረት ተደርጓል፡፡

# እንደ ማር ስለሚጣፍጥ አንብቡት

የገድለ አርሴማ አዘጋጅ፤ ‹‹እርሱም የሰው ልጅ ሆይ፥ አፍህ ይብላ፥ በምሰጥህም በዚህ መጽሐፍ ሆድህን ሙላ አለኝ፡፡ እኔም በላሁት፥ በአፌም ውስጥ እንደ ማር ጣፈጠ›› (ሕዝቅኤል 3፥3) የሚለውን የሕዝቅኤልን መጽሐፍ የተጠቀመው ‹‹አንብቡት እንደ ማር ይጣፍጣል ድኅነተ ነፍስም ይገኝበታል›› በሚል

122 አንድ አባት ከሥነ አፈታት ጋር በተያያዘ የሰጡት ምሳሌ ለዚህ ቦታ ተስማሚ ሳይሆን አይቀርም፡፡ በእርሳቸው ምሳሌ መሠረት ሙዝ፣ አፕል፣ አናናስ እና ብርቱካን ጣፋጭ ፍራፍሬዎች በመሆን አንድ መደብ ላይ የሚቀመጡ ቢሆኑም አመጋገብ ላይ ግን እንደየባሕርያቸው ነው የሚበሉት፡፡ አፕልን አጥበን ብቻ እንመገበዋለን፤ አፕልን እንደተመገብነው አናናስን እንብላ ብንል ውጤቱ የጠበቅነው አይሆንም፡፡ ሙዝን ልጣጩን በእጃችን በመላጥ ብቻ እንመገበዋለን፡፡ አሁንም አናናሱን ሙዙን እንደላጥነው በእጃችን እንላጠው ብንል የማይሆን ነገር ነው፡፡ ወይም ደግሞ ሙዝን በመግመጥ አንደተመገብነው ብርቱካኑን እንብላ ብንል በውስጡ ያሉት ፍሬዎች ያውኩናል፡፡ ስለዚህ አንዱን ፍራፍሬ ከሌላው በተለየ የአመጋገብ ሁኔታ በመመገብ በጣዕሙ ስንረካ ጥቅሙንም እንወስዳለን፡፡ እንዲሁ ደግሞ መጽሐፍ ቅዱስንም እንደየባሕርይ (መጽሐፍ ቅዱስ የታሪክ ክፍል፣ የመዝሙር ወይም የቅኔ ክፍል፣ የትንቢት ክፍል፣ ወደ ልዩ ልዩ አብያተ ክርስቲያናት እና ግለ ሰቦች የተላኩ የመልእክታት ክፍሎች አሉት) የማንጠቀም ከሆነ አናናሱን እንደ መግመጥ ሊሆንብን ይችላል፡፡

ለሚያስቀምጠው ሐሳብ ድጋፍ ለማድረግ ነው፡፡ እንደ ማር ስለሚጣፍጥ አንብቡት የሚለው ግን ትንቢተ ሕዝቅኤልን ሳይሆን ገድለ አርሴማን ነው፡፡[123] አዘጋጁ ገድለ አርሴማን እንደ ማር ይጣፍጣል ብሎ ቢያምን ያንንም በጽሑፉ ቢያስተላልፍ ምንም ማለት ላይሆን ይችላል፡፡ ከዚህም የበሳ ስለሚያስነብቡን፡፡ ችግሩ የሕዝቅኤልን ትንቢት የሐሳቡ ደጋፊ ለማድረግ መሞከሩ ነው እንጂ፡፡

## ለዳንኤል አንበሶች ሰገዱለት

በትንቢተ ዳንኤል እንደሰፈረው ጸሎት መጸለይ በተከለከለበት ሰዓት ዳንኤል ወደ አምላኩ በመጸለዩ ምክንያት ወደ አንበሳ ጉድ ጓድ ይጣላል፡፡ በዚያም ውስጥ ምን እንደተከናወነ መጽሐፍ ቅዱስ ‹‹ንጉሡም ተናገረ ዳንኤልንም፦ የሕያው አምላክ ባሪያ ዳንኤል ሆይ፥ ሁልጊዜ የምታመልከው አምላክህ ከአንበሶች ያድንህ ዘንድ ችሎአልን? አለው፡፡ ዳንኤልም ንጉሡን፦ ንጉሥ ሆይ፥ ሺህ ዓመት ንገሥ፡፡ በፊቱ ቅንነት ተገኝቶብኛልና፥ በአንተም ፊት ደግሞ፥ ንጉሥ ሆይ፥ አልበደልሁምና <u>አምላኬ መልአኩን ልኮ የአንበሶችን አፍ ዘጋ፥ እነርሱም አልጐዱኝም አለው</u>›› በማለት ነው ያስቀመጠው (ምዕራፍ 6 ቍጥር 20-22 - አጽንዖት የግል)፡፡

ያልተጻፈ ለማስነበብ የደፈረው የገድለ አርሴማ አዘጋጅ ግን ‹‹ነቢዩ ዳንኤልን በአንበሶች ጉድጓድ እንደ ጣሉት፤ እግዚአብሔር ግን እንዳዳነው፤ አንበሶችም እንደ ሰገዱለት፤

[123] መግቢያ ገጽ 7 ይመልከቱ፡፡

የእግሩንም ትቢያ እንደላሱ አስቡ›› በማለት መጽሐፉ ላይ ያልሰፈረ ነገር ያለ በማስመሰል ጽፏል፡፡[124]

ይህን ያደገረበት ምክንያት ከዚህ በኋላ ‹‹ያን ጊዜም እነዚህን አውሬዎች ከጉድጓዳቸው አወጡአቸው፡፡ እነሱም አንበሶች፣ ነብሮች፣ ድብና ጊንጦች ናቸው፡፡ ከብረት ማሠሪያቸውም ፈቷቸው ነገር ግን ወደ ቅዱሳን ሰማዕት አልቀረቡም፡፡ የብረቱን አጥር እየሰበሩ ወደ ዱር ሸሹ እንጂ፤ ከቅዱሳን ሰማዕት እግር በታች የሰገዱ ነበሩ፡፡ የእግራቸውንም ትቢያ የላሱ ነበሩ፡፡ ከጫማቸውም ሥር የተኙ ነበሩ፡፡ የቅዱሳኑን ሰውነት በጅራታቸው የዳሰሱ ነበሩ፡፡ መዓዛቸውንም ያሸተቱ ነበሩ›› በማለት ለሚያስፈረው ሐሳብ ድጋፍ ይሆነው ዘንድ በማሰብ ነው፡፡[125] ይህን ለማለት ግን በዳንኤል መጽሐፍ ውስጥ የሌለ ነገር ያለ በማስመሰል ማስፈሩ አንባቢውን ለማሳሳት ካልሆነ በቀር ምንም ምክንያት ሊኖረው አይችልም፡፡

## ያልተጻፈ ማንበብ

ያልተጻፈውን የማንበብ ችግር የገድለ አርሴማ ብቻ ሳይሆን የአብዛኛው አገልጋይና የብዙ መጻሕፍት ችግር ነው፡፡ ለተመለመደውና ባህላዊ ለሆነው ትምህርት መጽሐፍ ቅዱሳዊ ምንባብ ማቅረብ ግድ በሚልበት ጊዜ ሁሉ የሚወሰደው እርምጃ እሱ ነውና፡፡

በገድለ አርሴማ ላይ እንደተጻፈው ‹‹መድኀኒታችን፣ በእኔ ዘንድ ከሁሉ የሚበልጥ ሥጋውን ለእሳት ወይም ለሰይፍና ለስለት ወይም እንደ በጎችና ላሞች የሚታረድ፣

[124] የሚያዝያ ገድለ አርሴማ ቍጥር 45፡፡
[125] የሚያዝያ ገድለ አርሴማ ቍጥር 51-53፡፡

ወይም ለጊንጦችና ለአውሬዎች የሚሰጥ ይበልጣል ያለውን ልብ አድርጉ›› የሚል ነገር ጌታ ተናግሯል፡፡[126]

ይህን ንግግር ያደረገችው አርሴማ ስትሆን በእርሷ አቀራረብ መሠረት ጌታ ይህን ተናግሯል ከተባለ አርሴማ ይህን ሐሳብ ልታገኝ የምትችለው በሁለት ዓይነት መንገድ ነው፡፡ ወይ ራሱ ጌታችን ተገልጦም ሆነ በራእይ ነግሯት አልያም ከቅዱሱ መጽሐፍ አንብባ፡፡ ነገር ግን እንዲህ ያለ ሐሳብ ቃለ እግዚአብሔር ውስጥ የሌለ ሲሆን ገድሉም ውስጥ ጌታ ተገልጦም ሆነ በራእይ ይህን የሚመስል ሐሳብ ሲያስተላልፍ አልታየም፡፡ ምናልባት አርሴማ ጌታችን ስትል የጠራችው ጌታ ክርስቶስ ሳይሆን ሌላ ካልሆነ በቀር ጌታችን እንዲህ ያለ ነገር አልተናገረም፡፡ ይህ ደግሞ ለራሳቸው የስሕተት ትምህርት እንዲሆንላቸው መጽሐፍ ቅዱስን ምክንያት በማድረግ እንግዳ ትምህርት ወደ ቤተ ክርስቲያን አሾልከው ለማስገባት የሠሩት ሥራ ነው፡፡

## መጽሐፍ እንደ ተናገረ

የዐዲስ ኪዳን ጸሐፍት በብሉይ ኪዳን ውስጥ የተነገሩ ልዩ ልዩ ትንቢቶችን አንሥተው ‹‹ተብሎ እንደ ተጻፈ››፣ ‹‹ተብሎ እንደ ተነገረ›› እና መሰል መንገዶችን በመጠቀም ትንቢቱ መፈጸሙን ያበስራሉ፡፡ እንዲህ ሲያደርጉ ግን ታሪኩ በትክክል በተፈጸመበት ቦታ ላይ በመጥቀስ ነው፡፡

የገድለ አርሴማ አዘጋጅ ‹‹በዚያችም ከተማ ወንጌልን ሰብከው እጅግ ደቀ መዛሙርትን ካደረጉ በኋላ፥ የደቀ መዛሙርትን ልብ እያጸኑ በሃይማኖትም ጸንተው እንዲኖሩ እየመከሩና፤ ወደ

[126] የሚያዝያ ገድለ አርሴማ ቍጥር 98፡፡

እግዚአብሔር መንግሥት በብዙ መከራ እንገባ ዘንድ ያስፈልገናል እያሉ፥ ወደ ልስጥራን ወደ ኢቆንዮንም ወደ አንጾኪያም ተመለሱ›› (የሐዋርያት ሥራ 14፥21-22) ተብሎ በሐዋርያት ሥራ ላይ ያለውን ጥቅስ ጠቅሶ ትንቢት በማስመሰልና ትንቢቱም በአርሴማ ነው የተፈጸመው ለማስኘት ‹‹ብርን በእሳት እንደሚፈትኑት እግዚአብሔር ወዳጆቹን በመከራና በችግር ይፈትናቸዋል፡፡ ይህቺም ቅድስት አርሴማ መጀመሪያ በብዙ መከራና ስቃይ ፈተናት፡፡ በብዙ መከራ ወደ መንግሥተ ሰማያት እንገባ ዘንድ አለንና ብሎ መጽሐፍ እንደ ተናገረ ይህንም ቃል ለመፈጸም ብፅዕት ቅድስት አርሴማ የመከራውን ሸክምና የእሳቱን ዋይታ ታገሠች፡፡ ስለዚህም እርሷ ከሴቶች ልጆች ትበልጣለችና…›› የሚል ሐሳብ ያስነብባል፡፡[127]

የመጽሐፉ አዘጋጅ እዚህ ጋር ልዩ ልዩ ስሕተቶችን ሠርቷል፤

- ጥቅሱን ያለ መልእክቱ መጠቀሙ የመጀመሪያው ስሕተት ሆኖ ይታያል፡፡ ‹‹ወደ እግዚአብሔር መንግሥት በብዙ መከራ እንገባ ዘንድ ያስፈልገናል›› ያለው ጳውሎስ ሲሆን፤ ይህን የተናገረውም በትንቢት መልክ አይደለም፡፡ በልስጥራን ሆነው ወንጌልን በመስበክ ላይ ሳሉ እግሩ የሰለለችበትን አንድ ሰው አገኙና ፈወሱት፡፡ ይህን ተኣምር የተመለከቱ የአገሬው ሰዎች ‹‹አማልክት ሰዎችን መስለው ወደ እኛ ወርደዋል›› በማለት ለአማልክቶቻቸው የሚያደርጉላቸውን ሁሉ ሊያደርጉላቸው ሲሉ ሐዋርያቱ ልብሳቸውን በመቅደድ ጭምር ተቃውሟቸውን በማሰማታቸው ሊያደርጉ አስበውት የነበረው ነገር ቀረ፡፡

[127] መቅድም ቊጥር 23-24 ተመልከት፡፡

ይህን የሰሙና ቀደም ሲል ከሌላ ከተማ ያሳደዷቸው አይሁዳውያን እዚህ ድረስ መጥተው አሁን መሥዋዕት ሊያደርጉላቸው የነበሩትን የአገሬውን ሰዎች በማስተባበር ‹‹ጳውሎስን ወገሩ የሞተም መስሎአቸው ከከተማ ወደ ውጭ ጐተቱት፡፡ ደቀ መዛሙርት ግን ከበውት ሳሉ፥ ተነሥቶ ወደ ከተማ ገባ››፡፡ ከዚህ በኋላ በነጋታው ወደ ደርቤን ሔዶ ቀደም ሲል የሰፈረውንና ‹‹ወደ እግዚአብሔር መንግሥት በብዙ መከራ እንገባ ዘንድ ያስፈልገናል›› የሚለውን ንግግር አደረገ፡፡ ሐዋርያው ትናትና ደርሶበት ከነበረው ድብደባ የተነሣ ይህን መናገሩ ትክክል ነው፡፡ ትናንትና እነጳውሎስ እንደ ተቀበሉት ዛሬ መከራን የተቀበለ ሰው ይህን ጥቅስ መሠረት አድርጎ ቢያስተምር ትክክል ሊሆን ይችላል፡፡ ከመከራው ጋር አያይዞ ግን ትንቢቱ በእኔ ተፈጸመ ቢል ፈጽሞ ስሕተት የሆነ ትምህርት ይሆናል፡፡

- ምናልባት እዚህ ጋር አርሴማም እኮ ሰማዕትነትን ተቀብላለች፡፡ ሰማዕትነት ደግሞ በመከራ ውስጥ ማለፍ ነው ይባል ይሆናል፡፡ ነገር ግን ገድሏን ለመረመረ ሰው በመከራና በችግር ውስጥ ማለፏን ሳይሆን ከንገሡ ጀምሮ እስከ ቀሪው ሕዝብ ድረስ ፈርተዋትና ተንቀጥቅጠውላት መኖራቸውን ነው የሚመለከተው፡፡ መከራ ልትቀበል የሄደችው አርሴማ አልፎ አልፎም ቢሆን ንጉሡንና ወታደሮቹን እንዲሁም ቀሪውን ሕዝብ ስትቀጣ ይታያል፡፡ ‹‹ይህንም ቃል ለመፈጸም ብፅዕት ቅድስት አርሴማ የመከራውን ሸክምና የእሳቱን ዋይታ ታገሠች›› የተባለው ከየት የመጣ እንደ ሆነ ግን ግልጽ አይደለም፡፡ አይደለም መከራን ልትታገስ አንድ ጊዜ በጥፊ የመታትን ወታደር ምድር ተከፍታ እንድትውጠው ያዘዘች ሴት ናትና፡፡

- ሌላው ደግሞ መከራን ስለ መቀበሏ ምክንያት ‹‹መንገሥተ ሰማያትን ወረሰች›› የሚለው ነጥብ ነው። በዚህ ሐሳብ መሠረት መንግሥተ ሰማያትን ለመውረስ መከራን መቀበል ግድ ነው ማለት ነው። ሰዎቹ እንዲህ ለማለት ምክንያት የሆናቸው በሐዋርያት ሥራ ላይ ያለው ሐሳብ ሊሆን ይችላል። ነገር ግን ይህ ምንባብ መከራን መቀበል መንግሥተ ሰማያትን ለመቀዳጀት ያበቃል ማለቱ እንዳልሆነ መረዳት አስፈላጊ ነው። ሐዋርያው መከራን እየተቀበለ ያለው ስለ ክርስቶስ ፍቅር በመሆኑና በጌታችን በማመን ወንጌልን እየመሰከረ ያለ የክርስቶስ ባሪያ በመሆኑ መንግሥተ ሰማያትን የተቀዳጀው ቀድሞ ባመነ ሰዓት እንጂ አሁን መከራን እየተቀበለ ባለበት ወቅት አይደለም። ታዲያ ለምንድን ነው እንዲህ ያለው? ቢባል የክርስትና ጉዞ ዋጋ የሚያስከፍልና ብዙ መከራና ችግር ያለበት ቢሆንም በዚህ ውስጥ ጸንቶ መቆም አስፈላጊ መሆኑን ለማብሰር ነው። ሐዋርያው ምንም እንኳ ቀደም ሲል መንግሥተ ሰማያትን ለመውረስ የታደለ ቢሆንም እየደረሰበት ባለው መከራ ምክንያት ወደ ኋላ ቢያፈገፍግ ወይም ደግሞ መከራውን ፈርቶ ክርስትናውን ቢተው ከዚህ ዘላለማዊ ሕይወት ይጎድላል ማለት ነው።

## የእርስ በእርስ ተፋልሶ

በዚህ ርዕስ ስር ገድለ አርሴማ እርስ በእርስ ያለውን ተፋልሶ ለማሳየት ተሞክሯል።

1. ሰማዕት ለመሆን ከወሰኑትና በኋላ ላይ አርሴማ ከተቀላቀለቻቸው ውስጥ አንዱ የሆነው በርቲኖስ

‹‹ከመሞቴ በፊት ባገኝ ውሃ እጠጣ ዘንድ እወድዳለሁ›› ሲል ሌላኛውና አስፍሰጢስ የተባለው ደግሞ ‹‹እኔ ተርቤአለሁ በእውነትም እነግራችኋለሁ ብሎ ጮኸ፡፡ የአንዲት እንጀራ ቍራሽ ከቀመስንና እፍኝ ቀዝቃዛ ውሃ ከጠጣን ሰባት ቀንና ሰባት ሌሊት ሆኖናል›› የሚል ሐሳብ ያቀርባል፡፡

ይህን ስትሰማ የነበረችው አርሴማ ‹‹ስለ ማዕድ ወደ ጌታችን እንጸልይ›› ስትላቸው ‹‹ቡርክት ሆይ ስለ እኛ ጸሎትን አድርጊ›› ብለው ራሷን ይጋብዟታል፡፡ ገድሉ እንደሚለው ‹‹በአንድነት ተነሥተው ወደ እግዚአብሔር ጸለዩ››፡፡

ከዚህ ታሪክ በፊት ደግሞ አርሴማ ንጉሡ አስጠርቶ ካነጋገራት በኋላ ሰማዕታቱ ወዳሉበት ስትመለስ ‹‹ሰላምታ ሰጠቻቸው እነሱም ሰገዱላት ሰላምታም ሰጡአት፡፡… እኅታችን፣ እመቤታችን ቡርክት ቅድስት አርሴማ ሆይ አሉአት፡፡… አከበሯት፣ ፊጽመውም ከፍ ከፍ አደረጉአት›› ተብሎ ተጽፏል፡፡

ከዚህ በላይ ከሰፈሩት ነጥቦች ውስጥ አንባቢው ከዚህ በታች የተደገሙትን ትኩረት እንዲያደረግባቸው እጠይቃለሁ፤

- ውሃም ሆነ ምግብ ለማግኘት እንደሚፈልጉ ሐሳባቸውን ለመግለጽ በሚገባ መናገራቸውን፣
- አርሴማ ስትመጣ ለመስገድ ጉልበት (አቅም) የነበራቸው መሆኑን
- ከአርሴማ ጋር ለጸሎት ተነሥተው መቆማቸውን፡፡

ይህ ማለት ሰዎቹ ምንም እንኳ ለሰባት ቀናት ምግብ ያልበሉና ውሃ ያልጠጡ ቢሆኑም ጉልበታቸው የማይንቀጠቀጥና

ያልደከመ፣ እንደበታቸው ያልታሰረና መንቀሳቀስ የሚችሉ ናቸው ማለት ነው።

አርሴማ ለጸሎት በተነሣችበት ሰዓት ጸሎቷ እንዴት ነበር የሚለው ሲታይ ግን ከዚህ የራቀ መሆኑን ማስተዋል ይቻላል። ጸሎቷም የሚከተለውን ይመስል ነበር፤ ‹‹ጌታዬና አምላኬ ሆይ ስለ እነዚህ ቅዱሳን ሰማዕት እለምንሃለሁ፤[128] እማለድሀለሁ። የእነርሱም ጸሎት ትርዳኝ። በአንተም ዘንድ የተወደደች ትሁን ኃይላቸው ደክሞአል፣ ጉልበታቸው ተንቀጥቅጦአል፣ የሆዳቸው አንጀት ተጣግቶአል፣ አንደበታቸው ታሥሮአል፣ አፋቸው መርሮአል፣ ጎሮሮአቸው ተዘግቶአል፣ ከረሀቡና ከጥማቱ ብዛት የተነሣ ፈጽሞ መንቀሳቀስ አልቻሉም››።[129] ቀደም ሲል በቀረበው ክፍል ላይ ግን ሰዎቹ ሲንቀሳቀሱ፣ ሲሰግዱ፣ ሐሳባቸውን በተቀላጠፈ መንገድ ሲያቀርቡና አብረዋት ለጸሎት ሲተባበሩ ይታያል።

2. ንጉሡ ለጣዖቱ መሥዋዕት እንዲያቀርቡ ሰማዕታቱን በማስገደድ ላይ ሳለ የጣዖቱ ካህናት መጡና አማልክቶቹ እንደጠፉና እንደ ተሰባበሩ ይነግሩታል። በዚህ ጊዜ ምን ይሻላል? ‹‹አማልክቶቻችን በእርስዋ ኃይል ተጣሉ የተሰበሩና የተበታተኑ ሆነዋልና። እንደ እነርሱ እንዳታደርገን እኛም እርስዋን እንፈራለን። የምንሠዋውን

[128] ምንም እንኳን ለሰባት ቀናት ያልበሉት አብረው ቢሆንም አርሴማ በዚህ ስፍራ ላይ ስለ እነርሱ ስትጸልይ ራሷን አግልላ ነው። በዚህ ጸሎቷ እርሷ ርሀቡ ምንም ያልነካት ይመስላል። ጥቂት ዝቅ ብላ ግን ‹‹አሁንም አቤቱ ምግባችንን ትሰጠን ዘንድ፤ ይቅርታህንና ምሕረትህን እንፈልጋለን፤ እንታመናለን። ያም ባይሆን አበርታን የሚፈታተንን ይህን ረሀብና ጥም እንችል ዘንድ በኀይልህ አጠንክረን›› ስትል ይታያል።
[129] የግንቦት ገድለ አርሴማ ቍጥር 56-61 አጽንዖት የግል።

መሥዋዕትና የምናርደውን ላም የሚቀበለን የለም።... ከጠላቶቻችን እጅ ማን ያድነናል? ምግባችንና ልብሳችን ማን ይሰጠናል? በየጊዜውና በየዘመኑ ዝናም ማን ያዘንብልናል?...›› የሚል ጩኸት ያሰማሉ።

በዚህ ጊዜ አንዱ ተነሥቶ ‹‹ንጉሥ ድርጣድስ ሆይ ይህቺን ሴት መገደሏን ካላፈጠንህ አንተ በክፉ ሞት ትሞታለህ›› አለው። ሌላኛውም እንዲሁ ተነሥቶ ‹‹ንጉሥ ሆይ እርሷን የምትወድ አትሁን የእርስዋን ፍቅር አታስብ ጠባቂዋ ተበቅሎ በምድር ፊት ያጠፋሀል...›› የሚል አስተያየት ያቀርባል። የሁለቱ ሰዎች አስተያየት ያስቆጣው ንጉሥ አስተያየት የሰጡትን ሁለት ሰዎች በሞት ይቀጣቸዋል። ይህን ተከትሎ የገድሉ ጸሐፊ ‹‹ሁለቱም ሰማዕት ሆኑ›› ይላል።

‹‹ሰማዕት›› የሚለው ቃል ትርጉም ‹‹ሃይማኖታቸውን መስክረው በሰማዕትነት የሞቱና የሚሞቱ ማለት›› መሆኑን የቤተ ክርስቲያን መጽሐፍ ይናገራል።[130] መዛግብተ ቃላትም ‹‹በእምነቱ፣ በሃይማኖቱ ምክንያት የተገደለ››፣[131] ‹‹ስለ ክርስቶስ መንግሥት የሚመሰክር ተጋዳይ ራሱን ለስለት ለእሳት አሳልፎ የሚሰጥ ሰማዕት ምስክር እንደ ቅዱስ እስጢፋኖስ ስለ ክርስቶስ እግዚአብሔርነት በእውነት መስክሮ ቀዳሚ ሰማዕት የተባለ ቅዱስ ሰማዕት›› በሚል

[130] የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ታሪክ ከልደተ ክርስቶስ እስከ 2000 ዓመተ ምሕረት፤ (2000) ገጽ 257። ተሰማ ሀብተ ሚካኤል ግጽው፣ ከሣቴ ብርሃን ተሰማ ዐማርኛ መዝገበ ቃላት (2005 - ሦስተኛ ዕትም) ገጽ 234።

[131] ባህሩ ዘርጋው ግዛው፣ ዘርጋው ከፍተኛ የኣማርኛ መዝገበ ቃላት (መጋቢት 2006) ገጽ 174

ያስቀምጡታል፡፡[132] በገድሉ ላይ እንደሰፈረው ደግሞ እነዚህ ሁለት ሰዎች ጣዖት አምላኪና አርሴማ እንድትሞት የፈረዱ ሰዎች ሆነው ሳለና የሞታቸውም ምክንያት አርሴማ ትሙት ማለታቸው መሆኑ እየታወቀ እንዴት ነው ታዲያ ሰማዕት ሆኑ የተባለው?

በዚህ ስፍራ ላይ ያለው የገድሉ ችግር ይህ ብቻ አይደለም፡፡ ንጉሥ የመጀመሪያውን ሰው ‹‹ከሁለት ክፍል›› በመቍረጥ ገድሎ ሲያበቃ ሁለተኛውን ከመግደሉ በፊት፤

> ቅድስት አርሴማ ስለሚሉአት ስለዚህች የምትደነቅና የምትፈራ ሴት፣ እኔ ፈጽሜ አደንቃለሁ፡፡ እርስዋን የሚመስል በምድር ሁሉ አላገኘሁምና፡፡ ከአባታችን አዳምና ከእናታችን ሔዋን ልጆች በሰማይ በታች፣ ወይም በምድር ላይ ሥራዋ የሚያስደንቅ፤ የመልኳም ውበት ዕፁብ ነውና፡፡ በፀሐይ ላይ ያለ የብርሌን መልክ ትመስላለች፡፡ ብርሃንን ወይም መብራትን ምንም አትፈልግም፡፡ የሥጋዋ ንጽህና ነጭና የጠሩ ከሆኑ፤ ሁለመናዋ የበራ ነውና አለ፡፡ ነገሥታትና መኳንንት ደም ግባቷን ቢያዩ ከግርማዋ ከፍታ የተነሣ አድንቀው በሰገዱላት ነበር፡፡ ወርቅና እጅ መንሻም በአመጡላት ነበር፡፡ እኔም ጥላዋ እንዲያገኘኝ በእርስዋ ዘንድ እሰግድላትና እገዛላት ዘንድ እወዳለሁ

[132] የኢትዮጵያ ቋንቋዎች ጥናትና ምርምር ማእከል፣ ኣማርኛ መዝገበ ቃላት (ዐዲስ አበባ፣ 1993) ገጽ 110፡፡

የሚል ንግግር ያደርጋል፡፡

ይህን ንግግሩንም ተከትሎ የገድሉ ጸሐፊ ‹‹ቡርክት ቅድስት አርሴማ ሆይ የረድኤትሽ ጥላ ሁላችን የክርስቲያን ሕዝቦች ለዘላለሙ ይጠብቀን›› የሚል ማጠቃለያ ያስቀምጣል፡፡ ቀደም ሲል በተደጋጋሚ እንደቀረበው ንጉሡ ጣዖት አምላኪ ነው፡፡ በመሆኑም በብዙ ጣዖታት ተከቦ ለባዕዳን አማልክት እየሰገደ ያለ ሰውን ምስክርነት መሠረት በማድረግ እንዲሁም በጾታ ፍቅር ክፉኛ ተነድፎ ‹‹እኔም ጥላዋ እንዲያገኘኝ በእርስዋ ዘንድ እሰግድላትና እገዛላት ዘንድ እወዳለሁ›› ያለ ሰው የተናገረውን ተንተርሶ ‹‹የረድኤትሽ ጥላ ሁላችን የክርስቲያን ሕዝቦች ለዘላለሙ ይጠብቀን›› ማለት መጽሐፍ ቅዱሳዊ መሠረት ያለው ምክር ወይም ትምህርት አይሆንም፡፡[133]

በዚህ ምንባብ ውስጥ ሌሎች ነገሥታትም ሆኑ በፍቅሯ የተሸነፈው ንጉሥ እንደሚሰግዱላት የተጠቀሰ ነገር አለ፡፡ እነዚህን ነገሮች መሠረት በማድረግ ስግደት ይገባታል የሚል ሰው ቢኖር ፈጽሞ ስሕተት ይሆንበታል፡፡ ምክንያቱም እነዚህ ሰዎች ቃለ እግዚአብሔርን የማያውቁና በጣዖት አምልኮ ውስጥ ያሉ ሰዎች ናቸውና፡፡

3. በገድሉ ላይ የሰፈረው የአርሴማ ታሪክ እንደሚያስረዳው አርሴማና ንጉሥ ድርጣድስ የተገናኙት ከሮም በስደት በመጣችበት ሰዓት ሃያ ሰባቱ ሰማዕታት መከራን ሲቀበሉ ተመልክታ ከእነርሱ ጋር ሰማዕት ለመሆን ፈቅዳ ከተቀላቀለቻቸው በኋላ ነው፡፡ ይሄውም የሆነው የንጉሥ ባለሟል ላግባሽ ብሎ ፈቃደኛ ባለመሆኗ ምክንያት ንጉሡ

[133] የሰኔ ገድለ አርሴማ ቍጥር 33-39

ወዳለበት ቤተ መንግሥት ይዟት በመሄዱ መሆኑን መመልከት ይቻላል።[134] በዚያው መጽሐፍ ውስጥ ባለውና ባለ ዐሥራ ሁለት ምዕራፉ ተኣምረ አርሴማ ውስጥ ግን ‹‹ንጉሣችን ድርጣድስም የመምጣትዋን ነገር በሰማ ጊዜ እርስዋን ለመቀበል ከብዙ ሠራዊቱ፣ ከመኳንንቱና ከሕዝቡ ሹሞች ጋር ከክብሩ ዙፋን ተነሥቶ ወጣ›› በማለት ለመጀመሪያ ጊዜ የተገናኙት ንጉሡ እርሷን ለመቀበል በመሄዱ ነው ይላል።[135] ንጉሡና አርሴማ ለመጀመሪያ ጊዜ የተገናኙት በየትኛው መንገድ ይሆን? እሷ ወደ እርሱ ተወስዳ ወይስ እርሱ ወደ እርሷ መጥቶ?

## ሕግን የታመኑ የዘላለም ሕይወት ይወርሳሉ

መጽሐፍ ቅዱስ ሕግን በተመለከተ ‹‹… በሙሴም ሕግ ትጸድቁበት ዘንድ ከማይቻላችሁ ሁሉ ያመነ ሁሉ በእርሱ [በክርስቶስ] እንዲጸድቅ በእናንተ ዘንድ የታወቀ ይሁን››፣ ‹‹አፍም ሁሉ ይዘጋ ዘንድ ዓለምም ሁሉ ከእግዚአብሔር ፍርድ በታች ይሆን ዘንድ ሕግ የሚናገረው ሁሉ ከሕግ በታች ላሉት እንዲናገር እናውቃለን››፣ ‹‹ከሕግ ሥራ የሆኑት ሁሉ በእርግማን በታች ናቸውና፤ በሕግ መጽሐፍ በተጻፉት ሁሉ ጸንቶ የማይኖር የማያደርግም ሁሉ የተረገመ ነው ተብሎ ተጽፎአልና›› የሚል ሐሳብ አለው (የሐዋርያት ሥራ 13፥38-39። ሮሜ 3፥19። ገላትያ 3፥10)። በእነዚህ ሐሳቦች ላይ እንደሰፈረው ሕግ ለሰው ልጆች ለመዳን (የዘላለም ሕይወት ለመውረስ) ዋስትና አይሰጥም። ከዚያ ይልቅ ‹‹እንግዲህ ምን እንላለን? ሕግ ኀጢአት ነውን? አይደለም፤ ነገር ግን በሕግ

---

[134] የመጋቢት ገድለ አርሴማ ቍጥር 10-15።

[135] ተኣምረ አርሴማ ምዕራፍ 1 ቍጥር 6።

ባይሆን ኀጢአትን ባላወቅሁም ነበር፤ ሕጉ አትመኝ ባላለ ምኞትን ባላወቅሁም ነበርና። ኀጢአት ግን ምክንያት አግኝቶ ምኞትን ሁሉ በትእዛዝ ሠራብኝ፤ ኀጢአት ያለ ሕግ ምውት ነውና። እኔም ዱሮ ያለ ሕግ ሕያው ነበርሁ፤ ትእዛዝ በመጣች ጊዜ ግን ኀጢአት ሕያው ሆነ እኔም ሞትሁ›› በማለት ሕጉ ለፍርድ እንደ መጣና የሰው ልጆችን ኀጢአተኝነት እንደሚያሳይ ነው የተጻፈው (ሮሜ 7፥7-9)።

ከዚህ ውጪ የሆኑና ኢየሱስን መስበክ ትተው ሙሴን በመስበክ ላይ ያሉ አገልጋይ ነን ባዮች በክርስቶስ የመጣልንን ጸጋ ሳይሆን በሙሴ የተሰጠውን ሕግ ከፍ ከፍ በማድረግ ላይ መሆናቸውን በገድለ አርሴማ ውስጥ ‹‹በፈጠረላቸው ሕግና ሥርዓት የታመኑት ግን የዘላለም ሕይወትን በትንሣኤ ይነሣሉ።››[136] በሚል የሰፈረውን በማየት ማስተዋል ይቻላል።[137] ስለዚህም ከእንዲህ ዓይነቱ እንግዳ ትምህርት ራስን መጠበቁ ክርስቲያናዊ ግዴታ ነው።

---

[136] የሚያዝያ ገድለ አርሴማ ቊጥር 81።

[137] እንዲህ ያለውን ሐሳብ ገድለ አርሴማ ውስጥ ብቻ ሳይሆን በዚህ ዘመን ያሉና ራሳቸውን የዐዲስ ኪዳን አገልጋይ አስመስለው እያቀረቡ ያሉ አገልጋዮችም ዘንድ ይታያል። ከእነርሱም መካከል ‹‹መምህር›› ዘበነ ለማ አንዱ ናቸው። እርሳቸውም ‹‹የሙሴን ሕግ አስቡ›› በሚል ርዕስ በለቀቁት ስብከታቸው ውስጥ ‹‹እንዳትጠፉ፣ በሲኦል እንዳትወድቁ፣ በዘላለም ስቃይ እንዳትሰቃዩ፣ ከሚመጣው መከራ ከአስደንጋጩ መቅሰፍት ትድኑ ዘንድ የሙሴን ሕግ አስቡ››፣ ‹‹ለመዳን ከተሠጠ አንዱ ዋናው ነገር እግዚአብሔር ለሙሴ የሰጠውን ታቦት ማክበርና በእሱ እግዚአብሔርን ማምለክ ነው›› በማለት ነገረ ድነታችን ከክርስቶስ ጋር ሳይሆን ከሕጉና ሕጉ ከተጻፈበት ከጽላቱ (እሳቸው ታቦት እያሉ የሚጠሩት) ጋር የተሳሰረ በማስመሰል ነገረ ክርስቶስን ቸል እንድል ሲጋብዙን ነበር (ዘበነ ለማ (መምህር)፣ የሙሴን ሕግ አስቡ - የስብከት ድምፅ ወምስል 4፡21-5፡27፤ 15፡00-15፡35 ደቂቃ)።

# ማጠቃለያ

በብዙ ሰዎች ዘንድ አርሴማ ክርስቲያን ሰማዕት ናት፣ ብዙዎች እንደሚያምኑት በነገሥታት ፊት ቆማ እምነቷን የመሰከረች ጽኑ ሰማዕት ናት፡፡ ከዚህም የተነሣ አሁን አሁን አርሴማ ከቅዱሳን ወይም ከሰማዕታት አንዷ ብቻ ሳትሆን ልቃ እና ገና የምትታይ ሆናለች፡፡ ብዙዎች አብያተ ክርስቲያናትና አድባራት በደባልነትም ቢሆን ታቦተ አርሴማን በማስገባት ላይ መሆናቸውን ስናስተውል የተፈጠረውን ተጽዕኖ ለመረዳት ያስችላል፡፡

ከዚህም ሁሉ በላይ ለአርሴማ ተብሎ የተመረጠው ቀን ስድስት መሆኑ ከሠላሳው ቀናት አንዱ (በወር ውስጥ አንዴ) ብቻ ስሙ ይጠራ የነበረውን ኢየሱስን ሙሉ በሙሉ ለመሸፈን የተሠራው ሥራ ውጤታማ መሆኑን ያሳያል፡፡ ይህም ደግሞ ኢየሱስ የሚለውን ስም የማይወደው ጠላት ስሙን ከቤተ ክርስቲያን ለማስወጣት እየሠራ ያለው ሥራ አንዱ አካል መሆኑ ግልጽ ነው፡፡ ዛሬ በቅዱሳን ስም በማደብዘዝ ላይ ሲሆን ነገ ደግሞ…፡፡

ለስመ ኢየሱስ ፍቅር ያላቸው የቤተ ክርስቲያን አባቶች እና አገልጋዮች ‹‹እነርሱም ስለ ስሙ ይናቁ ዘንድ የተገባቸው ሆነው ስለ ተቈጠሩ ከሸንጎው ፊት ደስ እያላቸው ወጡ›› የሚለውን ቃል በማስታወስ ስለ ስሙ ሊናቁ እንጂ ስሙ ሲናቅና በሌላ አካል ሲሸፈን ዝም ብለው ሊመለከቱ እንደማይገባ ሊያስተውሉ ይገባል (የሐዋርያት ሥራ 5፥41)፡፡

ከእርሱ ውጪ ማንም የለንም፤ ከእርሱም ሌላ በሕይወታችን ላይ ልናነግሠውም ሆነ ስፍራ ልንሰጠው የምንችለው አካል የለም፡፡ መጽሐፍ ቅዱስ ከእርሱ ሌላ ማንም በሕይወታችን ላይ

ቦታ እንዲኖው አይፈቅድም፡፡ ስለዚህም ወቅትና አጋጣሚ እየጠበቁ የሚመጡ ‹‹ቅዱሳን›› የእርሱን ቦታ እንዲይዙና ስፍራውን እንዲቆጣጠሩት መፍቀድ አይኖርብንም! አለበለዚያ ግን ከፈቃደ እግዚአብሔር ውጪ እየኖርን ነው ማለት ነው!

**አምላክ ሆይ በሕይወታችን ላይ አንተን ብቻ ከፍ ከፍ ማድረግ እንድንችል እርዳን!!**

# ዋቢ

ማኅበረ ቅዱሳን፣ (ሚያዝያ 1999 ዓመተ ምሕረት) ሐመረ ተዋሕዶ፤ የሐመር መጽሔት ልዩ ዕትም መጽሐፍ። ዐዲስ አበባ፣ አማኑኤል ማተሚያ ቤት።

ማኅበራነ ቅድስት አርሴማ፣ (1995 ዓመተ ምሕረት)፣ ገድለ ቅድስት አርሴማ ግእዝና አማርኛ። ዐዲስ አበባ፣ ማተሚያ ቤት ያልተጠቀሰ።

በጽሐ ዓለሙ (መምህር)፣ (ሚያዝያ 2009 ዓመተ ምሕረት)፣ ታአዶኮስ። ጎንደር፣ ኅትመት ፋር ኢስት ትሬዲንግ ኃላ. የተ. የግ. ማኅበር።

ባህሩ ዘርጋው ግዛው፣ (መጋቢት 2006 ዓመተ ምሕረት)፣ ዘርጋው ከፍተኛ የአማርኛ መዝገበ ቃላት። ርኆቦት አታሚዎች።

ብርሃኑ ብስራት (መልአከ ብርሃን)፣ (መጋቢት 2004 ዓመተ ምሕረት)፣ ገዳማዊ ሕይወት እና ጌቴሴማኒ። ኤች ዋይ ኢንተርናሽናል የኅትመት ሥራዎች ድርጅት ኃላ. የተ. የግ ማኅበር።

ተሰማ ሀብተ ሚካኤል ግጽው፣ (2005 ዓመተ ምሕረት - ሦስተኛ ዕትም) ከሣቴ ብርሃን ተሰማ ዐማርኛ መዝገበ ቃላት። የታተመበት ቦታ እና ማተሚያ ቤቱ ያልተጠቀሰ።

ተስፋ ሚካኤል ታከለ (ተርጓሚ)፣ (2007 ዓመተ ምሕረት)፣ ድርሳነ ኢያቄም ወሐና - በግእዝ እና በአማርኛ። ዐዲስ አበባ፣ ያሬድ ማተሚያ ቤት።

________________፣ (2002 ዓመተ ምሕረት)፣ ገድለ አዳም። የታተመበት ቦታ እና ማተሚያ ቤት ያልተጠቀሰ።

ተስፋ ገብረ ሥላሴ ማተሚያ ቤት፣ (1984 ዓመተ ምሕረት)፣ ገድለ ተክለ ሃይማኖት።
ታፈሰ ለማ (ዲያቆን)፣ (መጋቢት 2009 ዓመተ ምሕረት)፣ በደም የታተመ ክርስትና። አሐዱ ማተሚያ ቤት።
ትንሣኤ ዘጉባኤ ማተሚያ ቤት፣ (1989 ዓመተ ምሕረት)፣ ተኣምረ ማርያም - ግእዝና አማርኛ። ዐዲስ አበባ።
________________፣ (1994 ዓመተ ምሕረት)፣ ገድለ ገብረ መንፈስ ቅዱስና ተኣምረ ገብረ መንፈስ ቅዱስ - በግእዝና በአማርኛ። ዐዲስ አበባ።
________________፣ (1988 ዓመተ ምሕረት)፣ መርሐ ጽድቅ ባህለ ሃይማኖት። ዐዲስ አበባ።
________________፣ (1997 ዓመተ ምሕረት)፣ ወንጌል ቅዱስ ንባቡና ትርጓሜው። ዐዲስ አበባ።
________________፣ (1989 ዓመተ ምሕረት)፣ ድርሳነ ሚካኤል ግእዝና አማርኛ። ዐዲስ አበባ።
ቴዎድሮስ ደመላሽ፣ (ጥር 2010 ዓመተ ምሕረት)፣ ሰማንያ አሐዱ በእግዚአብሔር ቃል ሲመዘን። የታተመበት ቦታ እና ማተሚያ ቤት ያልተጠቀሰ።
ኃይለ ማርያም ሽመልስ ካሣ፣ (2008 ዓመተ ምሕረት)፣ ሥዕለ ቅድስት አርሴማ ዐዲስ አበባ፣ ኅትመት ፋር ኢስት ትሬዲንግ ኃላ. የተ. የግ. ማኅበር።
አማን በላይ (መሪ ራስ)፣ (2000 ዓመተ ምሕረት)፣ መጽሐፈ ብሩክ - ዣንሸዋ ቀዳማዊ። አርቲስቲክ ማተሚያ ቤት።
አንዱ ዓለም ዳግማዊ (መምህር)፣ (ሚያዝያ 1998 ዓመተ ምሕረት)፣ ወላዲተ አምላክ በነገረ ድኅነት። ዐዲስ አበባ፣ ብራና ማተሚያ ድርጅት።

አያሌው ታምሩ (አለቃ)፣ (ሐምሌ 1979 ዓመተ ምሕረት)፣ ወላዲተ አምላክ በኢትዮጵያ። ዐዲስ አበባ፣ ማተሚያ ቤቱ ያልተጠቀሰ።

ኪዳነ ወልድ ክፍሌ (አለቃ)፣ (1948 ዓመተ ምሕረት)፣ መጽሐፈ ሰዋስው ወግስ ወመዝገበ ቃላት ዐዲስ። አርቲስቲክ ማተሚያ ቤት።

ዘነበ ለማ (መምህር)፣ (ሚያዝያ 2009 ዓመተ ምሕረት)፣ መጽሐፈ አሚን ወሥርዓት የሃይማኖትና የሥርዓት መጽሐፍ። ዐዲስ አበባ፣ ኅትመት ፋር ኢስት ትሬዲንግ ኃላ. የተ. የግ. ማኅበር።

___________________፣ የሙሴን ሕግ አስቡ - የስብከት ድምፅ ወምስል

የቅድስት አርሴማ ገድል በአማርኛ (1999 ዓመተ ምሕረት)። አሳታሚው፣ የታተመበት ቦታ እና ማተሚያ ቤቱ ያልተጠቀሰ።

የአብ ሥራ ግሩም፣ (2003 ዓመተ ምሕረት)፣ ለተኣምረ ማርያም አትከራከር የታተመበት ቦታ እና ማተሚያ ቤት ያልተጠቀሰ።

የኢትዮጵያ ቋንቋዎች ጥናትና ምርምር ማእከል፣ (1993 ዓመተ ምሕረት)፣ ኣማርኛ መዝገበ ቃላት። ዐዲስ አበባ፣ አርቲስቲክ ማተሚያ ቤት።

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ታሪክ ከልደተ ክርስቶስ እስከ 2000 ዓመተ ምሕረት፤ (2000 ዓመተ ምሕረት)።

የደብረ ባሕርይ ጋሥጫ አባ ጊዮርጊስና አቡነ በጸሎተ ሚካኤል አንድነት ገዳም፣ (ታኅሣሥ 2004)፣ ገድለ አባ ጊዮርጊስ ዘጋሥጫ እና ገድለ አቡነ በጸሎተ ሚካኤል ግእዝና አማርኛ። ማተሚያ ቤት ያልተጠቀሰ።

# የአዘጋጁ ሌሎች ሥራዎች

1. ሰማንያ አሐዱ በእግዚአብሔር ቃል ሲመዘን፣
2. ኢየሱስ እውነተኛ አማላጅ ጻድቅ ፈራጅ፣
3. የብልጠት ተረቶች፣
4. ለተኣምረ ማርያም አትከራከር (በስስ ኮፒ (በፒዲኤፍ) የሚገኝ)፣
5. የዲያብሎስ ማስታወሻ ደብተር (በስስ ኮፒ (በፒዲኤፍ) የሚገኝ)፣
6. ሃይማኖታዊ እንክርዳድ ቅጽ - ፩ (በስስ ኮፒ (በፒዲኤፍ) የሚገኝ)፣
7. መዛኙ ሲመዘን (በስስ ኮፒ (በፒዲኤፍ) የሚገኝ)፣
8. እንታደስ፣
9. በእንተ ታቦት (በስስ ኮፒ (በፒዲኤፍ) የሚገኝ)።